# የሚለውጥ የእግዚአብሔር ኃይል

አመሰግናለሁ፡ ወንድሜ። [ወንድም ካርል ዊሊያምስ እንዲህ አለ፡ “በእርግጥ ወንድም ብራንሃም ወደ ፊኒክስ ብዙ ጊዜ መምጣቱ ትልቅ እድል ነው። ከየትኛውም ቦታ በበለጠ ወደ ፊኒክስ የሚመጣ ይመስለኛል። ለማነኛውም፡ እኔ እዚህ እስካለሁ ድረስ፡ መምጣቱን እንዲቀጥል እንፈልጋለን። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድም ብራንሃም።”—እርታዒ።] አ—አመሰግናለሁ፡ ወንድም ዊሊያምስ።

እንደምን አደራችሁ፡ ወዳጆቼ። እኔ... ይህ ስለ ሻካሪያን ቤተሰብ ነው፡ ወንድም ዊልያምስና እህት ዊልያምስ እንዲሁም እዚህ ብዙ ሰዎች ስለሱ ያውቃሉ። ከመታመሟ ከሁለት እስከ ሦስት ዓመት ገደማ በፊት፡ በራዕይ አይቼ ነበረና፡ እንዳየሁትም ሆነ።

2 ባለፈው ዓመት እዚህ በነበርንበት ጊዜ፡ ጥር ወር ላይ ይመስለኛል፡ በስብሰባው ላይ እያለን፡ ያ ቄስ (ሰሙ ማን ነበር? ስሙን አሁን ረሳሁት።) እዚህ ነበር። [አንድ ሰው፡ “ስታንሊ” ይባላል አለ።—እርታዒ።] ስታንሊ፡ ቢሾፕ ስታንሊ፡ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እዚህ ነበር። ታስታውሳላችሁ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያመጣልኝ፡ ታውቃላችሁ፡ እንዲህ አለ...

ብዙ ትንቢት ነበር የተናገረው፡ “ልጄ ሆይ፡ ተፈውሰሻል።”

3 ራእዩም እሷ እንደማትድን የተናገረ መሆኑን ያውቅ ነበር። “ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሦስት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ትሞታለች።” ያንን ታስታውሳላችሁ? [የሆነ ሰው፡ “አዎ” አለ።—እርታዒ።] ስለዚህ፡ ሁለት ወይም ሶስት ሰዓት ውስጥ ነበር የምትሞተው።

4 ለዴሞስ መንገር አልቻልኩም ነበር። ለእንጀራ እናቷ፡ እዚህ ቦታ፡ በክፍሉ ውስጥ ነገርኳት። እንዲህ አልኳት፡ “የሚሻላት አይመስለኝም።”

ወይዘሮ ሻካሪያንም፡ “እንግዲህ፡ ሁሉም ሰው ትንቢት እየተናገረ ነው” አለችኝ።

5 እኔም፡ “በእርግጥ፡ እኔ ራሴ፡ ተሳስቼ ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን ተናግሪያለው። እርሷ አይሻላትም” አልኳት።

6 ከሦስት ዓመት በፊት፡ ለብዙዎቻቸው እንዲህ አልኳቸው፡ “ነፍሷንም ለማዳን ስትጣጣር፡ ወደ አልጋዋም ስትሄድ አየኋት። እንደዚህ እጆቿንም አነሳችና፡ ወደ እኔ ጮኸች። እኔም ወደ እርሷ—እንኳን መድረስ አልቻልኩም ነበር። ከዚያም ስትሞት አየኋት። ስመለከትም፡ አንድ ነገር ነበር፡ ሰዓት ነበር፡ በሁለት እና በሦስት ሰዓት መካከል የሚሆን ነገር አለ የሚል ነበር።”

7 ቢሾፑም፡ “እሺ፡ ብቻ ያ እንዴት እንደሚሆን እመለከታለሁ” አለ። ስለዚህ፡ እንዳየሁትም ተፈጸመ።

8 በእርግጠኝነት እዝነናል። ቤተክርስቲያን እህት ፍሎረንስ ሻካሪያን በማጣቷ፡ ታላቅ ሰው እንዳጣች ይሰማኛል። ብቻ፡ ታላቅ ዘማሪ ነበረች፡ በ-መንፈስ የተመላች ሴት ነበረች።

9 ከእናቷ ጋር ነበርኩ፣ እናቷ በተፈወሰች ጊዜ በምዕራብ የባሕር ዳርቻ ካገኘኋቸው፡ ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች አንዷ ነበረች። ኮ... ኮማ ውስጥ ነበረችና፡ ሰውነቷ በሙሉ አብጦ ነበር። እዚያ የ—የነበረው ዶክተር፡ እንዲህ አለኝ፡ “አሁን ስትጸልይ ጸጥ በል። ብዙ ጫጫታ አትፍጠር። ሴቲቱ እየሞተች ነው።”

እኔም፡ “እሺ፡ ወዳጄ” አልኩት።

10 እንዲህ አለኝ፡ ከዚያም፡ መናገሩን ቀጠለ። እና፡ ብቻ፡ እኔ አፌን እንኳ ለመክፈት፡ እድል አልነበረኝም።

11 ስለዚህ፡ ወንድም ዴሞስ እንድሄድና እንድጠይቃት ነገረኝ።

12 ስለዚህ፡ ወደ ላይ ወጣሁ። ፍሎረንስ መሬት ላይ ተንበርክካ ነበር፡ ከዚያም አንዲት ቄንጆ ትንሽ ልጅና፡ ሌሎች ሴቶችም እዚያ ነበሩ። እኔም እዚያ ሄድኩና ጸለይኩላት፡ ነገርኳትም። ራሷን ስታ ነበር። እንደገና እንደሚትነሳ ነገርኳት። ተነሳችም። ከሁለት ዓመት በኋላም፡ ሞተች። አሁንም እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ ይሰጣል።

13 ይህን እናውቃለን፡ ሁላችንም እዚህ የመጣነው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ እናምናለን፡ በተመሳሳይ መንገድም እንሄዳለን። አንድ በአንድ፡ እያንዳንዱ ሰው ያንን መሻገሪያ ይሻገራል። ለዚህም ነው በዚህ የክርስቲያን ሰዎች ህብረት ውስጥ፡ ዛሬ ጠዋት የተሰበሰብነው፡ ይህም እነሱ እንደሚመጡ ስለምናውቅ፡ እነዚህን ነገሮችን ለመናገር፡ ለእነሱም ለማዘጋጀት ነው።

14 አሁን እህት ፍሎረንስ ወጣት ሴት ነች፡ የአርባ-ሁለት አመት ልጅ ነች፡ ወንድም ዊሊያምስ እንደነገረኝ፡ በጣም ወጣት ነች። ይህ በ... በሽታ እንዳለባት ታውቅ ነበር፡ ለምን፡ ስለ እሷ ራእይ አይቼ ነበር፡ ውጤቷንም ነገረችኝ። ከዚያም፡ እግዚአብሔር ሁ... ሁሉንም ያውቃል፡ ከመሞቷ በፊት ኢየሱስን በክፍሉ ውስጥ አይታለች። ስለ እሷ መጸለይ አልፈልግም፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ጸልየናል። እንደ እሳት ሻካሪያን፡ እኛንም ያነቃቃን በመካከላችን ላለው ሕይወት፡ እግዚአብሔርን ማመስገን እንፈልጋለን።

15 ለወንድም ዴሞስና፡ ለእህት ሮዝ መጸለይ እንፈልጋለን። እስታውሱ፡ በሕይወታቸው ውስጥ፡ እስከፊ የሆነ ከባድ ችግር አጋጥሟቸዋል... አባቱ ነው፡ እ... አሁንም ባለፈው ዓመት እህቱ። [አንድ ሰው ወንድም ብራንሃምን እነጋገረ—አርታዒ።] ብቻ፡ አዎን፡ ከአስር፡ ወራቶች፡ ባ... ባነስ ውስጥ፣ እ—እህት ኤድናም፡ እንዲሁ።

16 ስለዚህ፡ ከወንድም ዴሞስ ጋር እንዴት ማዘን እንዳለብኝ አውቃለው። አባቴን፡ ወንድሜን፡ ባለቤቴንና፡ ልጄን፡ በ—በጥቂት ቀናት ውስጥ አጥቻቸዋለሁና፡ ስለዚህ ዛሬ ጠዋት ምን እንደሚሰማው አውቃለሁ። እንዴት እንደሆኑ የሚታውቁት በነዚያ ጫማዎች ውስጥ ስትቆሙ ነው፡ እንዴት ማዘን እንዳለባችሁ የምታውቁት ያኔ ነው። እና...

17 [የፒኤ ሲስተሙ ድምጽ እያሰማ ነው—አርታዒ።] ራሴ ነኝ ያሰጮህኩት። ይቅርታ። እዚህ የሆነ ቦታ፡ በእጄ ነክቼው ነው። ስለዚህ ይ—ይቅርታ በጣም እንድጮኽ አደረኩት፡ እንደዛ ለማድረግ ፈሊጌ አልነበረም።

18 ስለዚህ አሁን የሚትችሉ ከሆነ... ሁላችንም እንቁም፡ እ... አንገቶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

19 የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት አንተን ለማምለክ እዚህ ተሰብስበናል፡ ኢየሱስን ቤዛችንን በመላክህ፡ እናመሰግንሃለን እናወድስሃለንም፡ ሁል ጊዜ እዚህ እንደምንኖር እርግጠኛ አለመሆናችንን ስንመለከት፡ ይህ ሕይወት ካበቃ በኋላ ሌላ ተስፋ አለን። አባት ሆይ፡ እነዚህ ሰጋዎች፡ ምን ዓይነት አስቃቂ ሁኔታ ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ ስናይ፡ እዚህ ዘወትር መቈየት ስለሌብን ደስተኞች ነን። በሞት ሸለቆ ውስጥ፡ ማምለጫ መንገድ ፈጥረሃል።

20 አባት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ከእኛ ጋር፡ ስለነበረው ህይወት፡ ስለ እኅት ፍሎረንስ ሻካሪያን፡ ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ፡ ያንተን ምስጋና እየዘመረች፡ ከእኛ ጋር ስለቆመች እናመሰግንሃለን። አንተም ይህ እንደሚሆን፡ ከብዙ ዓመታት በፊት፡ ነግረኸናል፡ ይህም ለኛ ድንጋጤ አይሆንም ብለሃል። አንተም እውነት እንደምትናገር እናውቃለን። ከዚያም ቃልህ እንዲህ ይላል፡ “ከሴት የተወለደ ሰው፡ ዘመኑ አጭርና በመከራ የተሞላ ነው” ይላል። ይህም እውነት እንደሆነ፡ እናውቃለን፡ ጌታ ሆይ። ሁላችንም በዚያ ሸለቆ በኩል መውረድ እንዳለብን እናውቃለን። ስለዚህ በምድር ላይ ስለነበረው ህይወቷ እናመሰግንሃለን። አሁን፡ ዛሬ ጠዋት፡ ከዚህ መከራ ከሞላበት ቤቷ፡ በፍፁም ልትታመም ወደማትችልበት፡ ወደከበረው አካል እንደገባች በእምነት እናምናለን። እናም የመዘመር ችሎታዋ፡ የነበራት ድምጽ፡ መንፈሷም ከክርስቶስ ጋር በጸጋ የበዛ ነበር! ዛሬ ጠዋት መመለስ ብትችል፡ መመለስ አትፈልግም፣ ይህን ሁሉ እንደገና ማለፍ አለባትና። ይህም፡ አሁን አብቅቷል፡ ከእናቷና ከአባቷ ጋር ነች። ልጆቻቸውን ወደ ቤት ጠርተታዋል። ስለዚህ፡ እ—እናመሰግንሃለን።

21 ለወንድማችን ሻካሪያን፡ ለተወደደው ወንድማችን፡ ያሳለፈውን ሕይወት፡ በእነዚህ የ—የመጨረሻ ቀናት ውስጥ እየደረሰበት ያለውን ሥቃይና፡ እንዴት እየሆነ እንደሆነ በማወቅ፡ ዕድሜው እየገፋ ሲሄድ፡ ፀጉሩም እየሸሸ ሲሄድ፡ ትከሻውም እየጎበጠ ሲሄድ፡ በዚህ ሁሉ ለእግዚአብሔር በመስኩ ላይ ለመቆየት እየሞከረ ነውና፡ መጽናናትን እንዲያገኝ መጸለይ እንፈልጋለን። እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ብርታቱን ስጠው። እግዚአብሔር ሆይ፡ እንዲሰጠው፡ እንጸልያለን። በመሄዷ ላዘኑ ሁሉ ለእያንዳንዳቸው፡ እንጸልያለን።

22 ጌታ ሆይ፡ ይህንን እያሰብን ሳለን፡ እኛም አንድ ቀን መሄድ እንዳለብን፡ እንድናስታውስ አድርገን። እዚህ በጌታ በኢየሱስ ፊት ተሰብስበን ሳለን፡ ይህንን በአዲስ መልክ እንድታስታውሰን እንጠይቅሃለን። በደሙ ስርና በእምነት መሆናችንን፡ እንደነበረው፡ እድንፈትሽ፡ ወይም ህይወታችንን እንድንቃኝ አድርገን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

23 አሁን በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ለሕዝቡ ትንሽ መልእክት ለማድረስ ስሞክር፡ ዛሬ፡ ጌታ ሆይ፡ እንድትረዳኝ እጸልያለሁ። አበርታኝ፡ ምክንያቱም ያ—ያ—ያስፈልገኛል፡ ጌታ ሆይ። እንድታደርገው እጸልያለሁ። አንተን ብቻ የሚያከብር ነገር ይነገር። ዛሬ ጠዋት ድምፃችንን ሲሰሙ፡ ከፊታቸው የሚጠብቃቸውን ዘመን ለመጋፈጥ ዝግጁ ያልሆኑ ካሉ፡ “መንገድ፡ ሕይወት፡ እውነትም እኔ ነኝ፡” ላለው ለእርሱ ራሳቸውን የሚሰጡበት ጊዜ ይሁን። ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ። በስሙ እንጠይቃለንና። አሜን። (መቀመጥ ትችላላችሁ።)

24 [በመድረኩ ላይ አንድ ሰው ለወንድም ብራንሃም እየተናገረ ነው—

እርታዒ።] ይህ ወንድም ሁሉም ሰው በትክክል እየተሰማው እንደሆነ ማወቅ ይፈልጋል። ሁለት የሚሰሩ ማይክሮፎኖች አሉ። ያኛውስ ደህና ነው? ይሰማችኋል? የሚሰማችሁ ከሆነ እጃችሁን አንሱ። ይሰማችኋል? እጃችሁን አንሱ። ደህና።

25 ዛሬ ጠዋት ለሁሉም የሚሆን የመቀመጫ ቦታ ባለመኖሩ አዝናለሁ። እዚህ ለረጅም ጊዜ እንደማልቆይ እናምናለን፡ ምናልባትም የቃሉን ክፍል አንብበን ትንሽ ብንመለከት በቂ ነው፣ ይህም ጌታ እግዚአብሔር እየተነበበ ያለውን ቃሉን ያከብርልን ዘንድ፡ እኛም በእርሱ እንድናገለግለው፡ ከጸጋው ይሰጠን ዘንድ ነው።

26 ዛሬ ጠዋት፡ በቢሊ ፖል እንደተነገረኝ ከሆነ፡ በሚቀጥለው እሁድ በቱክሰን በሚገኘው፡ ግራንትዌይ አሰምብሊ ኦፍ ጋድ ቸርች ላይ እንሰብክ ይሆናል። እዚህ ከቱክሰን የመጣ ሰው ካለ፡ በዚህ ሳምንት ላላያችሁ እችላለሁ። በሚቀጥለው እሁድ፡ ግራንትዌይ አሰምብሊ ኦፍ ጋድ ጉባኤ እገኛለሁ።

27 ስለዚህ አሁን ከምሥራቅ ተመልሰናል፡ እኔ ራሴ በተራራው ላይ ባሉ ሰዎች፡ ከልክ በላይ በሆነው ደግነታቸው ከመጠን በላይ በመብላቴ፡ ሰውነቴ ትንሽ ደክሞታል። እ—እሞኝ ነበር፡ ስለዚህ በዚህ ሳምንት ጥሩ ስሜት አልተሰማኝም። ስለዚህ፡ ጸልዩልኝ።...

28 [አንድ ሰው እንዲህ አለ፡ "በጣም ብዙ ኦፖሰም።"—እርታዒ።"] ምን አልክ? ["በጣም ብዙ ኦፖሰም በላን።"] ወንድም ካርል ዊሊያምስ ቀልደኛ እንደመሆኑ፡ አሁን ያስፈልገናል ብዬ አስባለሁና፡ እንዲህ አለ፡ "በጣም ብዙ ኦፖሱም በላን።" ስለዚያ እንኳን አላውቅም፡ ወንድም ካርል፡ ብዙ ሽኮኮዎች ግን በልተናል።

29 ስለዚህ ዛሬ ጠዋት ለአንድ ሰው መጸለይ ከፈለጋችሁ፡ ይኸው፡ ለ—ለእኔ ብትጸልዩልኝ ደስ ይለኛል፡ ምክንያቱም ያ—ያስፈልገኛል።

አሁን በፍጥነት ወደ ቃሉ መግባት እንፈልጋለን።

30 እዚህም ብዙ ጊዜ ላቆያችሁ አልፈልግም፡ ምክንያቱም ዛሬ ጠዋት፡ በመላ አገሪቱ፡ በቴሌፎን-መስመር በቀጥታ ስርጭት እያዳመጡ እንደሆነ አምናለሁ፡ ከምዕራባዊ ዳርቻዎች ጀምሮ እስከ ምስራቃዊ ዳርቻዎች ድረስ ከሰሜን እስከ ደቡብ ድረስ። እናንተ እዚህ በተብርናክል እንዳላችሁት ብዙ፡ ብዙ ጉባኤዎች ይህን ስርጭት እየተከታተሉ ይገኛሉ። በተጨማሪም በፊኒክስ ውስጥ እየተላለፈ ነው፡ አገልግሎቶች ባሉበት ቦታ ሁሉ፡ በቀጥታ በቴሌፎን እየተሰራጩ ነው... በቤተክርስቲያኖችና በቤቶች ውስጥ፡ እንደዚህ ባሉ ነገሮች ውስጥ ይሰበሰባሉ፡ በጣም ጥሩ በሆነ ሞገድ በኩል እያዳመጡ ይገኛሉ። ከስርጭት እንኳ የተሻለ ነው ይላሉ። ይህ የቴሌፎን-መስመር ነው፡ ሪሲቬር ወይም ማይክሮፎን፡ ወይም ሌላ ነገር፡ በክፍል ውስጥ ያስቀምጣሉ። እነርሱም... ባለፈው ሳምንት፡ ባለቤቴ፡ ከኢንዲያና ወደ ቱክሰን እየመጣን፡ ልክ በክፍሉ ውስጥ ሆኖ እንደማዳመጥ ነው አለች። ስለዚህ የትም ቢሆኑ፡ ዛሬ ጠዋት መስመር ላይ ያሉትን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲባርካቸው እንጸልያለን። በኒውዮርክ ውስጥ አሁን፡ ኦህ፡ ከሰዓት በኋላ ይሆናል፡ በአገሪቱን ሁሉ ሲሰራጭ በተለያዩ ጊዜያት ይሆናል።

31 አሁን በሮሜ መጽሐፍ፡ ምዕራፍ 12ና፡ ቊጥር 1 እና 2 ላይ፡ ይ—ይህን ጥቅስ ማንበብ እንፈልጋለን።

> **እንግዲህ፡ ወንድሞች ሆይ፡ ሰውነታችሁን፡ ሰውነታችሁ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው፡ ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ፡ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፡ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።**
>
> **በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ፡ ይህን ዓለም አትምሰሉ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ፡ እርሱም በ... በጎና ደስ የሚያሰኝ፡ ፍጹምም የሆነው ነገር፡** ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ፡ **በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።**

32 አሁን፡ ጌታ ከፈቀደ፡ ዛሬ ጠዋት፡ **ለመለወጥ የእግዚአብሔር ሃይል** የሚል፡ ርዕስ እወስዳለሁ።

> በልባችሁ **መታደስ ተለወጡ እንጂ፡ ይ... ይህን ዓለም አትምሰሉ፡** አሁን፡ **የእግዚአብሔር** ፈቃድ፡ **እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ፡ ፍጹምም የሆነው ነገር፡** ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ **እወቁ።**

33 ይህ በዘመናችሁ በርካታ ፓስተሮቻችሁ የተጠቀሙበት ጥንታዊና የተለመደ ጥቅስ ነው። ከተጻፈበት ጊዜ ጀምሮ ጥቅም ላይ ውሏል። ነገር ግን፡ ስለ እግዚአብሔር ቃል አንድ ነገር፡ የእግዚአብሔር ቃል መቼም አያረጅም፡ ምክንያቱም ቃሉ እግዚአብሔር ነው። መቼም አያረጅም። በእያንዳንዱ ትውልድ፡ ለሃያ-ሰምንት መቶ ዓመታት፡ ያህል፡ ወይም ከዚያም በላይ፡ ይህ የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች፡ በካህናትና፡ በመሳሰሉት ሲነበብ ቆይቷል፡ መቼም አያረጅም። እኔ ራሴ፡ ለሰላሳ-አምስት ዓመታት ያህል፡ አንብቤዋለሁ። ባነበብኩት ቊጥር፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከትኩትን አዲስ ነገር አገኛለሁ። ምክንያቱም፡ በመንፈስ አነሳሽነት የተጻፈ ነው፡ እግዚአብሔር በደብዳቤ መልክ ነው። እያችሁ፡ የእግዚአብሔር ባህሪያት፡ በወረቀት ላይ ተጽፈው ይገኛሉ።

34 ብዙ ጊዜ፡ ሰዎች፡ “እንግዲህ፡ አሁን፡ ይህን መጽሐፍ ቅዱስ የጻፈው ሰው ነው” ብለዋል። አይደለ። መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው እግዚአብሄር እንደሆነ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ራሱ ይናገራል። የእግዚአብሔር ቃል ነው።

35 በጭራሽ ሊወድቅ አይችልም። ኢየሱስም፡ “ሰማይና ምድር፡ ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም” ብሏል። እግዚአብሔር በመሆኑ፡ ቃሉ ሊወድቅ አይችልም፡ ምክንያቱም የእርሱ አካል ነውና።

36 እናንተም የእርሱ ወንድና ሴት ልጆች በመሆናችሁ፡ የዚያ አካል ናችሁ፡ ይህም የእርሱ አካል እንድትሆኑ ያደርጋችኋል። ስለዚህም ነው በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ አብረን ወደ ህብረት የምንመጣው።

37 አሁን ይህ ቃል **ተለወጠ**፡ የሚለውን ትናንት፡ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ተመለከትኩት። እና፡ የሚናገረውን ጥቅሱን ስፈልግ፡ እዚሁ መገኘት የሚገባኝ ሰዓት ሊዛነፍብኝ ነበር፡ እና ይህን ቃል አገኘሁ፡ ወይም ይህን ጽሑፍ፡ ይልቁንም፡ ቃሉን አገኘሁት። ይህ ቃል በዚህ በመዝገበ ቃላት ውስጥ “አንድ ነገር ተቀየረ”

የሚል ትርጉም አለው። “መቀየር” እንደ ማለት ነው። **ተለውጧል**፡ ማለት “ከነበረበት የተለየ ሆኗል፡ ... ባህሪው በውስጡ ያለው ነገር ሁሉ ተቀይሯል” ማለት ነው፡ **መለወጥ**።

38 ዛሬ ጠዋትም ዘፍጥረት 1ን፡ ትዝ አለኝ። ይህ ዓለም ቅርጽ የሌለውና፡ ባዶ ነበር፡ ጨለማም በምድር ላይ ነበር፣ በባዶነት የተሞላ ብቻ ነበር። ይህ ዓለምም በዚያ ሁኔታ ላይ በነበረ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃው ላይ ሰፍፎ ነበር። እናም ሙሉ ምስሉ ተቀየረ፡ ከሙሉ ባዶነት፡ ወደ ዔደን ገነት ተቀየረ። ይህ የእግዚአብሔር የመለወጥ ኃይል ነው፡ ምንም ያልሆነን ነገር ወስዶ አስደናቂ ነገርን ሊያደርግ ይችላል። የእግዚአብሔር የመለወጥ ኃይል!

39 ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ፡ እግዚአብሔር ይህንን የኤደን ገነት ሲያዘጋጅ፡ ስ—ስድስት ሺህ ዓመታትን እንደወሰደ እንረዳለን። አሁን፡ እሱ ያን ያህል ረጅም ላይሆን ይችላል፣ ነገር ግን በመገመትና፡ “በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ቀን፡ በምድር ላይ አንድ ሺህ ዓመት ነው” ካለበት መጽሐፍ ቅዱስ በመውሰድ ነው፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር ጊዜን ቢቆጥር ማለት ነው። እናም ምድርን ለመፍጠር ስድስት ሺህ ዓመታት ፈጅቶበታል፡ በምድር ላይ መልካሙን ዘር ሁሉ ተክሏል። ሁሉም ነገር ፍጹም ነበር።

40 እኔ እንደማስበው፡ ብዙ ጊዜ፡ ተቺዎች እንኳን የዘፍጥረት መጽሐፍን ማንበብ ሲጀምሩ፡ መተቸት ይጀምራሉ፡ ምክንያቱም ያለማቋረጥ እራሱን የሚደግም፡ ወይም እዚህና እዚያ የሚጥላችሁ ይመስላል።

41 ነገር ግን፡ ወደ ጽሑፋችን ከመግባታችን በፊት፡ ሙሴ ራእይ እንዳየ፡ ለአንድ አፍታ እንመለከተው። እግዚአብሔርም ተናገረው። እግዚአብሔርም ሙሴን ፊት ለፊት፡ ከከንፈር ለጆሮው ተናገረው። አሁን፡ ሙሴን እንዳነጋገረው፡ ለሌላ ሰው ተናግሮ አያውቅም። አሁን፡ ሙሴ ከሁሉም ነቢያት ሁሉ የሚበልጥ፡ ታላቅ ሰው ነበር። እርሱ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። አሁንም እግዚአብሔር መናገር ይችላል፡ ድምጽ አለው። ተሰምቷል። እግዚአብሔር መናገር ይችላል።

42 እግዚአብሔርም መጻፍ ይችላል። እግዚአብሔር አስርቱን ትእዛዛት በራሱ ጣት ጽፏል። አንድ ጊዜ በ—በባቢሎን ግድግዳ ላይ፡ በጣቱ ጻፈ። አንድ ጊዜ ደግሞ ዝቅ ብሎ በአሸዋ ላይ፡ በጣቱ ጻፈ። እግዚአብሔር መናገር ይችላል። እግዚአብሔር ማንበብ ይችላል። እግዚአብሔር መጻፍ ይችላል።

43 የጸጋ ሁሉና የኃይል ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው፡ የመለኮታዊ ጥበብ ሁሉ ምንጭ ያለው፡ በእግዚአብሔር ነው። ስለዚህ፡ እርሱ ብቻ ፈጣሪ መሆኑን፡ እናውቃለን። ከእግዚአብሔር ውጪ ሌላ ፈጣሪ የለም። ሰይጣን በጭራሽ፡ መፍጠር አይችልም፡ የተፈጠረውን ብቻ ያበላሻል እንጂ። እግዚአብሔር ግን ብቻውን ፈጣሪ ነው።

44 ስለዚህ፡ በቃሉ ፈጠረ። ቃሉን ላከ። ስለዚህ በምድር ላይ ያስቀመጣቸውን ዘሮች በሙሉ በገዛ ቃሉ ፈጠራቸው፡ ዘሮች ሁሉ በራሱ በቃሉ ሠራቸው፡ ምክንያቱም ዘሩን ለመፍጠር ሌላ ምንም ነገር አልነበረም። አስቀምጧቸው፡ እነርሱም በውኃው አጠገብ ነበሩ። እንዲህ ብቻ አለ፡ “**ይህ** ይሁን፡ **ያም** ይሁን” አለ።

45 አሁን እንደምናውቀው፡ ብዙ ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የማይናገረውን ነገር የሚናገር ወይን ራሱን የሚደግም ይመስላል። ለምሳሌ ያህል፡ በዘፍጥረት

1 ላይ እንዲህ የሚል እናገኛለን፡ “እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፡ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፣ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው” ይላል። ከዚያም ይቀጥላል፡ ብዙ ነገሮች በምድር ላይ ሆኑ።

46 ከዚያም ምድርን የሚያርስ ሰው አልነበረም፡ የሚለውን እናገኛለን። “ከዚያም እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር አበጀው።” ያም የተለየ ሰው ነበር። “የሕይወትንም መንፈስ እፍ አለበት፡ ሕያውም ነፍስ ሆነ።”

47 የመጀመሪያው ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ሲሆን፡ እሱም መንፈስ ነው። ዮሐንስ 4፡ እንዲህ ይላል፡ “እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል” ይላል። እግዚአብሔር ግን መንፈስ ነው። እግዚአብሔር የፈጠረው፡ የመጀመሪያው ሰው፡ መንፈሳዊ-ሰው ሲሆን፡ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ነበር።

48 ከዚያም ይህን ሰው ሥጋ አደረገው፡ ሰውም ወደቀ። ስለዚህ እግዚአብሔር ወደ ታች ወርዶ የወደቀውን ሰው ለመቤዠት፡ በሰው አምሳል ሆነ። እንደ’ኔ ሃሳብ፡ ትክክለኛው የ—የወንጌል ታሪክ ያ ነው።

49 አሁን፡ እግዚአብሔር፡ በስድስት ሺህ ዓመታት ውስጥ፡ እነዚህን ሁሉ ድንቅ ዘሮች ተከላቸው፡ ወይም ይሁኑ በማለት ቃሉን ተናገረ። “**በዚህ** መንገድ ይሁን። **ይህ** ዛፍ ይሁን። **ይህ** ይሁን።” ሁሉም ነገር ፍጹም ነበር። ብቻ ጥሩ ነበር። በእግዚአብሔር ቃል እንደተናገራቸው ሆነው፡ ራሳቸውን መሆን ወዳለባቸው ተክል እንዲለወጡ እነዚህን እያንዳንዳቸውን ዘሮች እንደዛ እንዲሆኑ እግዚአብሔር አዘዛቸው። የኦክ ዛፍ ከሆነ፡ የኦክ ዛፍ ያፈራል። የዘንባባ ዛፍ ከሆነ፡ የዘንባባ ዛፍ ያፈራል።

50 ምክንያቱም፡ ታላቁ ፈጣሪ ቃሉን ልኳል፡ የቃሉም ዘር እውነተኛው ዘር ከመፈጠሩ በፊት የነበር ነው። ቃሉም ዘሩን ፈጠረ። አያችሁ፡ “ዓለምን ከማይታዩ ነገሮች ፈጠረ።” አያችሁ፡ ዓ—ዓለምን በቃሉ ፈጠረ። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ወደ መኖር እንዲመጣ ተናገረ።

51 እግዚአብሔር፡ ፈጣሪ፡ ሁሉንም ነገር ወደ መኖር ያመጣው እርሱ እንደመሆኑ መጠን፡ የተፈጠረው ዓለም ፍጹም መሆን ነበረበት። በጣም የ—የሚያምር ቦታ ነበር። በ—በምድር ላይ እውነተኛ ገነት ነበር።

52 አሁን፡ እያንዳንዱ ቦታ፡ የሆነ ቦታ የሆነ ዋና መስሪያ ቤት ሊኖረው ይገባል። ይህ ጉባኤ ዋና መስሪያ ቤት አለው፡ ይህ ምዕራፍም ዋና መስሪያ ቤት አለው፡ ቤተ ክርስቲያንም ዋና መስሪያ ቤት አላት። እግዚአብሔርም ዋና መቀመጫ አለው። ይህ ታላቅ ቦታ፡ የምንኖርባትም ሀገርም፡ ዋና መስሪያ ቤት አላት። ይህ ታላቅ ዔደን ዋና መስሪያ ቤት ነበረው፡ ዋና መስሪያ ቤቱም በኤደን የአትክልት ስፍራ፡ ወይም በኤደን ውስጥ፡ በአትክልቱ ስፍራ በስተ ምሥራቅ በኩል-ነበር።

53 እግዚአብሔርም በምድር ላይ ያሉትን፡ ታላላቅ ፍጥረታቱ በሙሉ እንዲገዙ፡ ልጁንና የልጁን ሙሽራን፡ አዳምንና ሔዋንን ሾመ።

54 እግዚአብሔር የአዳም አባት ነበር። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት፡ “አ... አዳም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር።” እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር።

55 እግዚአብሔርም ከሰውነቱ፡ አንዲት ረዳት አደረገለት፡ ምናልባትም ከጐድን አጥንቱ አጠገብ ካለው አጥንት ሊሆን ይችላል፡ ይህም ከእሱ

ጋር እንድትቀራረብ አድርጎታል፡ ረዳት አደረገለትም። በእርግጥ ገና ሚስቱ አልነበረችም፡ እርሱንም በቃል ብቻ ተናግሮት ነበር እንጂ፡ ገና ሰው አልሆነም ነበር። እናም ችግሩ የመጣው እዚህ ጋር ነው፡ ሰይጣን ከአዳም በፊት ቀድሞ እሷን ያዛት። ስለዚህ፡ እርሱ የተናገረው የእርሱ ቃል ብቻ ነበር።

56 እንዲህ እላለሁ፡ በዚህ ላይ በጣም ብዙ ጊዜ መውሰድ አልፈልግም። ነገር ግን አንዳንዶቻች ትንሽ ግራ ሊጋቡ ይችላሉ፡ በተለይም በደቡብ አከባቢ ያሉ አንዳንድ ሰዎች፡ ዛሬ ስለ እባብ ዘር፡ ከእግዚአብሔር ተቀብዬ፡ ለሰዎች ያስተላለፍሁት መልእክት፡ ትንሽ ግራ የሚያጋባ ሆኖ ያገኙት ይመስላል። ጌታ ቢፈቅድ፡ በእነዚህ ቀናት ውስጥ፡ ወደ ጀፈርሰንቪል፡ ወደ ቤት እሄዳለሁ። የስድስት-ሰዓት መልዕክት ወስጄ፡ ሁሉንም ማስተካከል እፈልጋለሁ፡ እያችሁ፡ ስለዚህ ያ የሚንናገረውን እንዲታውቁ በትክክል ያስቀምጥላችኋል። ይህም **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው። እኅታችን ፍሎረንስ ከመሞቷ ከዓመታት በፊት፡ ባየችው ጊዜ እንደነበረው ሁሉ እውነት ነው። እያችሁ፡ እውነት ነው። አሁንም፡ ም... ምናልባት በትክክል ሳንረዳው ቀርተን ሊሆን ይችላል።

57 አንድ ሰው ወደ'ኔ መጥቶ፡ ተቃራኒ የሆነ ነገር ቢነግረኝ፡ እኔ ራሴ፡ በተሳሳተ መንገድ ልረዳው እችላለሁ። ማንም ሰው የሚናገረውን መተቸት አልፈልግም። አንዳችን ሌላውን መተቸት የለብንም። ይህን በማድረግ ጥፋተኛ አይደለሁም፣ ጌታን አመሰግናለሁ። ኃጢአትንና አለማመንን ተችቻለሁ እንጂ፥ አንድም ግለሰብ አይደለም፡ እያችሁ፡ አ—አልተችም። ወ—ወንድማማቾችና እህትማማቾች ነን፡ እየጣርን ነው፡ ትናንት ጠዋት እኅት ፍሎረንስ ወደመጣችበት እየመጣን ነው፡ እያችሁ። እ... ሁ—ሁላችንም በዚያ መንገድ መምጣት አለብን። ከእናንተጋር የ—የማይስማማ ወንድም ወይም እኅት ለመተቸት መሞከር ዓላማዬ አይደለም። አይ፡ እንዲህ ማድረግ ከእኔ ይራቅ! የማንንም ስም ስጠራ ቴፕ ውስጥ የምታገኙት አይመስለኝም። ይህም፡ ብዙ ጊዜ አንድ ሰው የተሳሳተ እንደሆነ ይሰማኛል፡ ነገር ግን ያ በእሱ እና በእግዚአብሔር መካከል ነው። ይሁን እንጂ ችግሩ፡ በኃጢአት መንገድ... በትክክል አለመረዳት አንዳንድ ጊዜ ኃጢአት እንኳን አይደለም፡ ሰዎችን በትክክል አለመረዳት ብቻ ነው። እ— እያንዳንዳችን ራሳችንን የመግለጽ መብት አለን ብዬ አስባለሁ።

58 እንግዲህ ይህ ታላቅ ፈጣሪ የተፈጠረውን ልጁን አስቀመጠ። ስለዚህ፡ አዳም እሱ የፈጠረው የመጀመሪያው ልጁ ነበር። ኢየሱስ **አንድያ** ልጁ ነው፡ እያችሁ፡ እርሱም ከሴት ተወለደ። ነገር ግን አዳም በፍጥረት፡ በቀጥታ ከእግዚአብሔር እጅ በቀጥታ ነው የመጣው።

59 አሁን በዋና መሰሪያ ቤት ውስጥ፡ ከ—ከልጁ እና ከልጁ ሙሽራ ጋር ባጠቃላይ፡ እጅግ ፍጹም ይመስላል። ሰው ነበር፡ ለ—ለዚህ ሁሉ ራስ፡ የራሱ ልጅና ሙሽራው።

60 እያንዳንዱ ዘር ፍጹም ነበር፡ ዘንባባ፡ ዋርካ፡ ሣር፡ ወፎችና፡ እንስሳት። ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ትእዛዝ ፍጹም ሥርዓት ውስጥ ነበረ፡ "ተፈጥሯችሁን አትቀይሩ። እያንዳንዱ ዘር፡ ከራሱ ዓይነት ያፍራ! ዋርካ፡ ወደ ፓውፓው ዛፍ በፍጹም አትለውጡ።" እያችሁ? "ዘንባባ፡ ወደ ሌላ ነገር

አትለወጥ። ግን እያንዳንዱ ዘር ከራሱ ዓይነት ያፍራ!" በዘመናት ውስጥ ተ— ተመልክቶት ነበር።

61 ቃሉንም ተናገረ። ታላቁ የመፍጠር ኃይሉ እነዚህን እየመጡ ያሉትን ነገሮችና: ወንድና ሴትን ጭምር ሠራ። እነሱ ራስ ነበሩ ምክንያቱም ከ... ከሌሎቹ ዘሮች ሁሉ በላይ ነበሩ። በተጨማሪም ዛፎችን: እንስሳትንና: የመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ: ሌሎቹን ይመራቸው ዘንድ ከቃሉ ስር እንዳደረጋቸው እነርሱንም ከቃሉ ሰር አደረጋቸው። ቃሉን በምንም አይነት መንገድ: ፈጽመው: ማፍረስ የለባቸውም። በዚያ መኖር ነበረባቸው። "ከዚህ ቃል ምንም ነገር አትቀንሱ: ወይም አትጨምሩ! በዚህ ቃል መኖር አለባችሁ።"

62 ያ ፍጥረት እንደዚያ ቢቆይ ኖሮ: እሳት ሻካሪያን ዛሬ ጠዋት ባልሞተች ነበር: የእግዚአብሔር ታላቅ ሰርአት: እንደዚያ ቢቆይ ኖሮ! ወደዚያ ሁኔታ ወደ ኋላ እየተመለስን ነው ብለን እናምናለን። ወደዚያ ሰፍራ: ወደዚያ ሁኔታ እየመለስን ነው።

63 በዚያ ሰባተኛው ቀን ጠዋት: እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ተመልክቶ: እንዲህ አለ: "ይህ መልካም ነው። ደ—ደስ ብሎኛል። አዎን: ይህን በ— በ—በማድረጌ ደስ ብሎኛል። ያደረግኩት ነገር ሁሉ አሁን በቁጥጥር ሥር ነው። እነሆ ይህ ሁሉ ለልጄና ለሚስቱ አደራ እሰጣቸዋለሁ: እ—እነሱም (በሁሉም ነገር ላይ) ኃላፊነት ይወስዳሉ: ሁሉንም ነገር የሚከታተሉና ሁሉም ነገር ደኅና መሆኑን የሚያረጋግጡ: ሁሉም ነገር የራሱን አይነት እንደሚያፈራ የሚያረጋግጡ ይሆናሉ። አሁን ይህን ለማድረግ የሚያስችል ኃይል አለው" አለ። ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ አለ: "መልካም: ሁሉም ነገር በጣም ጥሩ ከሆነ: ሌላ ምንም ነገር ሊሆን አይችልም: ምክንያቱም የራሴ ፍላጐት ስለሆነ። እንደምፈልገው ነው የሆነው። እኔም እንደዚያው ተናግሬያለሁ: ቃሌም እንደፈለግሁት አደረገልኝ። ይሄው ሁሉም ነገር ሆነ። ሁሉም ነገር ጥሩ ነው!" ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ: "በሰባተኛው ቀን: እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ ዐረፈ" ይላል።

64 ሁሉንም ነገር የራሱን አይነት ለማፍራት: በቊጥጥር ሥር ነበር። አሁን: "ለማፍራት" የሚለውን አስታውሱ። እግዚአብሔር ዘሩን በምድር ሲዘራ: ዘሩ ከዘር ወደ ተክልነት ወይም ምንም ይሁን ምን: ወደነበረበት የሚመለወጠው: በውስጡ ባለው በሕይወት ኃይል ነው። የሚለውጥ ሃይሉ! አሁን: እግዚአብሔር ዘሩን እዚያ ሲያሰቀምጥ: እርሱ እንደተናገረው መሆን ከሚችልበት አቅም ጋር ነው ያሰቀመጠው። በትክክለኛው ምድብ ውስጥ እስከቆየ ድረስ: እግዚአብሔር እንደሚለው በትክክል ይሆናል። በዚያ መንገድ መሆን ነበረበት: ምክንያቱም እርሱ የፈጠረው በዚያ መንገድ ነው: መሰመር ፈጠረ። ያ: በእርሱ ቻናል: በቃሉ መሰመር ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ነገር: ቃሉ በተናገረው መሠረት በትክክል እንደተባለው ማፍራት ይኖርበታል። ከዚያ መንቀሳቀስ አይችልም። በትክክል በመሰመር ውስጥ ገብቷል። ስለዚህ: ሁሉንም ነገር በራሱ ልጅ ላይ በመተማመን: በዚያ መንገድ እንደሚሆን አሰበ: ከዚያ እግዚአብሔር: "ሁሉም መልካም ነው: ስለዚህ ዕረፍት አደርጋለሁ። እናም እያንዳንዳቸው እነዚህ ዘሮች በውስጣቸው: ወደምፈልገው ዝርያ የመለወጥ ኃይል አላቸው። ይህ መሆን ግዴታ አለበት: ምክንያቱም

ለእያንዳንዱ ዘር ከራሱ ውስጥ ለመውጣት፡ እኔ እንደምፈልገው፡ በራሱ አቅም ከራስ ውስጥ እንዲወጣ የሚለውጥ ኃይል ሰጥቻለሁ” አለ።

65 እግዚአብሔር ፈጽሞ አልተለወጠም። ያኔ እንደነበረው ዛሬም ተመሳሳይ ነው! እግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ ቈርጦ ይነሣል። ያደርገዋልም። ምንም ነገር ሊያግደው አይችልም። ያደርገዋል!

66 አሁን ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ እና በቅደም ተከተል ከተዋቀረ በኋላ፡ እግዚአብሔር አሁን ሁሉም ነገር ደኅና እንደሚሆን እርግጠኛ ሆነ፡ ከዚያም፡ ያንን ሲያደርግ፡ ከዚያ ጠላት መጣ። እ... እግዚአብሔር የመለወጥ ኃይል ሰጠ። ይህን ሰው የሚጠራው፡ እ—እንደገና ለመፍጠ ሳይሆን፡ ነገር ግን... የማዛባት ሃይል አለው፡ የማዛባት እንጂ፣ የመለወጥ ኃይል አልነበረውም። አሁን፡ ማንኛውም የተዛባ ነገር ከመጀመሪያው ሁኔታ ተወስዷል፡ የሆነ የተበላሼ ነገር አለ።

67 ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ በቆሎ እርሻዎች ላይ፡ እየተዘዋወርኩ ሳለ፡ አንድ ቅርንጫፍ ከዛፍ ላይ ተሰብሮ፡ በቆሎ ግንድ ላይ እንደወደቀ፡ አስታውሳለሁ። አገዳው እንደታሰበው ቀጥ ብሎ ለመቆም የተቻለውን ሁሉ እየሞከረ ነበር፡ ግን ተጣሞ ነበር ምክንያቱም የሆነ ነገር ስለሆነበት። ቅርንጫፉም በላዩ ላይ ተዘርግቶ ነበር።

68 ከዚያም በእርሻ ውስጥ የዱር አረግ እናገኛለን። ይህም፡ እዚህ ያላችሁ፡ ብዙዎቻችሁ ወንዶች እና ምናልባትም አንዳንዶቻችሁ ሴቶች ከ... ከኬንታኪ ከመጣችሁ ታውቃላችሁ። ሴቶቹም ልክ እንደወንዶች ዶማ ይጠቀማሉ፡ ዶማ ይዘው ወደ እርሻ ቦ—ቦታ ይወጡና፡ እኛ አንገቱ የተጣመመ ዶማ ብለን እንጠራዋለን፡ በ—በዚያ አረጉን ይቆርጡታል። ምክንያቱም፡ እነዚያን አረጎች ካላስወገዳችሁ፡ በቆሎው **እንደዚህ**፡ በመስመር ካለ፡ ከዚያም ያ አረግ ደርሶ፡ ያንን በቆሎ ያንቀዋል፡ ቀስ በቀስም እራሱን በላዩ ላይ ይጠመጠማል፡ ቀለል ባለ መልኩ፡ በብልሃት፡ እየተጠቀለለ ነው ለማለት እስከሚከብድ ድረስ ሳያስታውቅ ይጠመጠማል። በመጨረሻም እየጠነከረና እየጠነከረ ይሄዳል፡ የበቆሎውን ቅርጽ እስኪቀይር ድረስ ይጎትታል። ራሱን በራሱ ይጎትታል፡ በራሱ ተክል ዙሪያ ይጠቀለላል፣ መጀመሪያ ከነበረበት ነገር፡ ወደ ሌላ ነገር ይለውጠዋል። በቆሎ ነው፡ ነገር ግን የተጣመመ በቆሎ ይሆናል።

69 እኛም ሁላችን አሁንም በእግዚአብሔር አምሳል ነን። ነገር ግን አንዳንዶች እንደ እግዚአብሔር ልጆች ሆነው፡ የተበላሹ ናቸው። ከቃሉ ጋር የሚቃረኑና እርሱ እንዳለንና እ—እንድንራመድም ባዘጋጀልን በዚያ መንገድ የማይሄዱ ናቸው። አንድ ነገር በማዘጋጀት፡ ዓለም ከመንገዱ ያርቀናል፡ ወደራሱ እንድንቀርብ ያደርገናል፡ የእግዚአብሔር ወንድ ልጆች እና ሴቶች ልጆች እንድንሆን፡ ቀጥታ ጠባብ አድርጎን ከተከለበት፡ ያወጣናል። ኃጢአት ይህን ክፉ ነገር ያደረገው በእግዚአብሔር ልጆችና ሴቶች ልጆች ላይ ነው።

70 የሚያዛባ! በዚህ መንገድ ስለዚህ ነገር መናገር እንግዳ መስሎ እንደሚታይ አውቃለሁ፡ “ማ—ማዛባት፡” ነገር ግን ሃጥያት ማለት እንደዛ ነው፣ አዛባው፡ ወይም አጣመመው። **ማጣመም** ማለት “መቀየር፡ አንድን ነገር የተለየ ማድረግ” ማለት ነው። **ማዛባትም** ተመሳሳይ ነው፡ በሰላም እየመጣ ሳለ

ተዛባ፡ "በሌላ መንገድ ተሰራ።" ያም ሆኖ ዘሩ ተመሳሳይ ነው፡ ነገር ግን የተዛባ ነው።

71 አሁን ደግሞ ይህ የሚያዛባው እግዚአብሔር ለመለወጥ ግዜ እንዳለው ሁሉ፡ ለማዛባት፡ እኩል ጊዜ አለው። አሁን በ... በኤደን ገነት ውስጥ፡ ዘሩን ተክሏል፡ ወይም፡ ዘሩን ፈጽሞ አልዘራም። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ የእግዚአብሔርን ዘር ይኸውም የእግዚአንሔርን ቃል፡ ለማዛባት፡ የተለየ ነገር ለማድረግ፡ ስድስት ሺህ ዓመታትን ወሰዷል፣ ለ... ለመጀመሪያ ጊዜ ሔዋን እሱን ካዳመጠችበትና፡ ለራሷ አንድ ትንሽ ሀረግ ካገኘችበት ጊዜ ጀምሮ።

72 አስታውሱ፡ ሰይጣን በመጀመሪያ የጠቀሰው የቅዱሳን መጻሕፍትን ሃሳብ እንደሆነ አስታውሰ፡ "እግዚአብሔር፡ 'በኤደን የአትክልት ሰፍራ ካሉት ዛፎች ሁሉ አትብሉ' ብሏልን? " አያችሁ? "ከማንኛውም ዛፍ አትበሉ ብሏልን? "

73 አሁን አስታውሱ፡ ሔዋን እንዲህ አለች፡ "አዎ፡ ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ መብላት እንችላለን፣ ነገር ግን በአትክልቱ ሰፍራ መካከል የሚገኘውን ዛፍ፡ መንካት እንኳ አይገባንም።" አሁን ተመልከቱት፡ በመልእክቱ፡ ያንን ቃል አጣመመ። ሔ... ሔዋን እንዲህ አለች፡ "እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፡ ይህን ብናደርግ፡ በዚያ ቀን 'እንሞታለን" አለች።

74 እንዲህ አለ፡ "ኦህ፡ በእርግጥ አትሞቱም" አለ። አያችሁ፡ እ—እሱ ሰው ነበር፡ እንዲህ አለ፡ "አ—አ—አሁን ይህን አድርጉ። እናንተም፡ በ—በ—በእርግጥ ያልተማሩ ሰዎች ናችሁ። እውነት ነው፡ እናንተ፡ ሁሉን አታውቁም፡ ከዚህ ብቻ ብትካፈሉ ግን፡ ጥበብን ታገኛላችሁ፡ እውቀትም ታገኛላችሁ። የማውቀውን ይህን ጥበብ ብትካፈሉ፡ መልካሙንና፡ ክፉን ታውቃላችሁ እንደ እግዚአብሔርም ትሆናላችሁ። እኔ አውቃለሁ፡ እናንተ ግን አታውቁም" አለ።

75 ይህም፡ ጥበቡን ማግኘት ጥሩ ነው። ነገር ግን ጥበብ ተቃራኒ ከሆነ፡ ጥበብ ከእግዚአብሔር የመጣ ትክክለኛ ጥበብ ካልሆነ፡ መለኮታዊ ጥበብ ካልሆነ፡ ተፈጥሯዊ ጥበብ ከሆነ፡ ምን ያህል ሳይንስ ቢኖረን ግድ አይሰጠኝም፡ ምን-ተጨማሪ ነገር ቢኖረን፡ ወይም ትምህርት ቢኖረን፡ ከዲያብሎስ ነው። ጌታ ቢፈቅድ፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ አረጋግጥላችኋለሁ። ከዲያብሎስ ነው።

76 ሥልጣኔ የዲያብሎስ ነው። በዚያ ላይ ሰብኪያለሁ። በምድር ላይ ያለው ባህል ሁሉ፡ የሳይንስ ኃይሎች ሁሉ፡ ሁሉም ነገር፡ ከዲያብሎስ ነው። በኤደን የአትክልት ሰፍራ፡ የሰበከው፡ የእውቀትን ወንጌል ነው። ያንን እውቀት ወሰደ፡ የተዛባ እውቀት፡ ከቃሉ እና ከፈቃዱ እና ከእግዚአብሔር እቅድ ጋር የሚቃረን እውቀት። አሁን እግዚአብሔር ያደረገውን ለማከናወን ስድስት ሺህ ዓመታት ፈጅቶበታል፡ ያደረገው ግን በተዛባ መንገድ ብቻ ነው፡ እና የራሱን ገነት ለማመቻቸት ተመሳሳይ ጊዜ ፈጅቷል። አሁን በምድር ላይ፡ በጥበብና፡ በእውቀት የተሞላች ገነት አለው። ይህ ከመጀመሪያው የእርሱ ወንጌል ነበር፡ እውቀት፡ ጥበብ፡ ሳይንስ። እግዚአብሔር እንደዚህ ያለ ነገር አይደግፍም። ለ—ለአንድ ደቂቃ እንድትመለከቱት እፈልጋለሁ። ይህን አደረገ፡ ምክንያቱም እርሱ ዓለማዊ ጥበብ ያለው ሰው ስለነበር ነው።

77 አሁን፡ ይህን ለማለት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ለብዙ ዓመታት እኔ እንደነበርኩ፡ ልክ እንደ እኔ ለሚሰማቸው ሰዎች ይህን መናገር፡ በ—በጣም ከባድ ነው። ነገር ግን እነዚያ የተራራው መላእክት፡ ሰባቱን ማህተሞች

ከከፈቱበት ጊዜ ጀምሮ፡ **ይህ** መጽሐፍ አዲስ መጽሐፍ ሆኗል። እግዚአብሔር በራእይ 10 ላይ፡ እንደሚያደርገው ቃል በገባው መሠረት፡ የተደበቁ ነገሮች እየተገለጡ ነው። እኛ ደግሞ እነዚህን ነገሮች ለማየትና ለመረዳት፡ እንድንችል እግዚአብሔር ከምድር፡ የተመረጥን ሰዎች ነን፣ ይህም አንድ ሰው የሚፈጥረው ተረትና፡ ሥጋዊ አእምሮ አይደለም። ይህ የእግዚአብሔር፡ ትክክል መሆኑን፡ የተገለጠ ቃል ነው። የተረጋገጠ ነው። በሳይንስ ሳይሆን፡ በእግዚአብሔር፡ የተረጋገጠ ነው። ከዚህ በፊት ባስተላለፍኩት መልእክት እንደገለጽኩት፡ እግዚአብሔር፡ ቃሉን ማንም እንዲተረጉምለት አይፈልግም። እርሱ ራሱ የራሱ ተርጓሚ ነው። እሱ ይህ ይሆናል ይላል፡ ደግሞም ይፈጸማል። ያ ማለት፡ ያ—ያረጋግጠዋል፡ ይተረጉመዋል።

78 ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ እኛ የጴንጤቆስጤ ሰዎች፡ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት "እብዶች ናችሁ" ሲሉን፡ "ይህ አይቻልም፡ መንፈስ ቅዱስ ያቀረ ነገር ነው" ሲሉን ነበር። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለሚሻው ሰው እንደሆነ ተገንዝበናል፡ አሁን ግን ከዚህ የተሻለውን ነገር እናውቃለን። እያችሁ፡ ቀስ በቀስ፡ ይህ ነገር ተከፍቷል።

79 አሁንም በእነዚያ ሁሉ የቤተክርስቲያን ዘመናት ውስጥ፡ የተደበቁ ምስጢሮች፡ በመጨረሻው ዘመን እንደሚገለጡ ቃል ገብቷል። አሁን ያሳውቀናል። በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። አሁን እዚህ ነን።

80 አሁን፡ ሰይጣን የሰልጣኔ ፈጣሪ ነው። የሳይንስ ፈጣሪ ነው። የትምህርት ፈጣሪ ነው።

"ይህ እውነት ነውን፡" ትላላችሁ?

81 እሺ፡ አሁን የእግዚአሔርን ቃል እናንብብ፡ ዘፍጥረት 4፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን ለአንድ ደቂቃ እንመልከት። በ... በጣም ረጅም ጊዜ ከወሰድኩ፡ ወንድም ካርል ምናልባት ይነግረኛል። ነገር ግን፡ በዘፍጥረት፡ ምዕራፍ 4፡ እና ቍጥር 16 ላይ፡ እግዚአብሔር፡ በወንዱና በሴቲቱ ላይ፡ እርግማን ለማውረድ ምን እንዳደረገ፡ እንዲሁም ምን ማድረግ እንዳለባቸው፡ እንዲሁም ያደርጉት ዘንድ ያላቸውን ሁሉ፡ **እርግማኑ** በእነሱ ላይ ማድረጉ ሳይሆን፡ ምን እንደሚሆን ይነግራቸዋል፡ ምድርን ሰለ አዳም ረገማት። እና አሁን ሔዋን ሁለት መንትዮች ልጆች እንደነበሯት፡ እናያለን። አንደኛው ከሰይጣን ሲሆን፡ ሌላኛው ደግሞ ከእግዚአብሔር ነው።

አሁን እናንተም እንዲህ ትላላችሁ፡ "ኡህ-ኡህ! አይደለም። ተው፡ ወንድም ብራንሃም!"

82 እስቲ አንድ ደቂቃ። ቃየን የአዳም ልጅ እንደሆነ የሚናገር፡ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፡ አግኙልኝ። "ቃየን ከክፉው፡" እንጂ ከአዳም እንዳልሆነ የሚገልፀውን፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አሳያችኋለሁ።

83 እዚህ ላይ እርጉዝ መሆኗን ልብ በሉ። መጀመሪያ፡ በ4ተኛው ምዕራፍ እንጀምራለን።

> **አዳምም ሚስቱን... አወቀ፤ እሷም ፀነሰች፡ ቃየንን ወለደች፡ ከዚያም፡ ከእግዚአብሔር...** ወንድ ልጅ አገኘሁ፡ **አለች።**

84 እርግጥ ነው፡ መሆኑ መች ይቀራል። አመንዝራም ወይም ሌላ ምንም ይሁን ምንም ቢሆን፡ ከእግዚአብሔር የመጣ ነው፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም ያ የእርሱ ዘር ነው፡ የእርሱ ዘር ሕግ ነው፡ የተበላሸ ዘር ይሁን፡ የተዛባ ዘር ይሁን፡ ወይም ምንም ይሁን ምን ያፈራል። ለማንኛውም፡ ያፈራል። እንዲያፈራ የእርሱ ትእዛዝ ነው።

**እንደገናም ወንድሙን አቤልን ወለደችለት።**

85 ከእንግዲህ አወቀው። አዳምም ሚስቱን አወቀ፡ እሷም ቃየንን ወለደች፡ አቤልንም ወለደች። ሰይጣን ያን ቀን ጠዋት ከእሷ ጋር ነበር፡ አዳም በዚያ ቀን ከሰዓት ነበር።

86 አሁን በቱክሰን፡ ያቺ ሴት ጥቁር ልጅና፡ ነጭ ልጅ በአንድ ጊዜ ስትወልድ፡ እዚህ በጋዜጣው ላይ የሚነበበውን ግርግር፡ አይታችኋል። በዚያ ጠዋት ከባለቤቷ ጋር ተኝታ የነበረች ሲሆን፡ ከሰዓት በኋላ ደግሞ ከሰውየው ጋር ተኛች። ስለዚህ ሰውዬው የራሱን ያሳድጋል… ነጩ ሰውዬ የራሱን ልጅ ያሳድጋል፡ ጥቁሩ ሰውዬም የራሱን ልጅ ማሳደግ እንዳለበት ተነጋገሩ። አያችሁ? ውሾች እና ሌሎች በሚራቡ ጊዜ፡ በጥቂት ሰዓታት ልዩነት ከሆነ፡ እንዲህ ያለ ክስተት፡ በእርግጠኝነት እንደሚሆን አውቃለሁ። ይህም ማረጋገጫው ነው።

87 አሁን ሥልጣኔ ከየት እንደመጣ ለማሳየት፡ ዘፍጥረትን ደግመን እናንብብ፡ ዘፍጥረት ምዕራፍ 4ን፡ እንመልከት። 16ተኛ ቁጥር።

**ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፡ ከዔድንም ወደ ምሥራቅ፡** በኖድ ምድር ተቀመጠ።

**ቃየንም ሚስቱን አወቀ፣ ፀነሰችም፡ ሄኖሕንም ወለደች። ከተማም ሠራ፡ የከተማይቱንም ስም፡ በ… በልጁ ስም፡ ሄኖሕ አላት።**

88 ሰልጣኔ ተጀመረ። ዶክተር ስኮፊልድ፡ እዚህ በስኮፊልድ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ፡ “የመጀመሪያው ሥልጣኔ ነው፡” ይላል። አስተውሉ፡ ከዚያም ወንዶች ልጆችን ወለደ፡ እነሱም ኦርጋንና ሙዚቃን ሠሩ። ሁለተኛው ደግሞ ወንዶች ልጆችን ወለደ፡ ሌሎችንም ድንቅ ነገሮችን፡ ማከናወን ጀመረ፡ ከተሞችን ገነባ፡ የ—የነሐስ መሣሪያዎችንም ሠራ፡ እንዲሁም የተለያዩ ነገሮችን አደረገ። አያችህ፡ ያንን ነው ያደረገው፡ ያ የመጀመሪያው ሥልጣኔ ሆነ፡ ይህም የቃየን-ሰልጣኔ ነው። ባለፋት ዘመናትም ተመሳሳይ ነገር አድርጓል።

89 አሁን ወደ 25ኛው ጥቅስ እንግባና፡ ቀጣዩ ምን እንደሆነ እንመልከት።

**አዳም ደግሞ ሚስቱን አወቀ፡** አሁን፡ **ወንድ ልጅንም ወለደች፡ ስሙንም ሴት አለችው፡ ቃየን በገደለው በአቤል** ፋንታ፡ **እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው።**

ለ… **ለሴት ደግሞ፡ ወንድ ልጅ ተወለደለት፣ ስሙንም ሄኖስ አለው፡** በዚያን **ጊዜም በእግዚአብሔር ስም መጠራት ተጀመረ** (ከሴቴ ወገን እንጂ፡ ከቃየን ወገን አይደለም)።

90 አያችሁ፡ ያ ሁላችንም የሚንጣበቅበት ጥበብን! በዛሬው ጊዜ ኮሙኒዝም ምንድን ነው፡ አምላካቸው ማነው? ይህ የአዕምሮ፡ ሳይንስ ነው። ለማንኛውም፡ ምን እየሠራን ነው? የት ነው የምንኖረው? ዛሬ እነዚህን ቃላት ተመልከቱ።

91 አሁን የራሱ የሆነ የኤደን ገነት አለው፡ ሰይጣን አሁን አለው። በእነዚህ ስድስት ሺህ ዓመታት ውስጥ፡ አመቻቸ (እንጂ አልፈጠረም)፡ የእግዚአብሔርን ምድርን በሙላት ግን፡ አወላገዳት፡ ፍጥረትን፡ እንስሳትን፡ ዝርያዎችን፡ የተዳቀሉትን፣ ዛፎችን፡ እፅዋትን፡ ሰውን፣ ሃይማኖትን፡ መጽሐፍ ቅዱስን፡ ቤተ ክርስቲያንን ሳይቀር እንኳ አዛባ፣ በሳይንስ፡ በሳይንስ በሚንቀሳቀስ ነገር ሁሉ፡ ሙሉ በሙሉ የኤደን የአትክልት ስፍራ እስክቆጣጠር ድረስ ሁሉንም ነገር አዛባ። መኪኖቻችን፡ ያለን ነገር ሁሉ፡ ሰው የሰራው ነገር ሁሉ፡ በሳይንስ የተሰጠን ነው። መልዕክቱ ወቅታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ፡ ራእይ 10 እንጂ ሌላ ዘመን አለመሆኑን ለማረጋገጥ፡ ታላቁን የኤደን ገነት እዚህ አኖረ! በዛሬው ጊዜ የሚከናወነውን የዘር ማባዛት ሂደት ተመልከቱ፡ የተሻሉ፡ ወይም፡ ቆንጆዎች እንዲሆኑ እንጂ፡ የተሻሉ እንዲሆኑ አይደለም። ዛሬ ትናንሽ ልጆችን ተመልከቱ።

92 ትናንት፡ ሴት ልጄን ወደ ጥርስ ሐኪም ወሰጄ ነበር፡ ዶክተሩም ጥርሷ ወጣ እያለ እንደሆነ ነገረኝ። በቱክሰን የሚኖር ወንድም፡ ወንድም ኖርማን፡ ትንሽ ሴት ልጅ ነበረችው፡ ጥርሰዋም ከነበረበት ወጣ እያለ ነበር። የጥርስ ሐኪሙ እንዳለው በቅርቡ፡ ምናልባትም፡ ወደፊት፡ ሰዎች እስከነ ጥርሳቸው፡ ሳይወለዱ አይቀሩም ብሏል። ይህን የሚያደርገው የምንበላው ምግብ ነው፡ የተዳቀለ ምግብ።

93 ባለፈው ወር፡ ስለ ኖበል ወንጌላዊ፡ ስለ ቢሊ ግራሃም፡ **በሪደሪስ ዳይጀስት** መጽሄት የተጻፈውን አንብባችኋል? እሱን እየሰማችሁ ነበር? ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አሁን ስለ እሱ እጸልያለሁ። ባለፈው ምሽት፡ ኮሌታቸውን- አዙረው በለበሱና፡ በሌሎች፡ ቀሳውስቶች ላይ በቀጥታ ተናገረ። የሆነ ነገር ደርሶበታል። ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ አሁን ያለበትን አቋም ይመለከታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡ አስተውሉ፡ አሁን እሱ ከሶዶም፡ ከዚያ ጠማማ ከተማ እየተጣራ ነው። አሁንም ይህንን **በሪደርስ ዳይጀስት** አስተውሉ፡ ቢሊ በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሣ ስብሰባዎቹን እንኳን ማድረግ አልቻለም። እንዲሁም መሮጥ፡ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግና፡ የመሳሰሉት ነገሮች ማድረግ እንዳለበት ነግረውታል። እኔ እንደማምነው፡ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለማድረግ፡ በየቀኑ አንድ ማይል ወይም እንደዛ፡ ይሮጣል።

94 ሰው በሰብሷል። የሰው ዘር በሙሉ ተበላሽቷል። ሁሉም ነገር በጥፋት ውኃው ዘመን እንደነበረው ነው። ሙሉ ለሙሉ የተዘበራረቀ፡ የተገላቢጦሽ፡ እግዚአብሔር ካስቀመጠላቸው ቀጥተኛ ረድፍ የተለየ ሆኗል። ሃጥያት፡ በሳይንስና በማታለል አማካኝነት፡ ኃጢአት መላውን የሰው ዘር አጣምሞታል።

95 በዚያ ጽሁፍ በታች በኩል፡ እንዲህ ሲል አንብባችኋል፡ "በአሁኑ ጊዜ፡ ትናንሽ ልጃገረዶችና ወንዶች ልጆች በአካላዊ አወቃቀራቸው፡ መካከለኛ ዕድሜ ውስጥ እንዳሉ ሆነዋል፡ በእድሜ በሀያ እና ሃያ-አምስት ዓመት መካከል ያሉት"? አስቡት።

96 ባለፈው ምሽት በመለየት ጸጋ፡ የሀያ-ሁለት ዓመት ዕድሜ ላይ ያለች ሴት፡ በወር አበባ ማቋረጥ ወቅት እንዳለች አየኋትና፡ ጠራኋት። ዶክተሯም የነገራት ይህንኑ ነበር።

97 አያችሁ፡ የወደቀ፡ የተበላሸ፡ በገሃነም-የታሰረ የተበላሸ ዘር ነው። ይህ ሥነ ምግባር የጐደለው እንደሚመስል አውቃለሁ፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡

እያችሁ፡ እውነት ነው፣ ይህ የምንኖርበት ዘር፡ ይህ የሰዎች ትውልድ የተበላሸ ዘር ነው።

98 አሁን በዛሬው ጊዜ፡ ከብቶችንና፡ እፅዋትን ማዳቀልን ልብ በሉ፡ ሳይንስ ወዲያውኑ ወደ ኋላ ይመለስና፡ ይህን የሚያደርገው ተመሳሳይ ሳይንስ፡ እንዲህ ይላል፡ "ይህ ነው መላውን የሰው ዘር የሚያጠፋው።" እኔ እንደማነበው እናንተም ታነባላችሁ። ደኅና፡ ለምን አያቆሙትም? ምክንያቱም ሊያቆሙት ስለማይችሉ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንደዚህ እንደሚሆን ተናግሯል። ነገር ግን ለአንድ ደቂቃ ቢያስቡት፡ እንደ አስቆርቱ ይሁዳ፡ መጠቀሚያዎች ናቸው፡ እግዚአብሔር እንደሚሆን የተናገረውን ነገር በትክክል በማስቀመጥ መሣሪያዎች ናቸው። ይህን የሚያደርጉት በራሳቸው ሳይንስ ላይ ተመስርተው ነው።

99 በሳይንሳዊ ጥናቱ፡ ሔዋንን እንዳታለላት ሁሉ፡ ቤተ ክርስቲያንንም አታለላት፡ ሄዋንም የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነበረች። አሁን፡ አዳም እንደገና ምሳሌ ነው፡ ወይም ይበልጥ፡ ሔዋን፡ ለቤተክርስቲያን ምሳሌ ነች፡ አሁን ዲያብሎስ ምን እንዳደረገ ልብ በሉ። እውቀትን ለማግኘት በምታደርገው መንከራተት፡ ከትክክልኛው ከእግዚአብሔር ቃል ወጥታ፡ የተጣመመውን ወይም የተበላሸውን፡ የሰይጣንን ቃል በመስማት፡ በመልካም እና በክፉ መካከል በመሃል ሆናለች።

100 በዛሬው ጊዜ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የተዛቡ ሆነዋል። አሁን እየተናገርኩ ያለሁት ስለ ግለሰቦች፡ ስለ ሰዎች አይደለም። የምናገረው ስለ ቤተክርስቲያኑ ዓለም ነው። አንዱ በአንድ መንገድ የተዛባ ነው፡ ሌላኛው ደግሞ በሌላ መንገድ የተዛባ ነው፡ እና፡ የተዛባው በሳይንስ ነው። እርሱ እንዳደረገው ተመሳሳይ ንድፍ ነው። በኢሳይያስ 14:12 ላይ ያለውን፡ ዛቻውን ሰይጣን፡ ፈጽሟል።

101 እስቲ ለአንድ ደቂቃ እናንብበው። በኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ፡ 14ኛውን ምዕራፍ፡ 12ኛውን ቍጥር እንጀምር።

> **አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ፡ ኦ ሊሲፈር ሆይ፡ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም** ያዋረድህ **አንተ ሆይ፡ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ!**

ይህ ኢሳይያስ ወደፊት በሚመጣው ዘመን፡ በራእይ ሲያየው ነው፡ እያችሁ።

> **አንተን በልብህ፡ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፡ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፡ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ፡... እቀመጣለሁ፡**

102 የሰይጣን ዓላማ፡ ከዔደን ጀምሮ፡ የራሱ የኤደን ገነት ማድረግና፣ ራሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ነበር፡ ይህም የእግዚአብሔር ከዋክብት እንዲያመልኩት፡ ልጆችም እንዲያመልኩት ነው። ይህንንም ሲያደርግ ወደ ቤተክርስቲያንም በማምጣቱ፡ አሁን ሙሉ በሙሉ ተከናውኖለታል። ይህም፡ በዝርዝር አልናገርም። ነገር ግን ቴፕ የሚያዳምጡ ሁሉ ያውቁታል። የ—የምንኖረው በዚህ ዘመን ውስጥ ነው፡ በትምህርታዊ ፕሮግራም አማካኝነት ይህን ያደረገው ሰይጣን ነው፡ የተሻለ ተስማሚ፡ የተሻለ **ይህ**፡ የተሻለ **ያ**። ሳያውቁ፡ ሁል ጊዜ፡ በቀጥታ ወደ ሞት እየሄዱ ናቸው። ዕውሮች፡ ዕውራንን የሚመሩ፡ ዕውር የአሕዛብ መሪዎች፡ ዕውር የሳይንስ መሪዎች፡ ዕውር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፡ ዕውራንን የሚመሩ

ዕውሮች ናቸው። ኢየሱስም፡ “ተዉአቸው፡ ሁለቱም ወደ ጕድጓድ ይወድቃሉ” አላቸው።

103 እዚህ ላይ የሁለቱ የኤደን ገነቶች ተምሣሌት እርስ በርስ በጣም ተቀራራቢ በመሆናቸው፡ ቢችሉ የተመረጡትን ሊያታልሉ እንደሚችሉ ልብ በሉ። ማቴዎስ 24፡24 እንዲህ እንደሚሆን ይናገራል። ነገር ግን ለጥቂት ጊዜ ቆም ብለን እነዚህን ሁለት ዔደን ገነቶችንና፡ በተለይ አንድ ነገርን እንመልከት፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ያንን ዔደን ገነት እንደፈጠረ እንዴት እንደሚነግረንና፡ የእግዚአብሔር ቃል ሌላኛው ዔደን እንደሚመጣ እንዴት እንደሚያስጠነቅቀን እንድናስብ እፈልጋለሁ።

104 አሁን፡ ደግሞ ሌላ የኤደን ገነት መኖሩን እናውቃለን፡ ነቢዩን፡ ጳውሎስን፡ በ2ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 2 ላይ የተናገረውን ብንሰማ ሌላ የኤደን ገነት መኖሩን እናውቃለን። ከፈለጋችሁ ማንበብ እችላለሁ።

> እራሱን ከፍ ከፍ እያደረገ፥ **የዓመጽ ልጅ እስኪገለጥ ድረስ፡** ያቺ **ቀን** ከጌታ ዘንድ፡ **አትመጣም፡...**

> ... አምላክ ከተባለው ሁሉ፡ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ **ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው፡** ተቃዋሚ እርሱ ነው።

105 እስቲ አስቡት! ነቢዩ በኢሳይያስ 14፡ ያየውን ተናገረ “ሉሲፈር፡ ልቡን፡” እግዚአብሔር፡ “ይህን ያደርጋል በማለት” በመንፈስ ምሪት ባሳየው ራእይ አማካኝነት ተናግሯል። በኢሳይያስ፡ ከጳውሎስ ከስምንት መቶ ዓመታት፡ ወይም ከዛ አከባቢ በፊት ነበር ያየው።

106 አሁን እዚህ፡ ከስምንት መቶ ዓመታት በኋላ፡ ጳውሎስ፡ ወደ ስፍራው መምጣቱን ተመለከተ ልብ በሉ፡ ቀጥሏል፡ የእርሱ ገነት፡ የእርሱ ሳይንሳዊ ገነት፣ ከሳይንሳዊው ዓለም ጋር፡ ከሳይንሳዊ ሙሽራ-ቤተክርስቲያን ጋር፡ ሁ—ሁሉም “በእውቀት” ቃል ሥር፡ ታላላቅ ሴሚናሮችን፡ ታላላቅ ዲግሪዎች፡ የትምህርት ፕሮግራሞችን ይዘው ቀጥለዋል።

107 አዳምጡ፡ ወንድሜ፡ እኅቴ፡ እያንዳንዳችን ፍሎረንስ የሔደችበትን መንገድ እንከተላለን። በኢየሱስ ስም፡ ይህን እንድታስቡ፡ እጠይቃችኋለሁ። እኔን አታስቡኝ። እኔ ወንድማችሁ ነኝ። ይ—ይህ አይደለም። የሚናገረውን የእግዚአብሄር ቃል የሆነውን፡ መጽሐፍ ቅዱስን ተመልከቱ። እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ፍጹም በሆነ መንገድ ያጸደቀውን፡ የምንኖርበትን ዘመን፡ የምንገኝበትን ቦታ፡ ተመልከቱ።

108 እነዚህ ፕሮግራሞች በራሳቸው፡ ፍፁም የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ናቸው። አሁን፡ ኤደን ሊኖረው ይገባል፡ አደርገዋለሁ ብሏልና። እዚህ ላይ ቀላል የእግዚአብሔር ቃል እርሱ እንደሚያደርገው ይናገራል፡ እዚህም ወደ ውጭ እንመለከታለንና እርሱ ሲያደርግ እናያለን። ምሁራዊ፡ ሳይንሳዊና፡ ሃይማኖተኛ ከሆነች ሙሽሪት ጋር ጨርሷል። አንድ ቀን የሚቋቋመውን፡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤትን፡ ይመራል። ሁሉም ከእርሱ ጋር ይሆናሉ።

109 ሰዎቹን ይፈትናቸዋል፡ እነሱ መጥፎ ሰዎች ስለሆኑ አይደለም፡ አተካከላቸው እንደ በቆሎ፡ በመደዳ መስመራቸውን የጠበቁ ነበሩ፡ ነገር ግን ሰይጣን ሳይንስ፡ ምርምር፡ ትምህርት፡ የዶክተሮች ዲግሪዎች፡ ተብለው

የሚጠሩትን አረሳችን ዘራ። አንዳንድ ጊዜ ከሆነ ሴሚናሪ የዶክትሬት ዲግሪ ማቅረብ ካልቻላችሁ በስተቀር ወደ መድረክ እንኳን አይፈቅዱላችሁም። ሁሉም ስሕተት ነው! ሰዎች አይደሉም፣ ስሕተት የሆነው ፕሮግራሙ ነው። አሁንም ምን አደረገ? ይህ ሁሉ እንደገና ወደ ላይ ተነሥቶ፡ መላውን ዓለም (በብዙ ማዳቀል፡ የእግዚአብሔርን ትክክለኛውን ዘር በማጣመም) ወደ ሌላ ወደ ጨለማ ትርምስ አመጣው።

110 ነገር ግን እግዚአብሔር ዳግመኛ ሰለ እኛ ግድ ስለሚለው በጣም ደስ ብሎኛል፡ አሁንም ቢሆን በሁኔታው ላይ መንቀሳቀስ ይችላል። ይህን እንደሚያደርግና ሙሽራው የምትሆነውን ታናሽ መንጋ፡ እንደሚጠራ ቃል ገብቷል።

111 እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት፡ ወይም እነዚህ ኤደኖች፡ ምን ያህል ፍጹማን እንደሆኑ ተመልከቱ።

112 እግዚአብሔር፡ በቃሉ ዘር አማካኝነት! ቃሉን ሕያው ሊያደርገው የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ምክንያቱም የቃሉን ሕይወት-ሰጪ እሱ ነው። በቃል ውስጥ ያለው ሕይወት ከመንፈስ ሕይወት ጋር ሲገናኝ፡ ዘሩ ምንም ይሁን ምን ያፈራል።

113 አሁን ምን እንደሆነ ልብ በሉ። በኤደን የአትክልት ስፍራ የእግዚአብሔር የጽድቅ ሰርአት ነበር፡ ያም ከ—ከሰርዓቶቹ አንዱ ነበር። የመጀመሪያው ሥርዓት ንጹሕ ነበር፡ ሰዎች ኃጢአት አያውቁም ነበር። ሰለ ኃጢአት ምንም አያውቁም ነበር። አዳምና ሔዋን ሁለቱም እርቃናቸውን ነበሩ፡ ነገር ግን ከእርቃናቸውን የተደበቁ ነበሩ፡ በመንፈስ መሸፈኛ ፊታቸውን ሸፍነው ነበር። እርቃን መሆናቸውን፡ በጭራሽ አያውቁም፡ ምክንያቱም ተደብቀዋል። ምክንያቱም፡ መልካሙንና ክፉ የሆነውን ነገር የማያውቁ በመሆናቸው፡ በአዕምሯቸው ላይ የእግዚአብሔር መጋረጃ ነበር። ሁለቱም በዚያ እርቃናቸውን መቆማቸው፡ እውቀቱ ገና እንዳልመጣላቸው ያሳያል፡ አያችሁ፡ እርቃናቸውን ነበሩ። ጥንዶቹ እርቃናቸውን ነበሩ እና አያውቁም ነበር።

114 አሁን የሚትከፍቱ ከሆነ፡ ከፈለጋችሁ፡ ራእይ፡ ምዕራፍ 3ን፡ አንብቡ ወይም ጻፉ። መንፈስ ቅዱስ ይህን የመጨረሻ ዘመን ሲተነብይ፡ ለሎዶቅያ የጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን ዘመን በመጨረሻው ዘመን፡ እንዲህ ብሏል፡ "እራቁት፡ እና ዕውር ነህ፡ አታውቀውምም።"

115 በቅንነት ሰር፡ እራቁታም መሆናቸውን ሳያውቁ፡ በመንፈስ ቅዱስ መጋረጃ ሥር፡ ከኃጢአት የተሸፈኑ፡ የእግዚአብሔር ዘር ይህ ነው።

116 አሁንም በመጨረሻው የቤተክርስቲያን ዘመን ውስጥ፡ እንደገና እርቃናቸውን ሆነው እዚህ እናገኛለን፡ አያውቁምም። ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ መጋረጃ አይደለም። ሰይጣን በሔዋን ላይ የጣለው መጋረጃ ነው፡ የፍትወት መጋረጃ፡ የፍትወት መጋረጃ ነው። እነሱ እርቃናቸውን መሆናቸውን እንኳን እስከማያውቁ በጣም ረከሱ፡ ሴቶቻችን በጐዳና ላይ፡ በአጫጭር ቁምጣዎች፡ ወሲብ በሚቀሰቅስ አለባበስ ይዞራሉ።

117 አንድ ሰው አንድ ቀን፡ በጋዜጣ ሊለብሱት ያሉትን አዲሱን ቀሚሳቸውን ላክልኝ፡ ከትከሻ አሥራ አራት ኢንች፡ ወይም እንደዛ ነገር ነው፡ ብዬ

አስባለሁ። ሴቶቻችን ይህ የ—የፍትወት መጋረጃ መሆኑን ቢገነዘቡ ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ?

118 እናንተም—እንዲህ ትላላችሁ፡ “እኔ በእግዚአብሄር ፊት፡ ለባለቤቴ፡ ከምንም አይነት ምንዝርና ንጹህ መሆኔን፡ ማ—ማረጋገጥ እ... እችላለሁ።”

119 ሆኖም ግን አሁንም፡ በፍርድ ቀን፡ “አመንዝራ” ተብለሽ ትጠሪያለሽ። መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራልና። ኢየሱስም፡ “አንዲትን ሴት በፍትወት ስሜት የሚመለከት ሁሉ፡ በዚያን ጊዜ በልቡ ከእሷ ጋር አመንዝሯል” ብሏል።

120 “ዕውር፡ እራቁት፡ ይህን ግን አታውቀውም!” ማዶ ላይ ስላሉቱ ምስኪን ሴቶች አይደለም፣ በእነሱ ላይ ምንም ነገር የለኝም። ያን ያህል ክፉት ነው! የቤተክርስቲያን ሥርዓት ግን ይህን መገንዘብ ተሰኖታል፡ ሊቃወመው ያቃተው ይመስላል፣ በክርስትና ስም ፀጉራቸውን እንዲላጩ፡ ሜ-ካፕ እንዲለብሱ፡ አጫጭር ሱሪዎችን እንዲለብሱና ሌሎች ነገሮችን እንዲያደርጉ፡ ይፈቅዳሉ። እንዴት ያለ አስቃቂ ነገር ነው! እያችሁ፡ በሰይጣን ዔደን ውስጥ፡ እንደገና እርቃናቸውን ናቸው፡ አያውቁትምም። አያውቁም።

121 እንደማይ አምናለሁ፡ ምናልባት፡ ከዚህ ማዶ ያለው የመዋኛ ገንዳን፡ አሻግራችሁ ስታዩት፡ አሁን እዚያ ያሉ ሴቶችን። ይህች ሴት፡ አታውቀውም እንጂ ምን እየሠራች እንደሆነ ብትገነዘብ ኖሮ። እርቃኗን ናት። የሴቷ ገላ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር ለዚህ ትውልድ፡ በቆዳ፡ ያለበሳትን ልብስ አውልቃ ትጥላለች። ያለማቋረጥ ታወልቃለች። “በስልጣኔ፡ በከፍተኛ ትምህርት፡ በተሻለ ሥልጣኔ፡ በከፍተኛ ሥነ ምግባር” በሚሉት ቃላት ሥር፡ ተራቁታለች። ይህን እንደምትረዱት እርግጠኛ ልሁን። ይህ ሁሉ የዲያብሎስ ነው፡ ሁሉም በጌታ በኢየሱስ መምጣት ይጠፋል። ሁሉም ነገር፡ ይደመሰሳል። ምንም ነገር አይተርፍም።

122 እና፡ ኦህ፡ ወዳጄ፡ በመላ አገሪቱ፡ እዚህ በፊኒክስ እያዳመጣችሁኝ ሳለ፡ እነዚህን ነገሮች አስቡ! በእነርሱ ስር ናችሁ። አሁን፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ “ብቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስታሉ።”

123 የ... የመጀመሪያው መጋረጃ ቅዱስ መጋረጃ ነበር፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እሷም ከዚያ ውጭ ማየት አልነበረባትም። ይሁን እንጂ—ሰይጣን ግን ስለ እውቀት ሊነግራት በጀመረ ጊዜ ግን፡ አለምን አጮልቃ ማየት ጀመረች።

124 ቤተ ክርስቲያኗም፡ ልጇ ያደረገችው፡ ይህንኑ ነው። ማየት አለባችሁ፡ እንደ አንዳንድ ፊልም ተዋንያን መልበስ አለባችሁ፡ ወይም ወጣት ወንዶች እንደ ኤልቪስ ፕሪስሊ ወ—ወይም እንደ ፓት ቡን፡ ወ—ወይም በሃይማኖት ስም፡ እንደ አንዳንድ ሰዎች መሆን አለባችሁ።

125 ፓት ቡን ቼርች ኦቭ ክራይስት እምነት ተከታይ ነው። ኤልቪስ ፕሪስሊ የጴንጤቆስጤ እምነት ተከታይ ነው። ከኢየሱስ ክርስቶስ ክሕደት ጋር በተያያዘ ከአስቆሮቱ ይሁዳ በከፋ ክህደት ዓለምን ወደከፋ ትርምስ ወስጥ የከተቱ ሁለት አጋንንታዊ ገጸ ባህሪያት ናቸው። ይህን አያውቁም። እነዚህ ልጆች ይህን አያውቁም። እነዚያ ወ—ወንዶች፡ ሰዎቹን አልቃወማቸውም፡ እኔ የምቃወመው የሚገፋፋቸው መንፈስን ነው።

126 ትንሽ አንድ እርምጃ እንድወስድ ካደረጋችሁ፡ ይህ አረግ አንድ ጊዜ፡ የቦቆሎውን ቅርንጫፍ ከያዘ፡ ምን እንደምፈጠር ተመልከቱ፣ በቆሎው ይጠፋል። ኦህ፡ አዎ፡ ይይዘዋል። ይህን የሚያደርገው በዚህ መንገድ ነው። ሁልጊዜ ያደርገዋል። ሔዋን ወደ ዓለም አንድ እይታ ብቻ መመልከት ነበረባት።

127 ወንድሜ እና እኅቴ፡ አንድ ነገር ልንገራችሁ። በ1ኛ ዮሐንስ፡ ምዕራፍ 2 ቊጥር 15 ላይ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ ከፈለጋችሁ እናነበዋለን፡

> ... **ዓለምን**፡ ወይም በዓለም ያሉትን ነገሮች **የምንወድ ከሆነ፡ የ**እግዚአብሔር **ፍቅር በ**ውስጣችን **ስለሌለ** ነው።

128 አሁን፡ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ቃል **ምድር** አይደለም፣ የግሪክ ቃል ነው፡ **ኮስሞስ**፡ ትርጒሙም “የዓለም ሥርዓት” ማለት ነው። የምድርን፡ የዓለምን ፋሽን የምንወድ ከሆነ፡ የዘመኑን ሁኔታ የምንወድ ከሆነ፡ “ይህ አስደናቂ ዘመን ነው፡ ኦህ፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች አሉን” ብለን የምናስብ ከሆነ፡ ይህን ካሰባችሁ፡ ይህ የሆነበት ምክንያት እስተሳስባችሁ የተሳሳተ ስለሆነ ነው። በዲያብሎስ ተዛብቷል። “ምክንያቱም ዓለምን ስርዓትና፡ በዚህ ዓለም ውስጥ ያሉትን ነገሮች የምትወዱ ከሆነ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችሁ ስለሌለ ነው።” ይህን አስታውሱ። ኦህ እግዚአብሔር ሆይ! ወደ ምን እየተመለከትን እንደሆነ ተመልከት!

129 እዚህ ላይ ለአንድ ደቂቃ ቆም ብዬ ትንሽ ታሪክ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት የሆነ አንድ ቄስ ሰማሁት። እና ረጭተውባቸው ስለነበረ...

130 ልክ ሰይጣን መጀመሪያ እንዳደረገው፡ ወደ ዔደን የአትክልት ስፍራ ሲመጣ እንደሰራው። እርሱ ዘሮቹን ቆፍሮ ማውጣትም አልቻለም። ሊያጠፋቸው አልቻለም። ነገር ግን መርዝ ረጨባቸው፡ ዘሩንም አበላሸው፡ ትክክለኛውን የራሱን አይነት ፍሬ አላፈራም። የመጀመሪያውን ዘር አበላሽቶታል።

131 እነዚህ ሁሉ የሃይማኖት ፕሮግራሞች እንደዛ ናቸው። እነሱ አሁንም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናቸው፡ ግን እየተዛቡ ነው። ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱት፡ ትክክል የሆነውን ነገር ለማድረግ ስለሚፈልጉ ነው። አንዲት መነኩሴ መጥሮ ሴት ለመሆን ወደ ገዳም አትገባም። አንድ አገልጋይ መጥሮ ሰው ለመሆን ሲል ትምህርት ቤት አ—አ—አይገባምና። መቼም ቢሆን መጥሮ ሰው ለመሆን ስትል፡ ወደ ቤተክርስቲያን አትቀላቀልም፡ እጅ አትጨብጥም፡ ወይም በቤተክርስቲያንህ ውስጥ የምታደርገው፡ ስምህን በመዝገብ ላይ አታሰቀምጥ። ጥሩ ሰው ለመሆን ይህን ታደርጋለህ። ይህ ግን መታለል ነው፡ ይህን የሚያደርገው ጠማማነት ነው። ሰይጣን የረጨው ነገር ነው። እያችሁ? እግዚአብሔር መቼም ቢሆን ድርጅት አልነበረውም። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንዲህ ያለ ነገር በየትኛውም ቦታ አይገኝም።

132 እግዚአብሔር ድርጅታችን ነው፡ እኛም በእርሱ አንድ አካል ሆነን፡ በሰማይ፡ በእግዚአብሔር፡ ተደራጅተናል። በትክክል። ስማችን በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ተመዝግቧል። አስተውሉ።

133 ነርገር ግን፡ እያችሁ፡ በጣም ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፡ ነገር ግን ከ— ከቻላችሁ ትንሽ እንድትታገሱኝ እፈልጋለሁ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት... ከርዕሴ ስለወጣሁ ይቅርታ አድርግሉኝ።

134 ነገር ግን ይህንን ነጥብ ለማጉላት፡ ሰይጣን በኤደን ምን እንዳደረገ ትንታኔ ልሰጣችሁ እ—እፈልጋለሁ፦ አስቃቂ የሆነ መርዝ ረጨ። ያ የተረጨው ነገር ምን እንደሆነ ማወቅ ትፈልጋላችሁ? ልነግራችሁ እችላለሁ። ቀመሩን አግኝቻያለሁ፡ ሁለት ቃላት ናቸው፡ አለማመን፡ ይህም ከእምነት ተቃራኒ ነው፡ አለማመንን፡ ጥርጣሬ። ሳይንስም ቦታውን ሞላ። ወደ ዘሩ የገባውን ክፍተት፡ ሰይጣን ያንን ቀዳዳ፡ በእውቀት በሳይንስና በሰልጣኔ ሞልቶ፡ መላውን የእግዚአብሔርን ፍጥረት፡ አዛብቶታል።

135 ወደ መጥፎ ሁነታ እንዳስገቧሃችሁ እንደምታስቡ አውቃለሁ፡ ነገር ግን እኔም ከእናንተ ጋር በዚያ ሁነታ ውስጥ ነኝ። ሁላችንም ምን ማድረግ እንደምንችል ለመሞከር እዚህ ተገኝተናል። እነዚህ ነገሮች የሚነናገረው የተለይን ለመሆን አይደለም። ሐቀኞች መሆን አለብን።

136 እኛ፡ እያንዳንዳችን፡ ለእያንዳንዱ ቃል መልስ ወደምንሰጥበት፡ ወደ መንገዱ መጨረሻ ደርሰናል። አሁን፡ ድምፃችን... በተወለድን ቀን፡ የጮኽናት የመጀመሪያ ጩኸታችን እንኳ ሳትቀር በቴፕ ተመዝግባለች። ያ የተቀዳው በፍርድ ቀን ወደ ኋላ በድጋሜ ይጫወታል። የምትለብሱት ልብስ እንኳ፡ በፍርድ ቀን በፊታችሁ ላይ ይታያል። ሳይንስ እንኳን በቴሌቪዥን አማካኝነት፡ ያንን ሰርቷል። ቴሌቪዥን ምስልን አይፈጥርም፡ ከዚህ በፊት የተቀዳውን ያሰራጫል እንጂ፡ የልብሳችሁ ቀለም፡ በእያንዳንዷ እንቅስቃሴያችሁ፡ በአዕምሯችሁ ውስጥ ያለው እያንዳንዷ ሃሳብ፡ በእርግጠኝነት በእግዚአብሔር መዝገብ ውስጥ ይቀመጣል። ያ ትልቅ ነገር በቀጥታ በፊትሽ ላይ ይቀመጣል፡ እያንዳንዱ የለበሽው ቆሻሻ ልብስ፣ ወደ ጸጉር ቤት በሄድሽ ቁጥር፡ እግዚአብሔር የሰጠሽን ጸጉር ትቆርጫለሽ። እንዲህም ይሆናል። አንቺም መልስ ትሰጪበታለሽ። እዚያ አንድ እርምጃ መንቀሳቀስ አትችሉም፡ ይህን ስታደርጉ የልባችሁ ሃሳብ ሁሉ፡ በቀጥታ በፊታችሁ ይታያል። እንዴት ታመልጣላችሁ? “እንግዲህ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንል እንዴት እናመልጣለን?” አያችሁ? አናመልጥም። እያንዳንዱ እንቅስቃሴና፡ የልብ ሃሳብ፡ በሌላ ዳይመንሽን ውስጥ በትክክል ይመዘገባል፡ የምትለብሱት ልብስ ቀለም እንኳን ሳይቀር። ቴሌቪዥን፡ ቀለማትን የሚያሳየው ቴሌቪዥን ያንን በትክክል ያረጋግጣል፡ ያወጣና ያሳያል፡ አያችሁ፡ ያ እኛ ከምንኖርባቸው ሦስት ዳይመንሽኖች ውስጥ በአንድ ዳይመንሽን ውስጥ ብቻ ነው። አያችሁ?

137 አሁን ደግሞ መርዙ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት እንደመታ፡ ምድርንም እንዴት እንደመታ! የሰይጣን መርዝ በዘሩ ላይ፡ ክፍተትን አደረገና እንዲዛባ አደረገ። ከጊዜ ወደ ጊዜ፡ እየጠለቀ ወደ ቤተክርስቲያኖች ልብ፡ ወደ ሰዎች ልብና ወደ ሁሉም ነገር፡ ወደ ሳይንስ፡ ወደ ሳይንስ ውስጥ ገባ። የሰው ዘር ሁሉ አንዱ ከአንዱ ጋር፡ በመዳቀል... እያንዳንዱ ዘር የራሱን ፍሬ ዓይነት ማፍራት አለበት ብዬ አምናለሁ። የሰው ዘር፡ እፅዋትና፡ ሁሉም የተዳቀሉ በመሆናቸው፡ ወደ አንድ ቦታ አምጥቶናል፥ ምግብን ከምድር መመገባችን፡ ይህ፡ ሰውነታችን፡ የተዳቀለ እንዲሆን አድርጎታል፡ መላ አእምሮአችንን... አሁን፡ ሰውነታችን ከሀያ እስከ ሀያ-አምስት ዓመት ዕድሜ ውስጥ፡ እያሽቆለቆለ ከሄደ፡ በተበላሹ ሴሎች ምክንያት ነው፡ በተዳቀሉ ምግቦች ምክንያት ነው፡ የአንጎላችን ሴሎች አይበላሹም? ሴሎችም፡ አይደሉምን? ለዚህም ነው ወጣቶች እዚህ አውራ ጐዳና ላይ፡ በመክና የሚሮጡት፣ ስማቸውን እንዲህ ብለን እንደምንጠራቸው፡

ሴቶች፡ ቀበጦች፡ ብዙዎቹ፡ እዚህ ግማሽ እርቃናቸውን ሆነው በሕዝቡ ፊት ይሄዳሉ፡ አእምሮአቸውን አጥተዋል፡ የሥነ ምግባር ወይም የሥነ ምግባር እሳቤ የሌላቸው።

138 ወደ ትንሿ ታሪኬ እንመለስ። ይህ ቄስ ሆስፒታል ውስጥ እንደነበረና፡ በጣም ብዙ ልጆች ድንኳን ውስጥ ነበሩ አለ፡ እ... እርሱ ከውጭ ነበር የመጣው። ወደዚያ እንደወጣ ተናገረና፡ አንድ የቢሮ ሰራተኛ ነገረው፡ እንዲህ አለው፡ "ቄስ፡ ወደ ውጭ ወጥተን፡ ሜዳዎቹን መጎብኘት እንፈልጋለን" አለ። በዚያ ዘመን እንዳደረጉት፡ ይህን ሰናፍጭ እና ክየሎሪን ጋዝ ረጭተውባቸው ነበር።

139 እንዲህም አለ፡ "ወደዚያም ወጥቼ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡" እንዲህ አለ፡ "በዛፉ ላይ አንድም ቅርፊት አልነበረም፡ አንድም ሳር አልነበረም። የፋሲካ ቀን ጠዋት ነበር።" እንዲህ አለ፡ "እዚያ ታች አንዳንድ የቆዩ የተበላሹ ታንኮች ነበሩ፡ የቢሮ ሰራተኛው ይመዘግባቸው ነበር፡ እንዲሁም በታላቁ የአርጎን ጫካ አቅራቢያ፡ እነርሱን ማስተካከል የሚቻል እንደሆነ ለማየት ሄደ።" እንዲህ አለ፡ "በዚያ ብቻዬን ቆሜ ሳለሁ፡" እንዲህ አለ፡ "ወደ ላይ ተመለከትኩና፡ እንዲህ አልኩ፡ 'አምላኬ ሆይ፡ ሁሉም ነገር እንዲህ ሊሆን ነውን።"' ያ ትክክል ነው፡ ሁሉም እንዲህ ሆኗል። ሁሉም ተቃጥሏል፡ በየትኛውም ቦታ ምንም ሕይወት የለውም፡ ሳሮች ተቃጥለዋል፣ ዛፉ፡ በዚያ ጋዞች፡ ዛፎች ተገደለዋል፡ ሁሉም ነገር ተገደለ፡ ጥይቶችና ሌሎች ነገሮች ሲመቷቸው፡ ጠማማ ሆኑ፡ ወደ ታች ተንጠልጥለዋል።

140 ይህ የዛሬው ዓለም ምስል ካልሆነ፡ ይህ ሰይጣን የራሱን አለማመን፡ የራሱን ማዳቀል፡ የራሱን ሳይንስ፡ የራሱን እውቀት የሚረጭበት የዛሬው ዓለም ምስል አይደለምን! እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን፡ በገነት ውስጥ ባስቀመጠበት ጊዜ፡ በመጀመሪያ ምን እንደነበረ ተመልከቱ፡ በዚያ ውብ ገነት ያለ ሞት፡ ያለ ህመም፡ ያለ ሃዘን፡ ሁሉም ነገር በፍጹም ሰርዓት ውስጥ ነበር፡ የሰይጣን ዲዲቲ ምን እንዳደረገ እንደሆነ ተመልከቱ! ትርምሷ ወጣ። በውስጧ ምንም የቀረ ነገር የለም።

141 እንዲህ አለ፡ "ማልቀስ ጀመርኩ። ወደ ኋላ ተመለስኩ፡ ወደ አንድ አለት ተጠጋሁ።" እንዲህ አለ፡ "ወደዚያም ሄጄ ድንጋዩን ተመለከትኩትና፡ ወደ ኋላ ገፋሁት። ከድንጋዩ በታች አንድ ትንሽ ነጭ አበባ እያደገች ነበር፡ የቀረችው ብቸኛዋ ሕያው ነገር እርሷ ነች፡ ምክንያቱም በአልቱ ስር ተጠልላ ነበር።"

142 አምላኬ ሆይ፡ ዓለቴ ሆይ፡ ሸሸገን ዛሬ፡ ኦ አምላኬ ሆይ፡ እነዚህ መርዞች በሳይንስና በትምህርት ስም በየቦታው በሚበሩበት ጊዜ ዛሬ ሸሸገን። ሸሸገን። አምላኬ ሆይ፡ እስከዚያ ቀን ድረስ ጠብቀኝ፡ ይህ ጸሎቴ ነው። አሁን እያንዳንዳችን፡ በዚያ ዓለት፡ በክርስቶስ ሥር ነን ብዬ፡ ተሰፋ አደርጋለሁ።

143 በቀደም ሰብኬ ነበር፡ ብዙዎቻችሁ ሰምታችኋል። አደን ለማደን፡ በጫካ በኩል ታች እየሄድኩ ነበር፡ እና የሆነ ነገር አትኩሮቴን ሳበ። እና ምን ነበር የምትሉት፡ ባዶ የሲጋራ ካርቶን ወይም ጥቅል፡ ወይም የሆነ ነገር አየሁ። የአንድ ኩባንያ ስም አለበት፡ ሰማቸውን መጥራት ያለብኝ አይመስለኝም፡ ነገር ግን የትንባሆ ኩባንያው ነበር... "የሚያስብ ሰው ማጣሪያ፡ የሚያጨስ ሰው ሽታ፡" የሚል መፈክር ነበረው።

144 በጫካ ውስጥ ትንሽ ወ—ወደ ታች መሄድ ጀመርኩና፡ የሆነ ነገር ሳበኝ፡ “ወደዚያ ወደ ሲጋራ ጥቅል ተመለስ።”

145 እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “የሰማይ አባት ሆይ፡ እነዚያን ሽኮኮዎችን አንድ ቀን ጠዋት፡ ወደ መኖር ያመጣሃቸው ወደዚያ ዛፍ እየወረድኩ ነው። ለምን ወደ ኋላ ተመለስ ትለኛለህ? ”

146 የሆነ ነገር እንዲህ አለ፡ “እሁድ መሰበክ ያለብህ ስብከት አለ። የስብከቱ ርዕስ በሲጋራው ካርቶን ላይ ተጽፏል።”

“በሲጋራ ጥቅል ላይ? ” ብዬ አሰብኩና፡ ወደ ኋላ ተመለስኩ።

147 እናም ማሰብ ጀመርኩ፡ “የሚያስብ ሰው ማጣሪያ፡” ምን ዓይነት ማታለያ ነው! አንድ ሰው የሚያስብ ሰው ቢሆን ኖሮ፡ በጭራሽ አያጨስም ነበር። ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ሰዎች ያንን ይውጣሉ።

148 ከሁለት ዓመት በፊት ይመስለኛል፡ በአንዱ ኮንቬንሽን ላይ በነበርኩበት ወቅት፡ የምዕራብ ዳርቻ ላይ በነበረው የንግድ ትርኢት ላይ ነበርኩ። የዩል ብሪነር ፎቶግራፍ እና የብዙዎቹ እዚያ ነበሩ። ብዙዎቹ፡ ሳይንቲስቶችም፡ በተመሳሳይ አዳራሽ ውስጥ፡ ስለ ሲጋራ ማጨስ አደጋ ተነጋግረው ነበር። ያንኑ ጭስ በአንድ ዕብነ በረድ ላይ አድርገው፡ በትንሽ በጀሮ ማጽጃ-ጥጥ ነገር አድርገው ትንሽ ኒኮቲኑን ወስደው ከዚያ አውጥተው በአይጥ ጀርባ ላይ አስቀመጡት፡ ከዚያም አይጡን በጎጆው ውስጥ አስቀመጡት፡ በሰባት ቀናት ውስጥ በካንሰር ተይዞ መራመድ እንኳን አልቻለም። አያችሁ? እንዲህ አለ... በውኃ ውስጥ አወጣውና፡ እንዲህ ይላል፡ “ማጣሪያ!”

149 እንዲህ ይላል፡ “ማጣሪያ? እንደዚህ ያለ ነገር የለም።” እንዲህ ይላሉ፡ “እናንተ... ” አሁን፡ ይህ ሳይንስ ራሱ ነው። እነሱም፡ “ታር ባይኖረው ኖሮ ፈጽማችሁ ባላጨሳችሁ ነበር። ጭሱን የሚፈጥረው ታር ነውና።”

150 ይህ ሁሉ ሲጋራው የሚሸጥበት፡ ማታለያ መንገድ ነው፡ የ... የ... ሃይማኖትን የሚቃወም ወይም አክራሪ እንደሆንኩ አድርጋችሁ እንደማታስቡኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ዲያብሎስ በሰውዬው ውስጥ ገብቶ፡ ሲጋራ እንዲያጨስ፡ ራሱን እንዲገድል ያደርገዋል። እርሱም የአንድ ሲጋራ ኒኮቲን ሲ—ሲፈልግ፡ ፍላጐቱን ያሟላል፡ አሁን ኩባንያው ይህንን አሳሳች ዘዴ ይዞ ይመጣል፡ እንዲህም ይላል፡ “የሚያስብ ሰው ማጣሪያ።” በዚያኛው እንደተደረገ (እሱን ለማርካት) ከውስጡ ብዙ ታር ለማግኘት፡ አራት ወይም አምስት ሲጋራዎችን ያጨሳል። አሜሪካውያን ለወንድሞቻቸውና ለእህቶቻቸው ሞት እየሸጡ ነው! አልገባኝም።

151 ነገር ግን ፡ በውስጡ፡ ይመስለኛል፡ “የሚያስብ ሰው ማጣሪያ ይላል ትክክል **ነው**።”

152 አሁን፡ አንድ ሰው ሲጋራ የሚያጨስ ከሆነ፡ አስታውሱ፡ የሚያጨስ ሰው ሽታ ይኖረዋል። ከዚያ፡ እስከሚታጨስ ድረስ የ-... የማጨስ ፍላጎት የማታሟላ ከሆነ፡ ማጨስ የራሱን ሱስን የ... የማርካት ሽታውን ያወጣል፡ ስለዚህ፡ አራት፡ ወይም አምስት ሲጋራዎችን ታጨሳላችሁ፡ ለአንድ መደበኛ ሲጋራ፡ ከዚህ በፊት ከምትከፍሉት በላይ ትከፍላላችሁ። አያችሁ፡ ምትሃት፡ ይህ የሸያጭ ምትሃት ነው፡ ሕዝብን፡ አሜሪካውያንን እያታሌለ ነው። ስለ ቫሊ ፎርጅ፡ ጆርጅ ዋሽንግተን ሳስብ፣ ሁለት-ሦስተኛ የሚሆኑት ወታደሮቹ፡ በዚያ ቀዝቃዛ ዘመን፡

ጫማ ሳይለብሱ ነበር የሚሰሩት፡ እኛ ያለንበትን ኢኮኖሚ እንደዚ ለመፍጠር! አሜሪካኖች ለቆሸሸ ትርፍ ብለው፡ አሜሪካዊያን ወንድሞቹ እኅቶቹ፡ በሐሰት ሸንገላ፡ ለሞት ይሸጣል፡ ሞትን ይሸጣሉ፡ ይህ የክፋት ሁሉ ስር። ለገንዘብ ፍላጎት፡ የገንዘብ ፍቅር ነው። ይህ ሁሉ ነገር ሊጠፋ መሆኑን ሳያውቅ፡ ሙሉ በሙሉ ሁሉም ነገር እብደት ሆኗል! ነገር ግን ካላጨሳችሁ፡ ሸታው ሊኖር አይችልም።

153 ከዚያም፡ "የሚያሰብ ሰው ማጣሪያ" ብዬ አሰብኩ። የሚያሰብ ሰው ማጣሪያ! ከዚያም የሰብከት ርዕሴን ከዚያ ወሰድኩና "የሚያሰብ ሰው ማጣሪያ የቅዱስ ሰው ሽታ።"

154 ስለዚህ የሃይማኖት ተቋማችን እንደዚያው ብዙ ነገር አድርገዋል ብዬ አሰብኩ፡ ሰዎችን ተቀብለው ራሳቸውን ክርስቲያኖች ብለው ይጠራሉ። ለምን? በሃይማኖት ተቋማቸው ወይም በድርጅቶቻቸው ውስጥ ብዙ ሰው ስለሚያገኙ ነው። እዚህ ብዙ ሰዎች አሉን ምክንያቱም **በዚህ**፡ **በዚያ**፡ እና **በሌላው**፡ በማንኛውም ነገር ሥር እንዲገቡ እናደርጋቸዋለን። "ይህ ምንም ለውጥ አያመጣም፡ ሰማቸውን ማህደር ውስጥ አስመዘግበው ክርስቲያን ነን ይላሉ። በቃ። ኦህ፡ 'በእምነት ድናችኋል።' ማመን አለባችሁ።" ያ'ማ ዲያብሎስም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል። አዎን።

155 ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ፡ ይህም የሚመጣው በእግዚአብሔር ማጣሪያ ነው! ይህ የማሰብ ችሎታ ያለው ሰው ማጣሪያ ነው። በእጁ ይዤዋለሁ። የሃይማኖት ተቋም ሽታ አይሰጥም፡ ነገር ግን የቅዱስ ሰው ሽታ ያረካል፡ ታውቃላችሁ።

156 በዚህ ማጣሪያ ውስጥ ጸጉሯን-የምታሳጥር ሴት እንዴት ልትመጣ ትችላለች? እንዴት ነው አንዲት ሴት አጫጭር ሱሪ ለብሳ ልትመጣ የምትችለው፡ ወይስ ሱሪ ለብሳ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና፡ "ሴት የወንድን ልብስ መልበስ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው።" ራሱን ከፍ አድርጎ የሚመለከት ሰው፡ ወደዚህ መጥቶ እንዴት እንደ ሴቶች ሊለብስ፡ ፀጉሩ እንደ ሴት ሊያሳድግ፡ ወደ ታች፡ አይኑ ላይ እስኪወርድ ድረስ፡ ልክ **እንደዛ** ሊጠቀልል ይችላል? እሱ የሚሰቱን የውስጥ ልብስ ይለብሳል፡ እሷ ደግሞ የሱ የውጭ ልብሱን ትለብሳለች። የሚያሰብ ሰው ማጣሪያ? አስተሳሰብ ያለው ሰው ያንን አያደርግም፡ ወይም አስተሳሰብ ያላት ሴት ያንን አታደርግም። የእግዚአብሔር ቃል ያ እንዲሆን አይፈቅድም።

157 በዚያ ቃል በኩል ማለፍ የሚችል አንድም ነገር የለም። ያ መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ቃሉንም ወደ እናንተ ያመጣል፡ የቅዱሱንም ሰው ሽታ ያመነጫል።

158 ዛሬ፡ በጐዳና ላይ ቀበጥ ሴት ተመልከቷት፡ ቈንጆ፡ እግዚአብሔር የሰጣት የሚያምር ሰውነት ያላት ሴት፡ ሰይጣን እየተጠቀመበት ነው። ከዛሬ አንድ ሳምንት በኋላ በመቃብር ውስጥ እንደሚበሰብስ ሳታውቅ፡ በጣም ሥነ ምግባር የጐደለው አለባበስ ትለብሳለች።

159 ከረጅም ጊዜ በፊት እዚህ ጐዳና ላይ እየመጣሁ። በሳውዝ ዌስተርን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በተካሄደው ሰብሰባ ላይ በምዕራባዊው የባሕር ዳርቻ፡ አሰምብሊ ኦፍ ጋድ ቤተክርስቲያን በተካሄደው ሰብሰባ ላይ እየሰበክኩ ነበር። አንዲት እመቤት በመንገድ ላይ እየሄደች ነበር፡ የማይረቡ

ልብሶች... ለብሳለች፡ ቢኪንዎች፡ እንጃ ማን ብላችሁ እንደምትጠሩት፡ ጸጉሯ ወደታች ተንጠልጥሎ፡ ባርኔጣና ቡትስ ጫማ አድርጋለች። በመንገድ ላይ እየሄድኩ ነበር። እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “ምስኪን ሴት፡ የአባትዋ እና የእናትዋ የአንድ ቤተሰብ ልጅ ሆይ፡ እዚህ የመጣሺው የእግዚአብሔር ልጅ እንዲትሆኚ ነበር፡ የዲያብሎስ ወጥመድ ሆነሻል።” አሰብኩትና፡ “ወደ ኋላ ተመልሼ፡ ያችን ልጅ ልነግራት እችላለሁ ብዬ አሰባለሁ።” የኔን ልጅ ሣራ ያህል ዕድሜ ያላት ትመስላለች፡ አሥራ ሰባት ዓመት፡ አሥራ ስድስት ዓመት፡ ወይም ሌላ። እኔም፡ “አይ፡ ባልነግራት ይሻላል። ወደዚህ መንገድ ወጥቼ ስለ እሷ እጸልያለሁ። አንድ ሰው ቆሜ ከእሷ ጋር ስነጋገር ካየኝ፡ ይህን ባላደርግ ይሻለኛል” ብዬ አሰብኩ።

160 አሁን፡ አዳምጡ፡ የእግዚአብሔር ልጆች፡ በዚሁ ቦታ ላይ ስትገኙ፣ እነዚህ የዛሬዎቹ ኤልዛቤሎች ይጫወቱባችኋል፡ ነገር ግን አስተሳሰብ ያለው ሰው አስቀድሞ ያስባል። ምናልባት፡ በጣም ቈንጆ ልትሆን ትችላለች፡ “ከእሷ ጋር አንዴ እንዲህ ላድርግ፡” ነገር ግን ልጄ ሆይ፡ ይህ የነፍስህን ዋጋ ያስከፍልሃል፥ እናንተም ሴቶች፡ ለእነዚያ ቀበጦች! የሚያሰብ ሰው ማጣሪያ የአንድ ቅዱስ ሰው ጣዕም ያመነጫል።

161 እናንተ ያገባችሁ ወንዶች፡ እንደነዚህ ያሉትን ሴቶች በጐዳና ላይ ስታዩ፡ እናንተ የእግዚአብሔር ልጆች፡ በመጀመሪያው ጅማሬ ላይ ምን እንደሆነ አታውቁምን? ሳይንስ ሴቶችን በጥፋት ውኃው ዓለም ጊዜ በጣም ቈንጆ ባደረጋቸው ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች በወሰዱ ጊዜ (የእግዚአብሔር ሴቶች ልጆችን አይደለም)፡ እግዚአብሔር በጭራሽ አልታገሰውም። ሁሉንም ነገር አጥፍተዋል፣ ሳይንስ፡ ቊንጅና። በ... በመጨረሻው ዘመን የሚነሱ የሴቶች ውበት እየጨመረ መምጣቱ፡ የመጨረሻው ዘመን ምልክት ነው፣ እግዚአብሔር አረጋግጦታል። ስለዚህ፡ የሚያሰብ ሰው ማጣሪያ ተጠቀሙ፡ የቅዱስ ሰው ጣዕም ይኖራችኋል። ይህ ቤትህን ዋጋ ያስከፍላል። ቦታህን ዋጋ ያስከፍልሃል። ያለህን ነገር ሁሉ፣ እንዲሁም፡ ነፍስህን ያስከፍልሃል። ቤታችሁን ያፈርሳል። ልጆቻችሁን የሚያሳድገው ሌላ ወንድ፡ ወይም ሌላ ሴት ልትሆን ይችላል።

162 የሚያሰብ ሰው ማጣሪያ ውሰጂ፡ የቅድስት ሴት ጣዕም ያመነጫል። ወደ ጸጉር ቆራጭ ቤት ስትሄጂ፡ ወይም ሌላ ቦታ፡ እንዲህ ይሉሻል፡ “ታውቂያለሽ፡ ራሰ ምታት ይይዝሻል” ይሉሻል። መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውን፡ የምታሰብ ሴት ማጣሪያ ዉሰጂ፡ አየሽ፡ ከዚያም ከሱ ራቂ። አየሽ? አታድርጊው።

163 እኔ ወንድማችሁ ነኝ፡ እወዳችኋለሁ። በእናንተ ላይ ምንም የለኝም። እግዚአብሔር ያውቃል። ያ ነው የምናገረውን እንዲናገር የሚያደርገኝ፡ ለእናንተ ያለኝ የ—የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። አንድ ሰው ወደዚያ ቢሄድና ትክክል እንዳልሆናችሁ የማይነግራችሁ ከሆነ፡ ፓስተራችሁ እንደዚያ እንድትሆኑ የሚፈቅድ ከሆነ፡ አይወዳችሁም ማለት ነው። ሊወዳችሁ አይችልም። ለሴቶች እንዲህ ዓይነት ፍቅር አልፈልግም። ለእህቴ የተቀደሰ ሽታ እንዲኖራት እፈልጋለሁ። በእውነትም እኅቴ እንድትሆን እፈልጋለሁ። ማንም ስለ እሷ በጣም ቆንጆ እንደሆነችና እንዴት እንደሆነች፡ ማንም ሊናገር አይችልም፡ እነዚያ የወሲብ ንግስቶች፡ “ወደ እኛ... ” ሁህ-ኡህ። አይሆንም። እመቤት እንዲትሆን እፈልጋለሁ!

164 ኦህ ጌታ ሆይ፡ ከዓለት በታች ጠብቀኝ። አዎን። በኤፌሶን 5፡26 ላይ፡ ወደዚህ ዓለት ማለፍ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ፡ ይህም፡ “በቃሉ በመለየት በውኃ በመታጠብ።” በትክክል።

165 አሁን፡ ይህ ዲያብሎስ በትምህርቱ እንዲረጭባችሁ አትፍቀዱለት። አይ፡ አይ። ተጽእኖዋችሁን ይገድልባችኋል። ዲያቢሎስ ይህን እንዲወስድ አትፍቀዱ፡ “መልካም፡ እኔ እናቴ አባል የነበረችበት ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ፡ አባቴ፡ አያቴም እዚያ ነበሩ።” ዲያቢሎስ ይህን እንዲረጭባችሁ አትፍቀዱ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናትና፡ ስለእነዚህ ነገሮች፡ አስቀድሞ ተናግሯል፡ ሁሉም ወደ ዘሪነት ተለውጠዋል! በትክክል። ሁሉም ነገር የተበላሸ ነው። ሁሉም ነገር የበሰበሰ ቍሰል ሆኗል። እንዲህ እያለ፡ እንዲረጭባችሁ አትፍቀዱ፡ “ደህና፡ ይህ ከፍ ያለ ሥነ ምግባር ነው። እኛ ከቀድሞዎቹ ጊዜያት የበለጠ የተማርን ሆነናል።” ዲያብሎስ ይህን በላያችሁ እንዲያደርግ አትፍቀዱ። የሰልጣኔ፡ የትምህርትና የሳይንስ ፕሮግራሙን በሙሉ አሳይቼቸዋለሁ። ያንን ወደ ቤተክርስቲያኑ በቀጥታ አስገብቷል፡ ያንን አትስሙ። አሮጌዎቹን የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችና ሌሎች ነገሮችን ከማየት ተቆጠቡ!

166 ጽሑፋችንም እንዲህ ይላል፡ “ተለወጡ እንጂ፡ አትምሰሉ።” ወደ ውስጥ ገብታችሁ፡ “እሁድ፡ ተቀብያለሁ” አትበሉ። አይ። ወደ ውስጥ ገብታችሁ አሁን ተለወጡ። መጀመሪያ ከነበራችሁበት፡ እግዚአብሔር እንዲትሆኑ ወደሞፈለገው ተለወጡ።

167 አሁን፡ ይህ በእናንተ ውስጥ ባለው ዘር ይወሰናል። የአስተሳሰብ፡ የትምህርት ዘር በውስጣችሁ ከተተከለ፡ ለእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች፡ አንድ ነገር ብቻ ነው ሊያደርግ የሚችለው፡ ያዛባችኋል፡ ያ ነው በቃ። ማድረግ የሚችለው ብቸኛው ነገር ይህ ነው። በዛሬው ጊዜ ያሉ ሰዎች፡ እኔ እንደማያቸው፡ እግዚአብሔር እንዳለ እንኳን የማያምኑ ይመስላሉ።

168 ይህን አገላለጽ ይቅርታ አድርግሉኝ። በዚህ ምክንያት የማንም ስሜት የሚጐዳ ከሆነ፡ ስሜታችሁን ለመጉዳት አይደለም። ከጥቂት እሁዶች በፊት፡ ሴት ልጄ፡ ወደ ቴሌቪዥን መጥቼ መንፈሳዊ መዝሙር እንድመለከት ጋበዘችኝ። እሁድ ጠዋት ነው። ኦራል ሮበርትስን በፕሮግራሙ መስማት ፈልጌ ነበር፡ እንዲነግሩኝ ጠየቅኳቸው። እንዲህ አሉኝ፡ “ይህን ሰማው፡ ግሩም መዝሙር ነው።” ወንዱ ልጄም እዚያው ቆሞ፡ እርሱም፡ ስለ መዝሙሩ ነገረኝ። እኔም ተቀመጥኩ...

169 ቤቷ ውስጥ ቴሌቪዥኑ ካላት ሴት ተከራይተን ነው። እንጂ በቤቴ ውስጥ ቴሌቭዥን እንዲኖረኝ አስቤም አላውቅም። አይ፡ ወዳጄ። በቤቴ ውስጥ እንዲህ ያለ ነገር አልፈልግም። በጠመንጃዬ አፈንዳው ነበር። ከዚያ ክፉ ነገር ጋር ምንም ግንኙነት አልፈልግም። አይ፡ ወዳጄ! ነገር ግን...

170 እስቲ ስለ እናንተ አሪዞናውያን ልንገራችሁ። በቀደም የነበረውን፡ የትምህርት ቤቶችን ጥናት አይታችኋል፡ አላያችሁም? በአሪዞና ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙት ልጆች መካከል ሰማንያ በመቶ የሚሆኑት በአእምሮ በሽታ ይሰቃያሉ፡ ከእነዚህ ውስጥ ስልሳ-ሰባት በመቶ የሚሆኑት ቴሌቪዥን በመመልከታቸው ነው። ስለዚያስ?

171 ጠመንጃችሁን ብትጠቀሙበት የተሻለ ነው! አያችሁ? አሁን፡ ዲያብሎስ ያ ነገር እንዲረጭባችሁ አትፍቀዱለት። በጭራሽ፡ ወዳጄ። አሁን ሰዎች፡ እንዳልኳችሁ፡ ሰዎች ወደ ፍርድ መምጣት እንደሌለባቸው ይመስላቸዋል።

172 እነዚያ ወንዶችና ሴቶች፡ አንዳንድ ሕንዳውያን ቤተሰቦችና፡ ሌላም ብዙ ነገሮች ነበሯቸው። ሚስተር ፑል የሚባል አንድ ሰው የዚያ አለቃቸው ይመስለኛል። መሳለቂያ የሆነ ዘመናዊ የመዝሙር አይቼ ከሆነ ይህ ነው፡ አዘማመራቸው ያ ነበር፣ የቀበጦች ስብሰብ ቆመው፡ እጃቸውን ወደላይ-እና-ወደታች እየወዘወዙ ነበር።

173 በእርግጥ ዛሬ ጠዋት የዘመረውን ወጣት አድንቄዋለሁ፡ ያ መዝሙር፡ እንደ ጨዋ ሰው፡ እንደ ትክክለኛ ሰው ነው የዘመረው። ያንን እ—እወዳለሁ። እ—እናንተ ነጋዴዎች አንዳንድ ጊዜ እዚህ የቆሙትን እነዚህን ዘማናዊ ወጣቶችን ታመጣላችሁ፡ ፊታቸው ሰማያዊ እስኪሆን ድረስ ትንፋሻቸውን ይዘው፡ ይጮሃሉ፡ ይንጋጋሉ፣ ያ መዘመር አይደለም፡ ያ ብዙ ሳይንሳዊ ጫጫታዎችን እያደረገ ነው። **መዘመር** "ከልብ የሚመነጭ ዜማ ነው።"

174 እኔም እንዲህ አሰብኩ፡ "እንዴት ያሳዝናል! እንዴት ያሳፍራል! ታዲያ እንዴት ነው በሃይማኖት ስም፡ እግዚአብሔር እንደሌለ አድርገው የሚመላለሱት!" በቀደም፡ አንድ ሰው፡ ከልጄ ጋር የሚሄደውን ልጅ እንዲህ አለ፡ አንድ ክርስቲያን ልጅ፡ ስለ አዳምና ሔዋን አንድ ብልጥ አስተያየት ሰጠ፡ እንዲህ አለ፡ "ሄዋን በአትክልት ስፍራ በኩል እየሄደች ነበር። እንዲህ አለ፡ 'ልጆች ሆይ፡ ያቺን ዛፍ ታያላችሁን?' እንዲህ አለ፡ 'እናታችሁ ከዛ በልታ ነው ከቤታችን ያወጣችን'" አንድ ታማኝ ክርስቲያን የሆነ ሰው፡ ቃል ኪዳንንና የእግዚአብሔርን ቃል ወስዶ፡ ወደ አሳማ ማረፊያ ይጥለዋል ብላችሁ መገመት ትችላላችሁን! ወደ ፍርድ እንደማይቀርቡ አድርገው ያሰባሉ። እግዚአብሔር ምሥጢርን ሁሉ ወደ ፍርድ ያመጣል። እግዚአብሔር እንደሌለ አድርገው ይመላለሳሉና።

175 ሞኞች ብዬ ልጠራቸው አልፈልግም፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል አ... አይደለም ይላልና። ኢየሱስ እንደዛ አላለም። "ማንንም ሰው ሞኝ አትበሉ።" ነገር ግን በመዝሙር 14፡1 ላይ፡ "ሞኙ በልቡ፡ 'እግዚአብሔር የለም ይላል' ይላል።" አያችሁ? ሞ—ሞ... ሞኞች ብዬ መጥራት አልፈልግም፡ የሚመላለሱት ግን እንደ ሞኞች ነው። እንደዛ ናቸው።

176 ስለዚህ፡ ዛሬ የት እንደደረስን ታያላችሁ፡ ልክ እንዲህ እንደማለት ነው፡ 'እግዚአብሔር የለም።" "የቤተክርስቲያን አባል ነኝ!" ሁሉም ለእነሱ፡ ሁሉም ነገር፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ትልቅ ቀልድ ነው። "ቤተክርስቲያናችን የት እየሄዱ እንዳሉ ታውቃለች!" አዎ... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]... በቀጥታ ወደ ሲኦል፡ በትክክል። ቀጥታ በመንገዳቸው ላይ ናቸው፡ ቀጥታ በሳይንስ እና በትምህርት፡ በሥነ መለኮት ሴሚናሮች እና በመሳሰሉት፡ ይህ ሁሉ ወደ ሲኦል መንገድ ቀጥታ ይገፋቸዋል። መንፈስ ቅዱስ ስለ ምንም ነገር ራእይ ለመስጠት እድል የለውም፥ ሴሚናሪው ጨርሶታል።

177 መንፈስ ቅዱስ ይምራን እንጂ፣ ሴሚናሪ፡ ጳጳሳትና የበላይ ተመልካቾችና፡ የመሳሰሉት ሊመሩን አይገባም። መንፈስ ቅዱስ መሪያችን ነው።

178 ቃየን እንዲህ ዓይነት ሰው ነበር። በሥራው በጣም ሃይማኖተኛ ነበር። አሁን፡ ሊኖራችሁ የሚገባው ሁሉ ሃይማኖት ብቻ ከሆነ፡ እግዚአብሔር ቃየንን

በማውገዙ ፍትሃዊ አልነበረም ማለት ነው። ምክኒያቱም፡ እሱ ሃይማኖተኛ ነበር፡ ልክ እንደ አቤል ሃይማኖተኛና ቅን ነበር። አሁን አስታውሱ፡ ስለ እግዚአብሔር ያስብ ነበር፡ እግዚአብሔርን ያመልክ ነበር፡ ቤተክርስቲያን ነበረው፡ መሠዊያ ሠራ፡ መሥዋዕት አቀረበ፡ ጸለየ፡ አምልኮ አቀረበ፡ ግን ተቀባይነት አላገኘም። ምንም ይሁን ምን... ኤሳውም፡ እንደዛ ነበር። አያችሁ?

179 ሃይማኖት፡ አያችሁ፡ የሰይጣን ሥራ ነው፣ ሁሉንም ነገር መግደል ሳይሆን፡ ማበላሸት ብቻ ነው። ያ ነው በቃ። ሁሉንም ነገር አይገድልም። ኦህ፡ ኮሚኒስቶች አይደሉም፣ አይ፡ አይ፡ ፀረ ክርስቶስ ኮሚኒዝም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ "የሚቻል ቢሆን የተመረጡትን እንኳ ያስታል" ይላል። የብረት መጋረጃውን አትመልከቱ፡ ግን ሐምራዊውን ተመልከቱ። ኧሃ-ሃህ።

180 ነገር ግን፡ አስተውሉ፡ ቃየን ሊያመልክ መጣ፡ ነገር ግን በውስጡ የተሳሳተ ዘር፡ ይኸውም የእባብ ዘር እንደነበረ ልብ በሉ። የሴቲቱ ዘር ስለሆነ፡ የእባቡ ሹክሹክታ በእሱ ላይ ሹክ ብሎ ነበር። ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢያውቅም፡ ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ አልሆነም። ይህንን ታውቃላችሁ? ሰይጣን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያውቃል፡ ነገር ግን ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ አይደለም።

181 አስተውሉ፡ እግዚአብሔር የአቤልን መልእክት ልክ መሆኑን ሲያረጋግጥ አይቷል። አሁን እኔ ለአንድ ደቂቃ እንዲታሰቡ፡ የአስተሳሰባችሁን ማጣሪያ እንድትጠቀሙ እፈልጋለሁ። የአቤል ትክክለኛ መልእክት፡ እግዚአብሔር እውነት መሆኑን አረጋግጧል! አሁን በምናባችሁ እየሳላችሁት ነው? ኡህ-ኡሁ። የአቤል መልእክት ተቀባይነትን አገኘ፡ ቃየንም እግዚአብሔር የአቤል መልዕክት ትክክል መሆኑን እንዳረጋገጠ አይቷል። ነገር ግን ይህን ማድረግ አልቻለም። ኩራቱ ዕንቅፋት ሆነበት። ያ ትክክል ነው፡ ኩራቱ እንዳይታዘዝ ከለከለው። እግዚአብሔር መልዕክቱን ሲያረጋግጥ ተመልክቷል።

182 ስለዚህ አሁን፡ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል ራሳቸውን ዝቅ ለማድረግ የከበዳቸው ይመስላል። ይ—ይ—ይህን ማድረግ አይፈልጉም። ለሃይማኖት መገለጫ ራሳቸውን እንደሚያስገዙ ምንም ጥርጥር የለውም፡ በእርግጠኝነት፡ ይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር ቃል አይገዙም።

183 ይህን ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ እ... እዚህ ጥቅስ ይዣያለሁ፡ የማመለክታችሁ ወደዚያ ነው። ዘፍጥረት 4፡6ና 7 ላይ፡ እግዚአብሔር ቃየንን፡ እንዲህ አለው፡ "ፊትህ ለምን ጠቆረ? በቍጣ ተሞልተህ፡ ለምን ትመላለሳለህ? የሚያናድድህን መልዕክት ስለ ሰማህ ነው።" እንዲህ አለው፡ "ደህና፡ ይህን የምታደርገው ለምንድን ነው? ወደ ቤተክርስቲያንህ ስላልገባሁ፡ ፊትህ ለምን ጠቈረ? ታዲያ ለምን እንዲህ አደረግህ?"

የማሰብ ችሎታ ያለው ሰው ማጣሪያ እየተጠቀማችሁ ነው? አያችሁ?

184 ወይም፡ "ለ... ለምን እንዲህ ታያለህ?" እንዲህ አለው፡ "መልካም ብታደርግ፡ ወንድምህ እዚያ እንዳደረገው አድርግ፡ ተቀብዬ እባርክሃለሁ። ለአንተም ተመሳሳይ ነገር አደርጋለሁ።" እሱ ግን ይህን ማድረግ አልቻለም። እንዲህ አለው፡ "አሁን፡ ይህን ካላደረግክ፡ ያለማመን ሃጥያት በደጅህ ታደባለች።"

185 አሁን “የተአምራት ዘመን አልፏል፡” ሲሉን፡ እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን እንደሚፈጽማቸው ቃል በገባቸው በራእይ ምዕራፍ 10ና፡ በሚልክያስ ምዕራፍ 4 መሰረት፡ የተጠቀሱትን ነገሮች በሙሉ ፍጹም በሆነ መንገድ አጽድቋል አረጋግጧል፡ አያችሁ፡ እነዚህ ሁሉም ነገሮች በትክክል ተረጋግጠዋል፡ ችግሩ ምንድነው፡ ወንድሞቼ? ምንድነው ችግሩ፡ አያችሁ?

186 ይህ ካላደረጉ፡ አለማመን ነው፡ ይህም ሃጥያት ነው... አንድ ሃጥያት ብቻ ነው ያለው፡ ይህም፡ አለማመን ነው። በትክክል። ስለጠጣችሁ፡ ስላጨሳችሁ፡ ስለቃማችሁ፡ አጫጭር ሱሪ ስለለበሳችሁ፡ ወይም ማንኛውንም ነገር ስላደረጋችሁ አይፈርድባችሁም። አይ፡ ያ አይኮንናችሁም። ይህ የሆነበት ምክንያት ስላላመናችሁ ነው። ብታምኑ፡ ይህን አታደርጉም ነበር። አያችሁ? አንድ አማኝ እንዲህ አያደርግም። የሚያስብ ሰው ማጣሪያ ይወስዳል፡ አያችሁ፡ አያችሁ፡ ወይም የሚታስብ ሴት ማጣሪያ ትወስዳለች፡ ከሁለቱ አንዱን ትወስዳላችሁ። መልካም። ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ሃጥያት በበር ላይ ያደባል።

187 አሁን በቃየን ላይ ያደረገውን አስተውሉ፡ ዛሬም እንዲሁ ያደርጋል፡ ቃየን ሆን ብሎ ኃጢአተኛ ሆኖ እንዲሄድ ያደረገው፡ ሆን ብሎ አለመታዘዙ ነው። እያንዳንዱ ሰው እንደዚያው ይሆናል። አቤል ያስተላለፈው መልእክት ከእግዚአብሔር **ዘንድ** የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ካየ በኋላ ሆን ብሎ ባለመታዘዙና ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆኑ፡ በዚያን ጊዜም ተመሳሳይ ድርጊት አደረገ፡ ከዚያም የድንበር መስመሩን ተሻገረ።

188 መሻገር የምትችሉበት መስመር አለ። ይህን ታውቃላችሁ፡ አይደል? አሁን፡ አገልጋዮች ሆይ፡ እዚህም ሆነ ይህ ሰ—ሰርጭት በመላ አገሪቱ በሚተላለፍበት በተሌፎን መስመር ውስጥ ያላችሁ፡ ይህን ተገንዝባችኋል? ቅዱሳት መጻሕፍትን ስትመለከቱ፡ አታደርጉትም፡ እግዚአብሔር... ኦ... ኦህ፡ ትቀጥላላችሁ፡ ተባረኩ። ስለዚህ እያንዳንዱ እስራኤላዊያን፡ እነሱ በትክክል በምድረ በዳ ውስጥ ይኖሩ ነበር፡ ልጆችን፡ ሰብሎችን ያሳድጉ ነበር፡ ተባርከዋል፡ ሁሉንም ነገር አላቸው፡ ነገር ግን “እያንዳንዳቸው ለዘላለም ከእግዚአብሔር ተለይተዋል።” ኢየሱስ እንደዛ ብሏልና። ኦህ፡ አዎ፡ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ይባርካችኋል፡ ነገር ግን እናንተ ሄዳቸዋል። በእርግጠኝነት። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ አሁን የሚለው ነው፡ እርሱ ያለው እንደዚህ ነው። አስተውሉ፡ የድምበር መስመሩን ማቋረጥ ትችላላችሁ። ይህን ታምናላችሁ? ቃየን አቋረጠው።

189 እ—እስቲ ለደቂቃ ይህን እንመልከት፡ ዕብራውያን 10፡26። ያንን በፍጥነት የማገኝ ከሆነ እንመልከት። የዕብራውያን መጽሐፍ፡ 10ኛው ምዕራፍና 26ኛው ቁ... ቁጥር፡ ይመስለኛል። እዚህ ላይ ጽፌዋለኑ። አንድ ደቂቃ ብቻ፡ ከእኔ ጋር ከታገሳችሁ፡ እስቲ ለአንድ ደቂቃ ብቻ እናንብበው። መልካም፡ እናንብበው።

> **የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በ... በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ፡ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፡**
>
> **የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው፡ የእሳት ብርታት አለ።**

190 ይህ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው። ይህን ካየንና ከሰማን በኋላ ሆን ብለን ካላመንን፡ መስመሩን ተሻግረናል ማለት ነው። ከዚህ

በኋላ ይቅርታ አይኖርም፡ መስመሩን ተሻግራችኋል።

“ኦህ፡” እንዲህ ትላላችሁ፡ “እግዚአብሔር አሁንም እየባረከኝ ነው።” ኦህ፡ አዎ።

191 እስራኤልን አስታውሱ፡ **ድንበሮችን**፡ እግዚአብሔር ቃል በገባላቸው ጊዜ፡ ወደ ቅድስቲቱ ምድር፡ መ... መልካም፡ ወቴትና ማር፡ ወዳለባት፡ ሙሴም ካሌብንና ኢያሱን፡ ሰላዮቹንም፡ ወደ ማዶ በመላክ፡ ምድሪቱን እንዲሰልሉና፡ የተረጋገጠውን ማስረጃ ይዘው እንዲመለሱ በላካቸው ጊዜ፡ አሥሩ ሰላዮች እንዲህ አሉ፡ “እኛ ማድረግ አንችልም፡ አቅም የለንም፡ እዚያ ያለውን ችግር ተመልከቱ፡ አክራሪዎች እንሆናለን፡ ከእነርሱ ጋር ለመዋጋት ያለን ትንሽ ትናንሽ ነገሮች ናቸው፡ እነርሱ ያላቸውን ተመልከቱ፡ ይህን ማድረግ አ—አንችልም፡ ማድረግ አንችልም” አሉ።

192 ኢያሱና ካሌብ ግን፡ “ይህን ሁሉ ማድረግ እንችላለን፡ እግዚአብሔር ቃል ገብቶልናል” አሉ።

193 እና፡ አስታውሱ፡ ወደ ኋላ ተመለሱ። ያ በቃዴስ-ባርኔያ ነበር። እነሱም ወደ ኋላ ተመልሰው በምድረ በዳ ተቅበዝበዙ። እያንዳንዳቸው ሞቱ፡ ለዘላለም ጠፉ። ኢየሱስ እንደዛ ብሏልና።

194 ይህን የድምበር መስመር አትሻገሩ፡ እያችሁ። “መልካም ነገር ማድረግ እያወቃችሁ፡ የማታደርጉት ከሆነ፡ ኃጢአት ይሆንባችኋል።”

195 እስራኤላውያንም እንዲሁ አደረጉ። ሙሴ በእግዚአብሔር እንደተረጋገጠ ካዩ በኋላ፡ በለዓም እንዲረጭላቸው አደረጉ፡ በዚያ በጸደቀው ውድ ዘር ላይ። ፓስተር ሆይ፡ ይህን ቃል የሚፃረር (በጭራሽ) ምንም ነገር አትናገር። በለዓምን ተመልከቱ፡ እርሱ ነቢይ ነበር፡ የእግዚአብሔርም ዘር ሲፀድቅ ተመልክቷል። ነገር ግን እሱ በሚኖርበት ታላቅ ሃይማኖት ተቋም ስር፡ ሞዓብ ያንን ተጓዦች በሀገሩ በኩል ሲመጡ አይቶ፡ ረጩና፡ እንዲህ አለ፡ “መልካም፡ ቆይ ቆይ። ሁላችንም ክርስቲያኖች ነን። ሁላችንም አማኞች ነን። ምክንያቱም፡ አባቶቻችንና አባቶቻችሁ አንድ ናቸው። እኛ የሎጥ ልጆች አይደለንምን? ሎጥ የአብርሃም የወንድም ልጅ አልነበረም? ሁላችንም አንድ አይደለንምን? እርስ በርሳችን እንጋባ።”

196 እስራኤልም፡ እንደ ሔዋን በኤደን የአትክልት ስፍራ፡ ሰይጣን እንዲረጭባት እንደፈቀደችው ሁሉ፡ እስራኤልንም በሐሰተኛ ነቢይ አማካይነት እንዲረጭባት አደረገ። ይህም፡ እውነተኛው ነቢይ በተረጋገጠ ቃል፡ ከእነሱ ጋር እያለ ይህን አደርጉ። ነገር ግን በአዕምሯዊ እውቀት ጽንሰ ሀሳብ አማካኝነት፡ በእነርሱ ላይ ረጩባቸው። እሰቲ አሰቡት። አሁን፡ ይቅር አልተባልም ነበር፡ ኃጢአት ይቅር አልተባልም ነበር።

197 ዘሮቹ ወደ ተሰፋይቱ ምድር በምደርገው፡ ግዳጅ መንገድ ላይ በሰበሱ። እያንዳንዳቸው በቀጥታ በቤተክርስቲያን ውስጥ፡ በጉዟቸው፡ እግዚአብሔርን እየተከተሉ፡ ጠፉ በሰበሱ። ሰይጣንም ያንን የአዕምሯዊ ስፕሬይ፡ የትምህርት፡ የአዕምሯዊ ጽንሰ ሀሳብ፡ እንዲህ እያለ ረጨው፡ “ለምን፡ ሁላችንም አንድ ነን፡ ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን።” ተመሳሳይ አይደላችሁም! ነገር ግን ያ የሐሰት አስተማሪ ያለውን የራሱን አዕምሯዊ ግንዛቤ እንዲረጭላቸው ፈቀደ።

198 ልክ ዓለም አቀፉ ምክር ቤት አሁን እያደረገ እንዳለ ነው፡ እያችሁ፡ ተመሳሳይ ነገር፡ “ለምን፡ ሁላችንም በአንድ ታላቅ ድርጅት ውስጥ እንቀላቀላለን” ይላሉ። ሙሉ የድርጅታችሁ ሥርዓት የዲያብሎስ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ የአውሬው ምልክት ነው። ጌታ ቢፈቅድ፡ በጣም በቅርብ ጊዜ፡ በዚህ ላይ መጽሐፍ ይኖረኛል።፡

199 በኖኅ ዘመን፡ በመርከብ ሊንሳፈፍ፡ ቃሉን ስታዘዝ፡ አስተውሉ። አሁን እዚህ ጋር አንድ ነገር ላስቀምጥ፡ እየመጣ ያለው ቃል ከምድር ወደ ሰማይ ለመለወጥ ነው። የነገሩን ሁኔታ እያዩ፥ ነገር ግን በአዕምሯዊ አስተሳሰባቸው፡ ስለ መጨረሻው ዘመን፡ ትንቢት ሲናገራቸው፡ በነቢዩ በኖኅ ፊት ይስቁ ነበር። ይ... ይህ አወቃቀር የተገነባው በእግዚአብሔር ቃል ነው፡ በውስጥና በውጭ፡ በጸሎትና በእምነት ነው የተገናባው። ዝናቡ ሲመጣ፡ የሃይማኖት አስተሳሰቦች ሁሉ ሞቱ በ... በቤተክርስቲያናቸው ውስጥ፡ በምድር ላይ በሰበሱ። መርከቡም ከሁሉም በላይ ተንሳፈፈ። ሳይንስ የተረጨው ዘር በፍርድ በሰበሰ።

200 ለማንኛውም፡ ምን ለማድረግ እየሞከርን ነው? ቤተ ክርስቲያናችንን ለማቋቋም እየሞከርን ነው ወይስ የእግዚአብሔርን ቃል ለማቋቋም? ምን ለማድረግ እየሞከርን ነው? በምን ላይ እየሠራን ነው? ሰዎች ወደዚህ እንዲመለሱ ለማድረግ እየሞከርን ነው? ይህች ታላቅ ሔዋን በእነዚህ የመጨረሻ ዘመን፡ ይህች ቤተ ክርስቲያን ሔዋን ምን ለማድረግ እየሞከረች ነው?

201 ቶሎ ብዬ እጨርሳለሁ፡ ወንድሜ፡ ምክንያቱም በ—በጣም ቆይተናል። አሥራ አምስት ደቂቃ ብቻ ሰጠኻና፡ የ—ያዝኩትን ቅዱሳት መጻሕፍትን በማስተማር እጨርሳለሁ። [አንድ ወንድም እንዲህ አለ፡ “በእርግጥኻነት፡ ሰብከቱን ቀጥል።”—እርታዒ።] አዎን። እሺ። አውቃለሁ። መልካም፡ ሰዎች ወደዚህ መጥተው ወደ ቀጣይ ነገር ለማለፍ ይችኩላሉ። ነገር ግን ለእኔ ለማቆም ከባድ የሆነ ይመስላል። እቸኩላለሁ። መልካም።

202 ተመልከቱ፡ ታላቂቱ የሳይንስ፡ የትምህርት፡ ዲቃላ ሔዋን ዛሬ፡ ቤተክርስቲያን የምትባለው፡ ምን ለማድረግ እየሞከረች ነው? የእግዚአብሔርን ቃል ከፍ ከፍ ለማድረግ እየሞከረች ነው? ሕዝቡም እንዲሁ እንዲያደርግ ትፈቅዳለች? የሚያስብ ሰው ማጣሪያ፡ ወይም፡ የእግዚአብሔር ማጣሪያ እየተጠቀሙ አይደለም። ምን እያመረቱ እንደሆነ ተመልከቱ። ራሳቸውን ከፍ ከፍ እያደረጉ ነው። ቤተክርስቲያን፡ በተዛባ የእውቀት ዘር መርሃ ግብርዋ፡ መላውን ዘር የእግዚአብሔር ቃል በሳይንሳዊ መንገድ እንዲቃወሙ አድርግኣለች። አሁን እነዚያን ነጥቦች ልያዛቸው፡ አሁን ለማጠናቀቅ፡ በጣም ረጅም ጊዜ አላወራቸውም። ሳይንሳዊ ድንቍርና! እግዚአብሔር፡ እዚህ ምድር ላይ፡ ቃል በገባው ቃል መሰረት፡ እያደረገ ያለውን ነገር ሲያደርግ፡ እነሱም ይህን ችላ ብለው ይሄዳሉ ምክንያቱም ሳይንሳዊ ደንቆሮ ናቸው። ሳይንሳዊ ድንቍርና!

203 ወንድም ዊልያምስ እዚህ በመምጣቱ ፈገግ እያልኩ ነበር፡ በወረቀት ላይ የሆነ ነገር ጽፎ ነው፡ “በዚህ ላይ ከሰዓት በኋላ ሙሉ መቈየት ትችላለህ፡” ወይም እንደዛ ነገር። ነገር ግን፡ ያንን አደንቃለሁ፡ ያ በጣም ጥሩ ነው። እያችሁ?

204 ሕዝቡ ግን ሆን ብ—ብለው ኃጢአት እየሰሩ ነው። በዛሬው ጊዜ ያለው የ—የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በሙሉ ሆን ብሎ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዲሠራ አድርጓል። ለምን፡ የሚያሳዩት ተመሳሳይ ባህሩ ይህ ትክክል መሆኑን ያረጋግጣል። መልካም። የፍትወት መጋረጃ አይኖቿን፡ ከእግዚአብሔርን ቃል ጋረዳትና፡ ራሷን እንደገና እርቃኗን አገኘች። ታውቃላችሁ፡ እግዚአብሔር፡ በራእይ 3 ላይ፡ እንዲህ ብሏል፡ "ኑ፡ ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ፡ ኩል ከእኔ ግዙ።" አያችሁ፡ ኩሉም ቃሉ ነው።

205 ታውቃላችሁ፡ እንዲህ ይላሉ፡ "መልካም፡ ይሄ ሰውዬ ዲግሪውን ለማግኘት፡ አርባ ዓመት ተምሯል። እሱ B.L.D.፡ D.D.፡ እና ይህ ሁሉ አለው።"

206 ኢየሱስ ስለዚህ ጉዳይ የተናገረውን ታውቃላችሁ? እንዲህም አለ፡ "ሰው ራሱን ይካድ።" ጳውሎስ አደረገ።

እንዲህ ትላላችሁ፡ "በእርግጥ እንዲህ ማለቱ አይደለም።"

207 እሺ፡ ታዲያ ጳውሎስ እየሱስ ያለውን ያደረገው፡ ለምን ነበር? እንዲህ አላቸው፡ "በሚያባብል ቃላት ወይም በሰው ጥበብ ወደ እናንተ አልመጣሁም፡ ምክንያቱም በዚያ ላይ ተሰፋችሁን ትገነባላችሁ። ነገር ግን እኔ ወደ እናንተ የመጣሁት በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ነው፡ እ... እምነታችሁ የሚገነባው በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንጂ፡ በጥበብ መገለጥ ላይ አይሁን።"

208 ሰዎች የሚያመሳስላቸውን ባህርይና ትህትናቸውን ያጡ ይመስላል። እንደ ድሮው አይደሉም። ነቢዩ፡ "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡" ብሎ ሲናገር ሕዝቡ፡ ይንቀጠቀጥ ነበር። አዎን፡ አድርገዋል። ሕዝቡ በፍርሃት፡ ተንቀጠቀጠ። አሁን ግን ፍርሐቱን ሁሉ አጥተዋል። እግዚአብሔርን አይፈሩም።

209 ሰሎሞን፡ "የ—የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው" ብሏል፡ መጀመሪያ።

210 ነቢዩ ግን **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** የሚለውን መናገር ይችላል፡ ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡ "ትርጉም የለውም!" አያችሁ፡ ምንም ተስፋ የላቸውም። እነሱም፡ እንዲህ ይላሉ፡ "ለምን፡ እኛ ብልህ ነን። እኛ አዋቂዎች ነን፡ እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን መቀበል የለብንም! ስለ ምን እያወራን እንደሆነ እናውቃለን!"

211 አንድ የድሮ አባባል አለ፡ ይህም፡ "መላእክት እንዳይደርሱበት በሚፈሩበት ቦታ፡ ሞኞች በተጠለፉ ጫማዎች ይራመዳሉ።" እርግጥ ነው።

212 አሁን፡ መለወጥ ማለት ምንድነው? (በፍጥነት እናያለን።) እንዴት ነው የምናገኘው? መለወጥ ምን ያደርጋል? እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው በቃሉ መንፈስ አማካኝነት ነው። ይለውጣል። ዘሩን ይተክላል፡ መንፈሱንም ያፈሰበታል፡ ዘሩ ምርቱንም ያፈራል። መንፈስ ቅዱስ የቃሉን ዘር በመለወጥ ከራሱ አይነት አፍርቶ እንዲጸድቅ ያደርጋል።

213 ምን ዓይነት ዘር ናችሁ፡ ያ የሚያሳየው በውስጣችሁ ምን እንዳለ ነው። ይህን መደበቅ አትችሉም። ውስጣችሁ ያለው ምንም ይሁን ምን፡ ውጪውን ያሳያል። ከዚህ መራቅ አትችሉም። ያንን ዛፍ ሌላ ነገር ማድረግ አትችሉም ነገር ግን ራሱን ነው የሚሆነው። አያችሁ፡ በ—በዚያ መንገድ መሆን በጣም

ጥሩ ነው። መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ያለውን ዘር ይቀይረዋል። ምንም ዓይነት ዘር ቢሆን፡ ይለውጠዋል። ክፉ ከሆነ፡ ክፉን ያፈራል። ግብዝ ከሆነ፡ ግብዝ ያፈራል። እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ፡ የማሰብ ችሎታ ባለው ሰው ማጣሪያ አማካኝነት፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ ይወልዳል። ዘሩ ሲመጣ፡ በዚያ በኩል ይመጣል፡ የእግዚአብሔርን ወንድ ልጅና ሴት ልጅ ይወልዳል።

214 አንድ ቀን ዓለም በሁከት ጨለማ ውስጥ በነበረችበት ጊዜ፡ እግዚአብሔር... አሁን በጥንቃቄ አዳምጡ፡ ምክንያቱም ከ... ከዚህ በኋላ ረዘም ላለ ጊዜ ስለማንናገር። ተመልከቱ። አንድ ቀን ዓለም እንደገና በሁሉም ዓይነት ሃይማኖቶች ስትሞላ፡ እጅ መታጠብ፡ ማሰሮዎች፡ የተለያዩ ካባዎችንና መጎናጸፊያዎችን መልበስና፡ የመሳሰሉት ነገር ሲያደርጉ፡ ዓለም በድጋሜ በሁከትና ብጥብጥ ውስጥ ትገባለች። እውነተኛው የእግዚአብሔር ህዝብ እስራኤል ከእግዚአብሔር ህጎችና ሥርዓቶች በጣም ተዛብተው ነበር፡ ኢየሱስም እንዲህ አለ፡ "እናንተም፡ በሥርዓታችሁ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ ከንቱ አድርጋችኋል፡ በሥርዓታችሁ።" እነርሱንም ቅዱሳን ካህናትን ተመልከቷቸው፡ ራሳቸውን እንደዛ ይጠራሉ፣ ኢየሱስም፡ "እናንተ ከአባታችሁ፡ ከዲያብሎስ ናችሁ፡ የእርሱንም ሥራ ታደርጋላችሁ" አላቸው። አያችሁ፡ እርሱ በትክክል ያለው ያንን ነው።

215 አሁን ዓለም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በነበረችበት ጊዜ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ አስቀድሞ በተወሰነው ዘር ላይ እንደገና ተንቀሳቀሰ። በትንቢተ ኢሳይያስ 9፡6 ላይ የተናገረውን ቃል ተረጎመውና ለወጠው፣ እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ በሰው ሥጋ የተገለጠው፡ ያንን የሁከት ዘመንን ለማዳን ነው። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ሲፈጠር፡ እነሆ እግዚአብሔር፡ ነቢዩ አስቀድሞ በማየት... አሁን ቃሉን አስታውሱ፡ ነቢዩ አስቀድሞ አይቶት ነበር፡ ሰይጣንን በዚህ በመጨረሻው ዘመን ያየው ያው ነቢይ፡ አያችሁ፡ የዚህ የትምህርት ፕሮግራምና ያሉትን ነገሮችን፡ የሃይማኖት ፕሮግራሙን ያየው ነብይ። ተመሳሳይ ነቢዩ፡ ኢሳይያስ 9፡6 ላይ፡ እንዲህ አለ፡ "ሕፃን ተወልዶልናል፡ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፣ ስሙም 'መካር፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት' ይባላል። ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም" ብሏል። ይህ ቃል ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው። መንፈስም በዚያ ቃል ላይ ህይወትን ዘራ፡ በድንግል ማኅፀን ውስጥ ተፈጠረ። አሜን። "አንድ ልጅ ተወለደ፡" አልተፈጠረም፡ "ተወለደ።"

216 ዲያብሎስ እሱን ለመርጨት፡ ደጋግሞ ሞከረ። ኢየሱስን አንሥቶ እንዲህ አለው፡ "አንተ እኔ እንደዚህ ነኝ የሚትለውን ከሆንክ፡ እዚህ የተወሰነውን ፈውስ አድርግልኝ። እንዴት ማድረግ እንደምትችል አሳየኝ። ይህን እንጀራ፡ እነዚህን ድንጋዮችን ወደ እንጀራ ቀይር። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚናገሩት አንተ ይህን ታደርጋለህና፡ የሚታደርግ ከሆን እንመልከት" አለው።

217 የሃይማኖት አጋንንቶች ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ሲናገሩ ታያላችሁ? "መለኮታዊ ፈውስ የሚባል ነገር ካለ፣ እዚህ ላይ ወንድም **እጌሌ-እና-እጌሌ** ተኝቷል፡ እስቲ ስትፈውሳቸው እንይ።"

218 ይህ ተመሳሳይ ዲያብሎስ በኢየሱስ መስቀል አጠገብ ቆሞ፡

“የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ፡ ከመስቀል ውረድ፡” አለው።

219 ቃሉ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ተናግሯል። መንፈስም እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መስክሯል። ኢሳይያስ 9፡6 ተፈጽሟል። ባለፈው ምሽት፡ በተደረገው ስርጭት ብዙዎቻችሁ እንደሰማችሁ እርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ፡ ይመስለኛል፡ ሰልሳ-ያህል-እንግዳ የሆኑ፡ ጥቅሶችን እንደሰጠን ሰምታችኋል ብዬ አምናለሁ።

220 ኦህ፡ ደግሞ ደጋግሞ ሞከረ፡ ሁሉንም ነገር አደረገ። አንድ ምሽት፡ በጀልባው ከኋላ በኩል፡ ኢየሱስ ተኝቶ አየው። “አሁን አጠፋዋለሁ፡” አለው። ግን አልቻለም።

221 ኢየሱስ የተሳሳተ ነገር እንዲያደርግ ሊፈትነው ቢሞክርም፡ ነገር ግን አልቻለም። ለምን? አስቀድሞ መወሰን በሚባል መድኃኒት ተረጭቶ ነበር። ሊታለሉ አይችሉም። አይ፡ አይሆንም። ቃሉ እንደሚመጣ ተናግሯል። አሜን። እርሱን የሚረብሸው ዲያብሎስ የለም፡ የእርሱን ቦታ ለመውሰድ አስቀድሞ የታሰበ፡ ሌላ የእግዚአብሔር ልጅ የለም። አስቀድሞ ተረጭቷል። የሰይጣን መርዝ፡ የሃይማኖት ተቋም ዶክተሮች ጨርሶ አይነኩትም። እሱ ቀጥ ብሎ ይንቀሳቀሳል፡ ምንም ነገር አይረብሸውም፡ አያችሁ። ምንም ተጽዕኖ አላሳደረበትም።

222 “ደህና፡ የምድር ሁሉ ቢሾፕ አደርግሃለሁ። በእኔ ግዛት ስር ነው። ብቻ አምልከኝ እንጂ፡ ቡዱኔ ጋር ተቀላቀል እንጂ፡ ገ—ገዥ አደርግሃለሁ። ዝቅ ብዬ፡ አንተን ከፍ አደርግሃለሁ።”

223 እንዲህ አለው፡ “አንተ ሰይጣን፡ ወደ ኋላዬ ሂድ። ቃል ለሆነው፡ ለእግዚአብሔር፡ ለእሱም ብቻ ስገድ፡’ ተብሎ ተጽፏል።” ከዚያም አንድ ቀን...

በዚህ ታላቅ ሰው፡ ለተወሰነ ጊዜ እዚያ መቈየት እፈልጋለሁ።

224 ነገር ግን አንድ ቀን፡ መንፈስ ቅዱስ እንደገና በእርሱ ላይ ተንቀሳቀሰ፡ ምክንያቱም በነቢዩ በኩል፡ ከእግዚአብሔር የመጣ፡ ስለ እርሱ የተጻፈ አንድ ቃል ነበር፡ “እንደ ሚታረድ በግ፡ ተነዳ።” መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ተንቀሳቀሰ፡ መራው፡ ወደ ቀራንዮ መስቀል ላከው። በዚያም ሞተ። በሞቱም ስለ እርሱ የተነገረው ሁሉ፡ ተፈጸመ፡ ይህም የሆነው በምድር ላይ ላሉት አስቀድሞ ለተወሰኑ የእግዚአብሔር ዘር ሁሉ ብርሃንንና ሕይወትን ለማምጣት ነው። ይህን ለማድረግ መንገዱን አመጣ። ዘሩ **ይኸው** ነው፡ መንፈሱ ሕይወትን ያመጣል፣ የእግዚአብሔርን ወንዶችና ሴቶች ልጆች ይለውጣል፣ በዚህ ጨለማ ሁከት ውስጥ ካለው ዓለም፣ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወደመሆን ይለውጣቸዋል።

225 “አስቀድሞ መወሰን” በሚለው ቃል አትሰናከሉ። እንደምትሰናከሉ አውቃለሁ። ነገር ግን፡ ስሙኝ፡ ቃሌ አይደለም። ከእግዚአብሔር ቃሎች አንዱ ነው። ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ ከኤፌሶን 1፡5ን አንብቡ፡ ይህም፡ “እርሱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ልጆቹ እንድንሆን አስቀድሞ ወሰኖናል።” አያችሁ?

226 ይህን ለማብራራት አንድ ደቂቃ ብቻ ስጡኝ፡ በ አንድ፡ ከአእምሯችሁ ውስጥ ይህን ለማውጣት፡ አንድ ደቂቃ ብቻ ስጡኝ። ተመልከቱ። ልክ በመጀመሪያ፡ በዘር መልክ፡ በአባታችሁ ውስጥ እንደነበራችሁ ነው። ይህን ታውቃላችሁ፡

ሁላችሁም ይህን ታውቃላችሁ? በቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ አያታችሁም፡ ውስጥ ነበራችሁ፡ ይህን ታውቃላችሁ?

227 የዕብራውያንን መጽሐፍ አንብቡ፡ ሌዊ ከአብርሃም በኋላ በአራት ትውልዶች ውስጥ በነበረበት ጊዜ፡ አሥራት እንደከፈለ እናገኛለን። አብርሃም አሥራት ለመልከ ጼዴቅ በከፈለው ጊዜ፡ ከአብርሃም በታች ለነበረው ለልጅ-ልጅ-ልጁ አሥራት ተደርጐ ተቆጥሮለት ነበር፡ በዚያን ጊዜም በአብርሃም ወገብ ውስጥ ነበረ። ይሄው ተመልከቱ። አያችሁ?

228 በአባታችሁ ወገብ ውስጥ ነበራችሁ፡ ነገር ግን አባታችሁ ወደ ሥጋ አካል እስክትለወጡ ድረስ ከእናንተ ጋር ምንም ዓይነት ኅብረት ሊያደርግ አልቻለም።

229 ልጁ በውስጤ ነበር። እ—እ—አንድ ልጅ ፈልጐ ነበር፡ ነገር ግን እርሱ በዚያን ጊዜ በእኔ ውስጥ ነበር። አያችሁ? ያኔ በእኔ ውስጥ ነበር። ሆኖም በጋብቻ አማካኝነት፡ በእኔ ውስጥ የነበረው ልጅ ልክ እንደ እኔ አይነት ሰው ሆኖ ተቀየረ፡ ከዚያም እንደ እኔ ሆነ።

230 እንደ ወላጆቻችሁ ትሆናላችሁ፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም ገና ከመጀመሪያው፡ በውስጣችሁ ነበር። አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን፡ ባህሪው... ይህ ማለት፡ የአባታችሁ እንጂ፡ የእናታችሁ ባሕርይ አይደላችሁም፣ የአባታችሁ ናችሁ። ዘሩ በአባት ውስጥ ይቀመጣል። አያችሁ? አሁን እናታችሁ እናንተን የምትወልድ መራቢያ ነበረች፡ የአባታችሁን ዘር ትወልዳለች። አያችሁ?

231 ምድርም፡ በሥጋ፡ የእግዚአብሔርን ዘር የምትወልድ መፈልፈያ ናት። አያችሁ፡ በትክክል። ዓለማችን፡ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ሳይሆን፡ የፈጠረው አምላክ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ነው ነው። አያችሁ? አያችሁ?

232 እንግዲህ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ከሆናችሁ፡ ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ውስጥ ነበራችሁ። የእርሱ ባሕርይ ናችሁ። በዚያን ጊዜ በውስጡ ካልነበራችሁ፡ ከዚያም ፈጽሞ አልነበራችሁም ወይም አትሆኑምም።

233 ምክንያቱም፡ እኔ **የዚህን** ሰው ልጅ፡ ወይም **የዚያን** ሰው ልጅ፡ ከወገበ መውለድ አልችልም፡ የራሴን ልጆች ብቻ ነው መውለድ የምችለው፡ እነሱም የእኔን አምሳል ይወልዳሉ። ሃሌሉያ! አያችሁ?

234 ወንዶችና ሴቶች ልጆች ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ውስጥ ነበሩ። አሁን ተመልከቱ። የዘላለም ሕይወት አለን፡ ትላላችሁ። እኛ የዘላለም ሕይወት እንዳለን፡ እናምናለን። ደኅና፡ የዘላለም ሕይወት አንድ ዓይነት ብቻ ነው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው። ዘላለማዊ የሆነው ብቸኛው ነገር፡ እግዚአብሔር ነው። እንግዲህ የዘላለማዊ ሕይወት ካላችሁ፡ ያ ሕይወት በውስጣችሁ ሁሌም ነበር ማለት ነው፡ ዓለምም ከመፈጠሩ በፊት በእግዚአብሔር ወገብ ውስጥ ነበራችሁ። ኢ... ኢየሱስ ራሱ ቃል ተብሎ የተጠራ ሲሆን፡ በቅዱስ ዮሐንስ 1 ላይ፡ እንዲህ ብሏል፡ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃል ስጋ ሆነ በእኛም ዘንድ አደረ።" ከዚያም በኢየሱስ ወገብ ውስጥ ነበራችሁ፡ ከእርሱ ጋር ወደ ቀራንዮ ሄዳችሁ። ከእርሱ ጋር ሞታችሁ፡ ከእርሱም ጋር ተነስታችኋል። ዛሬ እኛ በእሱ ውስጥ በሰማያዊ ስፍራዎች ተቀምጠናል፡ በመንፈሱ ተሞልተናል፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ነን። አብረነው ሞተን፡ አብረነው ተነስተናል። በትክክል።

235 አሁን፡ አሁን፡ አሁን ከእሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ትችላላችሁ። ያኔ ህብረት ማድረግ አትችሉም፡ ምክንያቱም ገና በውስጡ ቃል፡ ዘር ነበራችሁ። ነገር ግን አሁን ገልጦአችኋል፡ አሁን ከእርሱ ጋር እንድትሆኑ ይፈልጋል። ከዚያም ወደ ታች ወርዶ፡ ከእናንተ ጋር ፍጹም ኅብረት እንዲኖረው ስጋ ለበሰ። ፍጹም ኅብረት አያችሁ? ኦህ፡ ማይ፡ እነዚያ ጥልቅ የእግዚአብሔር ሚስጥሮች! ምንኛ አስደናቂ ናቸው! አያችሁ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ሆኖ እያየነው ከእኛ ጋር ኅብረት ማድረግ ስላልቻለ፡ ሰው ሆነ።

236 ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠው፡ እግዚአብሔር ራሱ ነበር፡ ምክንያቱም፡ እሱ ልጅ ነበር ምክንያቱም ስለተወለደ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር የሚኖርበት ድንኳን ብቻ ነበር። “እግዚአብሔርን ያየው አንድም ሰው የለም፡ ከአባቱ ጐን የሚኖረው አንድያ ልጁ ስለ እሱ ተረከ።” እግዚአብሔር ለራሱ ቤት ሰራ፡ የሚኖርበትን አካል፡ ልትነኩት እንድትችሉ ወደ ታች ወርደ። አንደኛ ጢሞቴዎስ 3:16፡ “የእግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር፡ ያለጥርጥር ታላቅ ነው፣ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ፡ ለመላእክት ታየ፡ በአህዛብ ታመነ፡ ወደ ሰማይ ዐረገ።” አያችሁ? አሁን እርሱ...

237 እናንተ ሥጋ ስለሆናችሁ፡ እርሱም ሥጋ ነው፡ እንግዲህ አሁን ኅብረት ማድረግ ትችላላችሁ፡ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር የፍቅር ባሕርይ ስለሆነ። እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ትክክል ነው? ኢየሱስም የእግዚአብሔር የፍቅር ባሕርይ ነበር። የፍቅርም ባሕርይ በተገለጠ ጊዜ፡ ይህም፡ እግዚአብሔር ራሱ ነበር፣ በእርሱ ላይ የታዩ ባህሪዎች ሁሉ፡ ወደ እርሱ ይመጣሉ፡ “አባቴ የሰጠኝ ሁሉ፡ ወደ እኔ ይመጣል።” እርግጥ ነው፡ አስቀድሞ የተወሰኑ መሆን አለባቸው። ካልሆነ ግን፡ እዚያ አትገኙም። ያ ነው በቃ። በእርግጠኝነት።

238 አሁን እኛ ኅብረት ማድረግ እንችላለን፡ ይህም በ—በቃሉ ባለጠግነት አማካኝነት ነው፡ በዚህም ውስጥ አንድ አካል ናችሁ። የቃሉ አካል ናችሁ፣ ምክንያቱም እርሱ በመጀመሪያ ቃል ነበር፡ አሁን እናንተ ቃል ናችሁ። አያችሁ? ዛሬ ማታ፡ ወይም እሁድ ወይም አንድ ቀን፡ ስለ ቃሉ ምንነት እሰብካለሁ፡ አያችሁ። አሁንም የቃሉ አካል ናችሁ።

239 አዳምጡ። አንድ ነገር ማድረግ አልችልም። በቅድመ አያቶቼ መኩራራት አልችልም። አይ፡ በአስቃቂ ሁኔታ ውስጥ ነው የመጣሁት። አባቴ አይሪሽ ነበር። እናቴ ግማሽ ህንዳዊት የሆነች፡ ህንዳዊት ነበረች፣ እናቷ ህንዳዊት ነበረች፡ ጡረታ ወጥታ ነበር። አሁን፡ ሁሉም፡ ሰካራሞች፡ አብዛኞቹ ሁሉም ጫማዎቻቸውን አድርገው፡ በመታገል፡ በሽጉጥ ተዋጊዎች ሆነው፡ ወዘተ ሞቱ። አባቶቼ እና የቤተሰቦቼ ዛፍ አስከፊ ስለሆነ፡ ስለዚያ ምንም ነገር መኩራራት አልችልም።

240 ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ ልኩራራበት የምችለው አንድ ነገር አለ ልኩራራበት የምችለው በጌታዬ በኢየሱስ ነው እሱም አዳነኝ። በሚለውጠው ኃይሉ፡ አስቀድሞ በመወሰን አንድ ዘር ተከለ፡ እኔም አየሁት። አሁን የማን ልጅ ነኝ? እዎ። በእርሱ ልኩራራ እችላለሁ። በሕይወቴ ውስጥ ስላሳ-ሶስት ዓመታትን በእርሱ ላይ በመኩራራት፡ አሳልፌበታለሁ። ሌላ ሠላሳ-ሦስት ዓመት ቢሰጠኝ ኖሮ፡ በእሱ ላይ የበለጠ ለመኩራራት እሞክራለሁ። አያችሁ? በቅድመ አያቴ ላይ ልኩራራ እችላለሁ፡ ሃሌሉያ፡ ያዳነኝና የሕይወትን ዘር **እዚህ** የዘራ፡ እናም

በዚህ ቃል ላይ ወደ ታች እንድመለከት፡ መንፈሱን ልኮ እንዲህ አለኝ፡ “እነሆ ይሄው። **እንዲህ** ተናገር፡ ይሆናልም። **ያንን** አድርግ።” ኦህ፡ ማይ፡ በእርሱ ላይ ልኩራራ እችላለሁ! እንዴት አድርጓል? በቃል በውኃ መታጠብ፡ የመለየት ውኃ። ልንገልጸው ብንችል ደስ ይለኛል።

241 እውነተኛ አስቀድመው የተወሰኑ አማኞች የቃሉ አካል ስለሆኑ ከቃሉ ጋር ይቆያሉ።

242 ኦህ፡ እናንተ ተቅበዝባዦች ከዋክብት፡ እስከ መቼ ትቅበዘበዛላችሁ? እናንተ ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ፕሬስባይተሪያን፡ አውትሳይደርስ፡ ማንነታችሁ ምንም ይሁን ምን፡ ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን፡ ከአምድ ወደ ሰፍራ፡ ከቴሌቪዥን ወደ ቴሌቪዥን፡ ከዓለም ወደ ዓለም፡ የምትቅበዘበዙ ኮከቦች፡ ለምን አትመጡም? ከአንተ ጋር አንድ መሆንን ይናፍቃል። እሱ ይናፍቃችኋል። በእምሮአችሁ መታደስ ሊለውጣችሁ ይፈልጋል፡ ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለሃይማኖት ድርጅት ሳይሆን፡ ለቃሉ ነው፡ ይህም፡ ይህ ፍላጐት በውስጣችሁ ካለ የዚህ አካል ናችሁ።

**ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፡ ይጠግባሉና።**
(አያችሁ? ኡህ-ሁህ።)

243 ከገባችሁበት ከዚህ የሃይማኖት ብልሹነት እንዲያወጣችሁ፡ የመለወጥ ኃይሉን ልኮላችኋል። በዚህ ባለንበት የተዛባ ሁከት ውስጥ፡ እግዚአብሔር የሚለውጥ ኃይሉን ልኮልናል፡ ቃሉን፡ የተረጋገጠውን፡ የጸደቀውን፡ ከዚህ ከሃይማኖት ብልሹነትና ከምትሄዱበት ድንቁርና ያወጣችኋል፡ “የተራቆትህ፡ ዕውር፡ ድሃ፡ መሆንህንም አታውቅም።” አሰቡበት፡ ወዳጆቼ።

244 እግዚአብሔር ቃሉን ለመፈጸም፡ የመለወጥ ኃይሉን በመላክ የሣራንና የአብርሃምን ሰውነት መሉ በሙሉ እንደለወጠ፡ ታውቃላችሁ። እንዲሁ አደርጋለሁ ብሎ ቃል እንደገባ፡ ሽማግሌውን ሰውዬንና አሮጊቷን ሴት ለወጣቸው።

245 እግዚአብሔር ቃል የገባውን ነገር፡ ይፈጽማል። ምንም ቢሆን፡ ምንም ነገር... ከተጣመመ ማንኛውም ነገር፡ እግዚአብሔር ምንም ነገር ማድረግ አይችልም። ይሁን እንጂ ቃሉን ይጠብቃል፡ መንፈሱንም ይልካል! “እኔ እግዚአብሔር ተከልሁት። ማንም ከእጄ እንዳይነቅለው፡ ቀንና ሌሊት አጠጣዋለሁ።” መጽሐፍ ቅዱስ ይላል።

246 ኦህ፡ የሚንከራተቱ ከዋክብት፡ በልባችሁ ውስጥ ያለ ፍላጎት! ይህን ማድረግ አለባችሁ፡ አለበለዚያ ዛሬ ጠዋት እዚህ አትቀመጡም ነበር። በእነዚያ አብያተ ክርስቲያናትና አዳራሾች፡ ባላችሁበት ሁነታ፡ ውጭና በገሪቱ ሁሉ ያላችሁ፡ የሆነ ነገር ወደዚያ ባያመጣችሁ ኖሮ በዚያ ሁኔታ በዚህ ሁኔታ አትሆኑም ነበር። አንድ ሰው ተናግሯችኋል። ከዚህ በላይ አትሂዱ። እንደ በረዶ ነጭ የሚያደርግ፡ በቃል በውኃ መታጠብ አለ። ኦህ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ሆይ፡ ስሙኝ! በዚህ ብልሹነት ውስጥ አትቆዩ። ከዚህ ውጡ! አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፡ ከዚህ ተቃራኒ የሆነን ነገር ሁሉ...

247 እንዲህ ትላላችሁ፡ “እኔስ በምን እተዳደራለሁ? እንዴት ነው **ይህን** የማደርገው? ” እሱ የእግዚአብሔር ጉዳይ ነው። “እንዴት ማድረግ እችላለሁ? ባልደረቦቼ እምቢ ይሉኛል።”

248 እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ “አባቱን፡ እናቱን፡ ሚስቱን፡ ባሏን፡ ቤቱን፡ ቤቶችን የሚተው፣ በዚህ ዓለም ቤቶችን፡ አባቶችንና እናቶችን፡ ወንድሞችንና እኅቶችን እሰጣቸዋለሁ፡ በመጪውም ዓለም፡ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ።” ቃል ኪዳን ነው፡ ወዳጆች። ይህ፡ ኦህ፡ ይህ ውኃ ማጠጣት አለበት! እግዚአብሔር የገባው ቃል ሁሉ ይፈጸማል። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ዘር ተሰፋ ነው።

249 እኛ፡ እኅቴ ሆይ፡ ፀጉርሽን መቆረጥ አቁሚ፡ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት ያልተለመደ ነገር ነው። እነዚህን ልብሶች መልበስ አቁሙ፡ ለእርሱ አስጸያፊ ነገር ነው!

250 እናንተ ወንድሞች ሆይ፡ እናንተም ሰዎች ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች እያደረጋችሁ፡ ሴቶቻችሁንም እንዲህ እንዲያደርጉ አየፈቀዳችሁ፡ የሃይማኖት ተቋማችሁን ማገልገላችሁን አቁሙ። ይህ ለክርስቲያኖች የማይገባ ነው።

251 ወደ ቃሉ ተመለሱ! ቃሉን ውሰድ፡ ያድጋል። ማደግ አለበት። በመጀመሪያ ደረጃ ወደ ላይ ያመጣው የእግዚአብሔር የመለወጥ ኃይል፡ ወደ ኋላ በሚወሰደው መንገድ ላይ ነው፡ አሁን እንደገና ወደ ኋላ እየወሰደ ነው። ወደነበረበት ተመልሶ ይሄዳል።

252 ሄኖክ ከሞት፡ በሚለውጠው በእግዚአብሔር ኃይል፡ ተለወጠ። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ለምንድነው? ለምትመጣው የምትነጠቅ ቤተክርስቲያን ምሳሌ ነው። አዎን። ኤልያስም እንደዚያው ነበር።

253 የኢየሱስ ስጋ ከሞተ በኋላ ሕያው ሆነ። በመቃብሩ ውስጥ፡ የኢየሱስ አካል በእግዚአብሔር ቃል ሕያው ሆነ፣ ከሞተ፡ ከቀዘቀዘ ምስል፡ ተለወጠ፡ ትንሣኤን አገኘ፡የተከበረ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነ። ምክንያቱም ነቢዩ፡ በመዝሙር 16፡10 ላይ፡ ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ በ16፡10 ላይ፡ እንዲህ ብሏል፡ “ነፍሱን በሲኦል አልተወውም፡ ቅዱሴንም መበሰበስን አያይም።” አምላክ ሆይ!

254 ይህ ቃል መፈጸም አለበት፡ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው! መነጠቅ ከፈለጋችሁ፡ በልባችሁ ውስጥ ትከሉት። እውነተኛ ክርስቲያኖች መሆን ከፈለጋችሁ፡ ይህን ቃል ተጠቀሙበት። ሕዝቅኤል ይመስለኛል፡ እግዚአብሔር፡ “ይህን መጽሐፍ ወሰደህ ብላው” አለው፡ ነቢዩና ቃሉ አንድ ይሆናሉ። ቃል የተገባው ነገር ሁሉ መፈጸም አለበት፡ ምክንያቱም ቃል የገባው ነገር የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ዘር ስለሆነ። እዚህ ያለ አንድ የተማረ የሃይማኖት ምሁር ከውስጣችሁ ለማውጣት እንዲሞክር አትፍቀዱ። በሥጋዊው ሳይንስና እውቀት፡ እንዲሁም በትምህርቱ እንዲረጭባችሁ አትፍቀዱለት። እግዚአብሔርን እመኑ!

255 አብርሃም በዘመኑ የነበረውን ሳይንሳዊ ምርምር አልወሰድም፡ “ልጅ ለመውለድ በጣም፡ በጣም ሩቅ ሄጃለሁ። **ይህንን**፡ **ያንን**፡ ወይም **ሌላውን** አድርጌያለሁ፡” አላለም። ነግር ግን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር፡ የሚቃረነውን ማንኛውንም ነገር፡ እንዳልነበረ አድርጎ ይቆጥረው ነበር። ባለማመን፡ የእግዚአብሔርን ተሰፋ አልተጠራጠረም፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን እያከበረ፡ በኃይል ጸና። እግዚአብሔር የሰጠውን የተሰፋ ቃል ለመፈጸም እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቅ ነበር።

256 ኦህ፡ በዚህ ምድር ላይ ባሉ አረጎች የተጣመማችሁ፡ የምትቅበዘበዙ ልጆች ሆይ! ተቅበዝባዥ እሳቶች ሆይ፡ የዚህ ዓለም ሰፍራዎችና ፋሽኖች የሳቧችሁ! እና፡ እህቴ ውዴ፡ ምንም እንደማያገባው ተራ ሽማግሌ ልትቆጥሪኝ ትችያለሽ፡ ነገር ግን ከእነዚህ ቀናት በአንዱ ፍሎረንስ ሻካሪያን በቀደም ምሽት ያጋጠማት ሲያጋጥምሽ፣ እንደምታውቁት፡ እሷም፡ በዚህ ክፍል ውስጥ፡ በዚህ ቦታ ተቀምጣ ነበር። ይህ ሲያጋጥምሽ፡ እኔ ሳይሆን፡ ይህ ቃል ትክክል መሆኑን፡ ታውቂያለሽ። ከፀጉር አስተካካዮች ሱቆች፡ ከፋሽን ሱቆች ውጪ። ከእነዚህ ነገሮች ራቂ።

257 እንዲህ ትላላችሁ፡ "እንዴት **እንዲህ** መሆን እንደሚቻል፡ ለምን ታላላቅ ነገሮችን አታስተምራቸውም?" ከኤቢሲ ጀምረን፡ ከዚያም ወደ አልጀብራ እንመጣለን። እያችሁ? ብቻ መማር ጅምሩ፡ "ይህም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።"

> **እንግዲህ፡ ወንድሞች ሆይ፡ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ።** ሥጋችሁን **እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና፡ ሕያው፡ ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ፡ ይህ ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።**

258 ይህን "ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁን" ብቻ አድርጉ፡ ሌላው የእግዚአብሔር ሰራ ነው፥ እያችሁ፡ መርምራችሁ ልታደርጉት የምትችሉትን ነገር አድርጉ። መ... መጽሐፍ ቅዱስ ያወገዘው ነገር፡ ሴት እርቃኗ ሆና ወጥታ ስትሄድ እንደዛ ስትሆን እንዲህ ዓይነት ድርጊት መፈጸሟ፡ ምክንያታዊነት የጐደለው ነገር አይደለምን? ይህ ሁሉ የሴሚናሪው ነገር፡ እንደዚህ ያሉ ነገሮች እዚህ ያለው ሁሉ ነገር፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ፍጹም ተቃራኒ በሆነ ጊዜ፡ አንድ ሰው ራሱን በዛሬው ጊዜ ባለንበት ዓይነት ዶግማ ውስጥ ማስገባት፡ ምክንያታዊነት የጐደለው ነገር አይደለምን? እያችሁ?

259 የኢሳይያስ ከንፈሮች፡ የረከሱ ከንፈሮች ያሉት ተራ ሰው ነበር። እንዲህ አለ፡ "ጌታ ሆይ፡ እርኩስ ከንፈሮች ባሉበት ርኩስ ሕዝብ መካከል ነኝ፡ እኔም ከንፈሩ የረከሱበት ሰው ነው። እግዚአብሔርን አይቻለሁና ወዮልኝ" አለ። መልአክም ወርዶ እሳቱን፡ እሳቱን ወሰደ፡ ቅዱስ እሳቱን ከእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ ወሰዶ፡ ከንፈሩን ቀየረው፣ ከተንከራታች ሰው ከንፈር፡ ወደ **ሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ወደሚል ነብይ ከንፈር ለወጠ። የእግዚአብሔር የሚለውጥ ኃይል!

260 አንድ መቶ ሀያ ዓሣ አጥማጆች፡ እ—እና ጥቂት ሐመራዊ ሃር የሚሸጡ፡ ሴቶች፡ እነዚያም ሰዎች በላይኛው ክፍል ውስጥ ተሰበሰቡና በሮችን ዘጉ፡ ከእነርሱም አንዳንዶቹ ሰማቸውን ለመፈረም በቂ ትምህርት ያልነበራቸው ናቸው። እግዚአብሔር ከአሳ አጥማጆች፡ ወደ ሰው አጥማጆች፣ ከጎዳና ተዳዳሪ ወንዶችና ሴቶች፡ ወደ እግዚአብሔር ቅዱሳን፡ ወደ ዘላለማዊነት ቀየራቸው። የሚለውጥ የእግዚአብሔር ኃይል!

261 ጳውሎስ፡ የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን አባል፡ የፕሬስባይተሪያን፡ የሜቶዲሰት፡ የባፕቲሰት፡ የጴንጤቆስጤ፡ ወይም የመሳሰሉት፣ ከማንኛውም ሰው በላይ የሚያውቀውን፡ ታላቅ የድፍረት መንፈሱን ይዞ፡ ጐዳናውን ተጓዘ። ያደገው በአገሪቱ ውስጥ ካሉት ምርጥ አስተማሪዎች አንዱ በሆነው፡

በገማልያል ትምህርት ቤት ነው። ወደ ደማስቆ በሚወሰደው መንገድ ላይ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለሚያምኑ ብዙ ሰዎች ሲያስር ምን ተፈጠረ? ወደዚያ በሚወሰደው መንገድ፡ ሲወድቅ፡ አንድ መልእክት ሰማ። ያ ከቤተክርስቲያን አባልነት ከቤተክርስቲያን ተጓዥነት፣ ወደ እግዚአብሔር ነቢይነት፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ፡ የእግዚአብሔርን ቃል የጻፈ ሰው አደረገው። ከቤተ ክርስቲያን አባልነት ወደ ቅዱስነት!

262 ኦህ፡ ተቅበዝባዥ ኰከቦች ሆይ፡ እንቁም! ተቅበዝባዥ ልጅ፡ ተቅበዝባዥ ዘር በዚህ ብልሹነት፡ ከቦታ ቦታ የሚትዞረው፣ ዛሬ ጠዋት፡ ተመለሱ፡ ልጆቼ። እባካችሁ በሕያዋንና በሙታን መካከል ለመቆም የሚሞክር ሰው እ— እንደመሆኔ መጠን ስሙኝ።

263 ሰርጭቱ በሚተላለፍበት ቦታ ያላችሁ ሰርጭቱ አሁንም ያልተቋረጠ ከሆነ፡ ወደዚህ ዝም ብላችሁ የመጣችሁ፡ እባካችሁን አንድ ደቂቃ ብቻ ቁጭ በሉ። እዚህ በቱክሰን እንዳረፈድን አውቃለሁ ወይም፡ ይቅርታ አድርጉልኝ፡ በፊኒክስ፡ አስራ ሁለት ሰዓት ሊሞላ ሃያ ደቂቃ ብቻ ነው የሚቀረው። እነዚህን ሰዎች ሁሉ እዚህ አቆየኋችሁ። ከስራችሁና ከነገሮቻችሁ ከልክ እዚህ አቆየኋችሁ። ነገር ግን ተመልከት፡ ውድ ጓደኛዬ፡ ለዘላለም ከአምላክ ርቀህ ልትኖር ትችላለህ። እባክህ ዛሬ ጠዋት ተመለስ ና። አትመጣም? በምንጭ ላይ ቦታ አለ።

ከረጅም ጊዜ በፊት፡ በበረት የሆነውን አውቃለሁ፡
ሰዎችን ከኃጢአታቸው ለማዳን ሕፃን ተወለደ።
ዮሐንስ በባሕሩ ዳርቻ አየው፡ በጉን ለዘላለም፡
ኦህ፡ በቀራንዮ የተሰቀለው፡ ክርስቶስ።

ኦህ፡ ያንን የገሊላ ሰው እወደዋለሁ፡ የገሊላ ሰው፡
ለእኔ በጣም ብዙ አድርጎልኛልና።
ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር ብሎኛል፡ መንፈስ ቅዱስን በውስጤ አሳድሮልኛል፡
ኦህ፡ እወደዋለሁ፡ ያን የገሊላ ሰው እወደዋለሁ።

አንድ ቀን ቀራጩ ወደ መቅደስ ሊጸልይ ሄደ፡
"አቤቱ፡ ጌታ ሆይ ማረኝ!" እያለ ጮኸ፡
የኃጢአቱ ሁሉ ይቅር ተባለ፡ ውስጡም በሰላም ተሞላ፣
እንዲህም አለ፡ "ኑ ይህን የገሊላ ሰው እዩት።" (በትክክል።)

አንካሳው ተራመደ፡ ዲዳው ተናገረ፡
ሃይሉ በባህር ላይ በፍቅር ተነገረ፣
ዓይነ ሰውራን ማየት ቻሉ፡ እኔ ብቻ ሊሆን እንደምችል አውቃለሁ
የዚያ የገሊላ ሰው ምሕረት።

264 ከዛሬው ጊዜ አገልግሎት ጋር አመሳስሉት።

በጉድጓዱ አጠገብ የነበረችው ሴት፡ አምስት ባሎች እንደነበሯት፡
የፈጸማቸውን ኃጢአቶች ሁሉ ነገራት።

የኃጢአት ይቅርታን ሁሉ አገኘች፡ ጥልቅ ሰላም በልቧ
ተቀመጠላት፣
"ኑ ይህን የገሊላ ሰው እዩት!" እያለች ጮኸች፡

265 ሴቶች ሆይ፡ ተመሳሳይ ነገር ሊያደርግ ይችላል። ዛሬ ጠዋት ልብሽን አንብቧል። ወንድ ሆይ፡ ልብህን አንብቧል። ኦህ፡ ቀራጭ ሆይ፡ እንጸልይ!

ኦህ፡ ያንን የገሊላ ሰው እወደዋለ፡ የገሊላ ሰው፡
ለእኔ በጣም ብዙ አድርጎልኛልና።
ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር ብሎኛል፡ መንፈስ ቅዱስን
በውስጤ አሳድሮልኛል፣
ኦህ፡ እወደዋለሁ፡ ያን የገሊላ ሰው እወደዋለሁ።

266 ዛሬ ጠዋት፡ ከእኔ ጋር ሆናችሁ፡ አትወዱትምን? ኦህ፡ አንተ ተጓዥ፡ ተቅበዝባዥ ኃጢአተኛ ሆይ፡ እዚህም ሆነ ውጭ የትም ብትሆ፡ ዛሬ ጠዋት ጌታዬን ትቀበላለህ? እርሱ ቃል ነው፡ ቃሉም ወደ እናንተ መጥቶአል። ታዲያ ዛሬ ጠዋት አትቀበሉትምን? እጆቻችሁን ታነሳላችሁ ወይም በእግራችሁ ቁሙ፡ ወይም ሌላ ነገር፡ ትጸልያላችሁ፡ እንዲህ በሉ፡ "እርሱን አሁን መቀበል እፈልጋለሁ። ወንድሜ ሆይ፡ ፈቃደኛ ነኝ። እሱን አሁን መቀበል እፈልጋለሁ።" እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ፡ በእግሮቻችሁ ትቆማላችሁ፡ እንዲህም በሉ፡ "እኔ... " ይልቁንስ፡ እንዲጸለይላችሁ፡ "እ... እኔ ኃጢአተኛ ነኝ።" ጌታ ይባርክህ፡ ወዳጄ። ሌላ ሰው? ሁሉም ሰው አሁን ይጸልይ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ።

ኦህ፡ ከረጅም ጊዜ በፊት፡ (ታውቃላችሁ፡ ዓለም፡ በሁከት
ውስጥ ነበረች።) በበረት የሆነውን አውቃለሁ፡
ሰዎችን ከኃጢአታቸው ለማዳን ሕፃን ተወለደ።
ዮሐንስ በባሕሩ ዳርቻ አየው፡ በጉን ለዘላለም፡ (ዛሬም
ያው ነው።)
ኦህ፡ በቀራንዮ የተሰቀለው፡ ክርስቶስ።

267 ዛሬም እርሱን በፍጹም ልባችሁ አትወዱትም፡ በዚህ ዓለም ውስጥ ካላችሁበት ሁኔታ መውጣት ትችሉ ዘንድ? እናንተ ሴቶች፡ እናንተ ወንዶች፡ ኦህ፡ በዚህ ጊዜ ሁሉ ለምን ተቀመጣችሁ? ይህ የሚያመለክተው በውስጣችሁ የሆነ ነገር እንዳለ ነው፡ የሚራብና የሚጠማ ነገር በውስጣችሁ እንዳለ ነው። በዚህ ሕንጻ ውስጥ ለሁለት ወይም ለሦስት ሰዓታት፡ እዚህ መቀመጥ አትችሉም ነበር፣ የሆነ ነገር አለ። ዛሬ ለምን አትታዘዙትም? ውድ ወንድሜ ወይም እድ እኅቴ፡ ፋሽንና ሳይንስ፡ ዓለም ነገሮች ሁሉ፡ ከአእምሯችሁ ውስጥ አሁን ይውጡ።

አብያተ ክርስቲያናት አንድ እየሆኑ ነው፡ ታላላቆቹ አገሮች
እየፈረሱ ነው፡ እስራኤል እየነቃች ነው፡
ነቢያት ያሉት ምልክት ሁሉ፣
የአሕዛብ ዘመን አልቆ፡ ጭንቀታቸውም ተገድበዋል፡
"እናንተ የተበተናችሁ፡ ወደ ቀያችሁ፡ ተመለሱ።"

የቤዛው ቀን ቀርቧል፡
የሰዎች ልብ በፍርሃት ወድቋል፣
በመንፈስ ተሞሉ፡ መብራቶቻችሁን ሙሉና አዘጋጁ፡

አይናችሁን እነሆ ተመልከቱ! ቤዛችሁ ቀርቧል።
ሐሰተኛ ነቢያት ይዋሻሉ፡ የእግዚአብሔርን እውነት ይክዳሉ፡
ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችን ነው።

268 አሁን፡ ያ እውነት ነው። ሁላችንም፡ የምንኖርበትን ዘመን፡ ታውቃላችሁ። እርሱ ግን እንዲህ አለ፡

ምሽት ላይ ብርሃን ይሆናል፡
ወደ ክብር መንገድ በእርግጥ ታገኛላችሁ።

269 አሁን የምንኖርበት ዘምን ይህ ነው። ብርሃኑ የሚያንጸባርቀው ምሽት ላይ ጨለማው ሲገባ ነው፡ በመሸ ጊዜ፡ የምሽት ኰከብ ያበራል።

የጨለማ እና የምሽት ኮከብ፡
ከዚያም በኋላ ጨለማ!
የመሰናበቻ ሀዘን እንዳይኖር፡
በመጨረሻ ሰሳፈር፣

ያለ ሁሉ የጊዜና የቦታ ዋጋ ነውና፡
ጎርፍም ብዙ ይወሰደኛል፡
ነግር ግን አብራሪዬን ፊት ለፊት ማየት እፈልጋለሁ
ያንን ዲልዲይ ስሻገር።

ሀዘን ብቻ መሆኗን፡ አትንገረኝ፡
ያ ሕይወት ባዶ ሕልም ብቻ መሆኑን!
ያንቀላፋች ነፍስም ሞታለች፡
ነገሮችም እንደሚመስሉት አይደሉም።

አዎ፡ ሕይወት እውነተኛ ነው! ሕይወት ቅን ናት!
መቃብርም ግቡ አይደለም፣
አፈር ነህና፡ ወደ አፈር ትመለሳለህ፡
ይህ ሰለ ነፍስ አልተነገረም።

የታላላቅ ሰዎች ሕይወት ያሰታውሰናል
ህይወታችንን ምከፍ ከፍ ማድረግ እንችላለን፡
እና፡ መለያየት፡ ከኋላችን ተወው፡
በዘመናት አሸዋ ላይ ያሉ አሻራዎች፣

የእግር አሻራዎች፡ ወይም ሌላ፡
የሕይወትን ዋነኛ ፈተናዎች እየተጓዘ ሳለ፡
የቀረና መርከቡ የተሰበረበት ወንድም፡
በማየት፡ እንደገና ልብ ያገኛል።

እንግዲያውሰ፡ ተነሥተን፡ እንሥራ።
ከልብ ለሚመጣው መከራ፣
እንደ ደደብ፡ ከብት አትሁኑ!
በጦርነቱ ጀግና ሁኑ!

270 ውድ አምላክ ሆይ፡ እነሱ የአንተ ናቸው። ሁለት ሰዎች በእግራቸው ላይ ቆመው አይቻለሁ፡ አባት ሆይ። አምላክ ሆይ፡ አሁን እንድትቀበላቸው፡

እጸልያለሁ። ልጆችህ መሆን ይፈልጋሉ። የኖሩበትን ሕይወት ባለማወቅ ከአንቅልፋቸው ነቅተዋል፡ እናም ዛሬ ፍሬሽ እና አዲስ መሆን ይፈልጋሉ፡ ይህም በዚህ ዘመን በልባቸው ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በተተከለው ዘር ነው። የዘላለም አምላክ ሆይ፡ የሁሉም ነገር ፈጣሪ ሆይ፡ ቃልህን የጻፍከው፡ እነዚህ ሰዎች ዛሬ ጠዋት የሚያደርጉትን እንደምታውቅ አምናለሁ። ጌታ ሆይ፡ ይህን ቃል፡ ቀንና ሌሊት እንድታጠጣቸው፡ እጸልያለሁ፡ ሰይጣንም ከእጅህ እንዲነጥቀው አትፍቀድለት። አንዳንድ ጊዜ፡ በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ፡ ሁሉም ነገር ተመልሶ ሲመጣ፡ ቃልህ ሊወድቅ ስለማይችል፡ እንደገና ይሆናል። ለዚህ ዓለም...

271 እንዲህ ዓይነቱ ሥልጣኔ በሚመጣው ዓለም ላይ አይኖርም። አውቶሞቢሎች አይኖሩም ወይም ሳይንስ ያደረጋቸው ነገሮች አይኖሩም። በመጪው ዓለም እንዲህ ዓይነት ነገር አይኖርም። ነገር ግን እግዚአብሔር በክብሩ አገዛዝ ውስጥ የሚያቋቁመው፡ የራሱ ዓይነት ሥልጣኔ ይሆናል። ምክንያቱም፡ በዚህ ሥልጣኔ ውስጥ በሽታ፡ ሞት፡ ኀዘን፡ መቃብርና፡ ድህነት አለ። በሚመጣው መንግሥት ግን፡ ሞት የለም፡ ሐዘን የለም፡ ሕመም የለም፡ እርጅናም የለም። ኦህ አምላኬ ሆይ፡ በሰልጣኔህ ውስጥ፡ ሁሉም ነገር አዲስ ይሆናል።

272 አምላካችን ሆይ፡ ዛሬ በኃይልህ፡ በአእምሮአችን በመታደስ፡ ለውጠን፡ ከዚህ ዓለም ደካማ አካላት፡ አሁን ወደ እግዚአብሔር ቃል እንድንዞር አድርገን። በልባችን ውስጥ ባለው ዘር አማካኝነት በእግዚአብሔር በሚለውጥ ኃይል፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ተብለው ወደሚጠሩ ፍጥረታት፡ እንደሚትለውጠን እናምናለን። አባታችን ሆይ፡ ለሕዝቡ፡ በኢየሱስ ስም፡ እጸልያለሁ። አሜን።

273 አሁን በየትኛውም ቦታ፡ በሰርጭቱ ውስጥ ላላችሁ ሁሉ፡ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችሁ አድርጋችሁ፡ እንድትቀበሉትና፡ በመንፈሱ እንድትሞሉ እፈልጋለሁ። ዛሬ ጠዋት የተነገሩት ቃላት፡ ወደ ልባችሁ ይግቡ። እናንተም ኢየሱስን ተቀበሉ። ሕይወታችሁን ትመለከታላችሁ፡ ከዚያ በኋላ ምን እንደምትኖሩ ታያላችሁ። ይህም የሚያስብ ሰው ማጣሪያ ውሰዱ። ከቃሉ ጋር የሚቃረን ነገር እያደረግህ እንደሆነ ከተሰማህ፡ ፈጥነህ፡ አቁመው። አያችሁ? ምክንያቱም፡ ሞት ከአንተ እንዲርቅ የሚያደርግ ማጣሪያ አለ፡ ይህም የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሎቹ ሕይወት ናቸው፡ ከሞት ይጠብቃችኋል።

274 እናንተ ሰዎች አሁን አዳራሹ ውስጥ ያላችሁ፡ እዚህ ለረጅም ጊዜ አቆየኋችሁ። በስብሰባው ላይ በመገኘታችሁ አመሰግናችኋለሁ። አምላክ ይህ ዘር እንዲሞት ፈጽሞ እንዳይፈቅድ እጸልያለሁ። እነዚህ ነገሮች የተለየ ሰው ለመሆን እንደተናገርኩ እንደማታስቡ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህን የምለው በፍቅር ተነሳስቼ ነው፣ ለሰዎች መሰበክ የምችልበት ብቸኛው ጊዜ፡ አሁን እንደሆንኩት፡ ሟች መሆኔን በማወቄ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን እወደዋለሁ። አዳኜም ነው። አስታውሱ፡ እሱ ባይሆን ኖሮ በጐዳና ላይ እዚያ እገኝ ነበር። እዚያ እገኝ ነበር፣ ወላጆቼ፡ ወገኖቼ ሁሉ፡ ኃጢአተኞች ነበሩ። ነገር ግን እግዚአብሔር፡ በሚለውጠው ኃይሉ አማካኝነት፡ ከእኔ የተለየ ፍጥረት እንደፈጠረ አውቃለሁ። ጥ—ጥሩ እንዲትሆኑ፡ ልመክራችሁ እችላለሁ። በችግር ጊዜ ይጠብቃችኋል። በሞት እንኳን፡ በሩ ላይ፡ ምንም ፍርሃት አይኖራችሁም። “በክርስቶስ ውስጥ

ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር፡ ሊለየን የሚችል ምንም ነገር የለም።" እግዚአብሔር እያንዳንዳችሁን ይባርክ፡ የዘላለምም ሕይወት ይስጣችሁ።

275 እዚህ ውስጥ የእግዚአብሔር ዘር የሌለው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያላገኘ ስንት ሰው አለ? እጃችሁን ከፍ አድርጋችሁ፡ እንዲህ በሉ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ መንፈስ ቅዱስን እንድቀበል፡ አስታውሰኝ።" አሁን ቃሉን በ— በልባችሁ ያዙ፡ እመኑትም። ራ... ራሳችሁን መመልከት ትችላላችሁ። ሂዱና በመስተዋት ተመልከቱ፡ የት እንዳላችሁ ማየት ትችላላችሁ። አያችሁ፡ ማወቅ ትችላላችሁ።

276 "መልካም፡ እጄን አላነሳሁም፡ እንዳለኝ አምናለሁ፡" ትላላችሁ።

277 ራሳችሁን በመስተዋት ተመልከቱ፡ ከዚያም ምን አይነት መንፈስ እያታለላችሁ እንደሆነ ታያላችሁ፡ አያችሁ። የተታለለ አስተሳሰብ! "ለሰው ቅን የሚመስል መንገድ አለ፡ ፍጻሜው ግን የሞት መንገድ ነው።" ይህ እውነት ነው?

> በመስቀል ሞተ መድኃኒቴ፡
> እኔን ለማዳን ከኃጢያቴ፡
> ኦህ፡ በደሙ መረጨት ከጥፋቴ፡
> ክብር...

278 ለአንድ ደቂቃ ብቻ፡ አይናችሁን ጨፍናችሁ፡ ለእርሱ ብቻ ዘምሩ። እጃችንን ወደላይ እናንሳ።

> ክብር ለስሙ! (የእሱ ውድ ስም!)
> ክብር ለስሙ!
> ደሙ በልቤ ላይ ነው፥
> ክብር ለ...

279 እናንተ ክርስቲያኖች የዳናችሁ፡ እርስ በርሳችሁ እጅ እንድትጨባበጡ እፈልጋለሁ።

> በድንቅ ከኃጢያት አዳነኝ፡
> ኢየሱስ በእረፍት ውስጤ ኖረልኝ፡
> በመስቀሉ እኔን አስገባኝ፡
> ክብር ለስሙ!
>
> ክብር ለስሙ! (የተከበረ ስም!)
> ክብር ለስሙ!
> ኦህ፡ ደሙ በልቤ ላይ ነው፣
> ክብር ለስሙ!

280 ደሙ የሕይወት ዘር በውስጡ እንዳለው፡ ታውቃላችሁ። ይህ እርሱን ለማያውቁ ሰዎች ነው፡

> ኦህ፡ ወደዚህ ምንጭ ወደ ሀብታምና ጣፋጭ ኑ፣
> ምስኪን ነፍሳችሁ ከእግሩ ስር አኑሩ፡
> ኦህ፡ ዛሬ ወሰዳችሁ፡ ፍጹማን ሁኑ፣
> ክብር ለስሙ!
>
> ኦህ፡ ክብር ለ...

ይህን መዝሙር ስንዘምር ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

ክብር ለስሙ!
ደሙ በልቤ ላይ ነው፣
ክብር ለስሙ!

281 ትወዱታላችሁ? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] ጳውሎስ፡ “በመንፈስ እዘምራለሁ። በመንፈስ አመልካለሁ” ብሏል። እጆቻችንን ወደ ላይ በማንሳት፡ እንደገና በዝግታ እንዘምር።

282 ታውቃላችሁ፡ ችግሩ፡ እኛ የጴንጤቆስጤ ሰዎች፡ ደስታችንን አጥተናል፡ ስሜታችንን አጥተናል። ቢሊ ግራሃም ባለፈው ምሽት እንደተናገረው፡ “እነዚያ ሰባኪዎች፡ ኮሊታቸውን አጥፈው፡ ወደ ደቡብ እየሄዱ፡ እጃቸውን እያጨበጨቡ፡ እግሮቻቸውን መሬት ላይ ወደላይ-እና-ወደ ታች እያደረጉ፡ እየዘለሉ፡ ደስ የሚላቸው ነገር ነበራቸው።” ደኅና፡ አዎ፡ የምደሰትበት ነገር አግኝቻለሁ። አያችሁ? አያችሁ? አዎ። አዎ፡ ስሜታችንን አጥተናል።

283 አሁን እጆችንን ብቻ እናንሣ። ስለ እንባዎች አትጨነቁ፡ ምንም አይጐዱም፡ አያችሁ። አይጐዱም። “በእንባ፡ ዘር ለመዝራት የሄደ ሰው፡ ውድ እህል ይዞ እንደሚመለስ፡ ጥርጥር የለውም።” መልካም።

ክብር ለስሙ ይሁን! (የተከበረ ስም!)
ክብር ለስሙ!
ደሙ በልቤ ላይ ነው፣
ክብር ለስሙ!
ክብር ለእርሱ ይሁን... (አምላክ ሆይ! እግዚአብሄር ይመስገን!)
ክብር ለስሙ!

ጌታ ሆይ፡ ዘሩን በልባችን ውስጥ፡ አኑር!

... ደሙ በልቤ ላይ ነው፣
ክብር ለስሙ!

65-0911 የሚለውጥ የእግዚአብሔር ኃይል
ራማዳ Inn
ፊኒክስ, አሪዞና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org